‹‹ማኅበረ ቅዱሳን›› እግዚአብሔር ያከበራቸው የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ ትሩፋትና አማላጅነት የሚዘከርበት በመሆኑ ይህን ስያሜ አግኝቷል።



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሰ/ት/ቤቶች ማ/መ ማኅበረ ቅዱሳን በልማት ተቋማት አስተዳደር በመጽሔት ዝግጅት ክፍል የሚታተም ትምህርታዊ መጽሔት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ

፳፱ኛ ዓመት ቁጥር ፫
ኅዳር ፳፻፲፩ ዓ.ም.

# ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ም/ዋና አዘጋጅ፡-
*ዲያቆን አሻግሬ አምጤ*

አድራሻ፡- የካ ክፍለ ከተማ
*ወረዳ 01/02 የቤት ቍጥር 521/522*
*+251- 911361580*

ከፍተኛ ሪፖርተር፡-
*ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን*

የገጽ መልክእ ባለሞያና ጸሐፊ፡-
*ገነት ታደሰ*

አሳታሚበማኅበረ ቅዱሳን ልማት ተቋማት አስተዳደር
*አ.አ አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06*

የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ፡-
**+251-118-124222**
***ፖ. ሣ. ቍ.80078***
***magazine@eotcmk.org***

የማኅበረ ቅዱሳን ሕዝብ ግንኙነት
***+251-962 17 17 17***

የልማት ተቋማት ሽያጭና ስርጭት መምሪያ
***0111 54 04 84/24 61 84/944 25 90 14***

የገበያ ጥናት አገልግሎት መምሪያ
***0111266549/942 38 17 91/944 25 90 26***

## ማውጫ

**መልእክት ዘማኅበረ ቅዱሳን**
ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ዘመኑን ለዋጀ አገልግሎት................ ፪

**ዐውደ ስብከት**
ንስሓ የገነት በር..................................................፬

**ትምህርተ ሃይማኖት**
"ጽዮንን ባሰብናት ጊዜ አለቀስን" (መዝ. ፻፴፮፥፩) ...............፯

**ዐብይ ጉዳይ**
አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ለሐዋርያዊ አገልግሎትና ለማኅበራዊ አንድነት..................................................፲

**ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ**
አርአያነት ተግቶ በመሥራት...................................... ፲፬

**እናስተዋውቃችሁ**
ርእሰ አድባራት ደብረ ኮሪራ ቅድስት ማርያም..................... ፲፯

**የነገዋ ቤተ ክርስቲያን**
እግዚአብሔርን የሚያስወድስ፣ ሰውንም የሚቀድስ አገልግሎት.....፳

**ኪነ ጥበብ**
በአንድ ላይ ስንጓዝ ከዓይኔ ተሠወረ ...........................፳፫

**የጥያቄዎቻችሁ መልስ** .........................................፳፮

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ።*

# ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ዘመኑን ለዋጀ አገልግሎት

በየዓመቱ በጥቅምት ወር የሚካሄደው አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሐዋርያዊ አገልግሎትን ለማጠናከር፣ አስተዳደርንና አሠራርን ለማዘመን አቅጣጫ ያስቀምጣል። ጉባኤ መደረጉ መልካም ቢሆንም መደረግ ስላለበት ብቻ መፈጸም እንደሌለበት ተረድቶ ለውጥ የሚያመጣ ሥራ ለመሥራት በሚገባ ታስቦበት ሊዘጋጅ ይገባል። ቤተ ክርስቲያን ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት እንድትሰጥ አሳብ ማቅረብ ብቻ ሳይሆን የታሰበውና የታቀደው ተግባራዊ እንዲሆን የድርጊት መርሐ ግብር አውጥቶ መሥራት ይጠበቅበታል። የተሠራውን ካልተሠራው ለይቶ ባልተፈጸመው ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ አሳብ ማቅረብ ይኖርበታል።

ካህናትና ምእመናን እጅና ጓንት ሆነው መሥራት የሚኖርባቸውም "ዓመታዊው ጉባኤያችን የጉባኤውን ሪፖርት አንብበንና ሰምተን የምንለያይበት ብቻ ሳይሆን የጋራ የሆነ ዕቅድ የምናወጣበትና የምንወያይበት ስብሰባ መሆን ይኖርበታል። ስለሆነም ከቤተ ክርስቲያኒቱ ማእከላዊ አስተዳደር ጀምሮ ከየአህጉረ ስብከቱ የሚቀርበውን ሪፖርት በማድመጥ አንዱ ከሌላው ልምድ የሚቀስምበት፣ እያንዳንዱ ተግባር የሚገመገምበት በጉባኤው የተገኙ ልምዶች ተቀምረው ተቋማዊ ቅርፅ ይዘው የቤተ ክርስቲያኒቱ ተጨባጭ ሁኔታ የሚታወቅበት ጉባኤ" በመሆኑ ነው (ዐዋጅ ነጋሪ መጽሔት፣፳፻፲፩)። ጉባኤውን በሠመረ፣ በሰከነና በተረጋጋ መንፈስ ማካሄድ ለሐዋርያዊ አገልግሎትና ለተቸገሩት ለመድረስ የሚኖረው ጠቀሜታ ብዙ ነው። የአሳብ ፍጭት በማድረግ ለዘመኑ ትውልድ የሚመጥን ዕቅድ ማዘጋጀት የሚቻለው ካህናትና ምእመናን ኅብረት ፈጥረው በመተባበር በአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤው የመከሩት ተግባራዊ ሲሆን ነው።

በአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የቀረበ አሳብ በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ተመክሮበት በተግባር ላይ የሚውል በመሆኑ ካህናትና ምእመናን ተማምነውና ተባብረው መሥራት ይጠበቅባቸዋል። የጉባኤው ተግባርና ኃላፊነት ተሰብስቦ ሪፖርት አንብቦ ከመበተን የላቀ፣ የነገውን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እውን ለማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ነው። ከጠቅላይ ቤተ ክህነት እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ድረስ የተፈጸመውን ተግባር በመገምገም ለሚመጣው ዘመን መሠራት የሚኖርበትን ያቅዳል። "እያንዳንዱ ተግባር የሚገመገምበት፣ በጉባኤው የተገኙ ልምዶች ተቀምረው ተቋማዊ ቅርፅ የሚይዙበት" የሚለው ትኩረት የሚያስፈልገው ነጥብ ነው። የተሠራውን መገምገም፣ የተጣመመውን ከተስተካከለው፣ የጎደለውን ሙሉ ከሆነው ለመለየት ያግዛል። ያልተሠራውን ለመሥራት፣ የተሠራውን አጠናክሮ ለመቀጠል ይጠቅማል። ሥራን በአግባቡ ለመፈጠም የተጣለበትን ኃላፊነት መረዳት ቀዳሚው ተግባር ነው። የአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ተሳታፊዎች ተግባርና ኃላፊነታቸውን በሚገባ ከተረዱ ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት ለመስጠት ቆርጠው ይነሣሉ። ቅዱስ ሲኖዶስ የሚያስተላልፈውን ውሳኔ ለመፈጸም በቅንነት ይሰለፋሉ።

በአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚሰጠው አገልግሎት ሰማያዊ ዋጋ የሚያስገኝ፣ ለተቸገሩት በመስጠትና ጉዳት የደረሰባቸውን በመደገፍ ውስጣዊ ሰላም የሚገኝበት ነው። በካህናትና በምእመናን አንድነት የሚፈጸመው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ዘመኑን የዋጀ እና ሚዛኑን የጠበቀ የሚሆነው የተሰጣቸውን ኃላፊነት ተረድተው በመሥራት ነው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ርስት ነጥቃ ትውልድን እንዳሳደደች፣ ሰዎች እንዲሞቱና አካባቢያቸውን ለቀው እንዲሄዱ ተባባሪ እንደሆነች ተደርጎ የሚነገረውን የሐሰት ትርክት ማስተካከል የሚቻለው ካህናትና ምእመናን በመተባበር ትክክለኛውን የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ያልተረዱት እንዲረዱት፣ በዓላማ የሚያጠፉትም ውሸታቸው እንዲጋለጥ ሲያደርጉ ነው።

ለጥፋት የተሰለፉ አካላት ምክንያት እየፈለጉ ክርስቲያኖችን ከዋሉበት እንዳያድሩ፣ ካደሩበትም እንዳይውሉ ሲያደርጓቸው የችግሩን ጥልቀት በመረዳት ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላትና የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ማስገንዘብ የሚቻለው በእንደዚህ ዓይነት ጉባኤዎች በመወያየት ነው። ታላላቅ ጉዳዮችን አንሥቶ መወያየት ብቻ ሳይሆን ለውይይት የቀረቡ ነጥቦች ወደ ተግባር እንዲቀየሩ ሳይታክቱ መሥራት ካልተቻለ ወጣቱ ትውልድ በአባቶቹ ላይ ያለው መተማመን ይቀንሳል። ለቤተ ክርስቲያኑና ለአገሩ ማበርከት የሚገባውን ሳይወጣ ይቀራል። ተግባራችን ሁሉ "በመንፈስ የሚመላለሱ፣ የሥጋንም ምኞት የማይፈጽሙ" በማለት ሐዋርያው የመሰከረላቸውን መምሰል የሚገባውም ለዚህ ነው (ገላ.፭፣፲፮)። ክርስቲያኖች በአገር ላይ የሚደርስ መከራ ሳያስቅቃቸው ትውልድን ለመታደግ የሚሠሩትም ቀደምቶቻቸውን አርአያ አድርገው ነው።

በሐዋርያት ሥራ እንደተገለጠው ቅዱሳን ሐዋርያት ጳውሎስና በርናባስ በአሕዛብ መካከል ገብተው ሲያስተምሩ ቤተ ክርስቲያንን የሚያዳክም፣ የምእመናንን አንድነት የሚከፋፍል ችግር ገጥሟቸው ነበር። የተፈጠረው ችግር የተፈታው ለአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ መካሄድ መነሻ በሆነው የሐዋርያት ጉባኤ ነው። ጉባኤው ውሳኔ ከማስተላለፉ አስቀድሞ የችግሩን ጥልቀት ብቻ ሳይሆን የአሕዛብን የኑሮ ዘይቤና ባህል ተረድቶ ማድረግ ያለባቸውን ከማይኖርባቸው በመለየት አቅማቸውን ያገናዘበ ውሳኔ አስተላለፈ። ውሳኔውም "አሁንም ወደ እግዚአብሔር በተመለሱ አሕዛብ ላይ ሥርዓት አታክብዱ እላችኋለሁ። ነገር ግን ለጣዖት ከሚሠዋው፣ ከዝሙት፣ ሞቶ የተገኘውንና ደም ከመብላት እንዲርቁ፣ ለራሳቸው የሚጠሉትንም በወንድሞቻቸው ላይ እንዳያደርጉ እዘዙዋቸው" የሚል ነው(ሐዋ.፲፭፣፲፱-፳)።

ከአሕዛብ ወደ ክርስትና የገቡት ክርስቲያኖችም ችግራቸውን ከግምት ውስጥ ያስገባና አቅማቸውን ያገናዘበ ውሳኔ ስለተላለፈላቸው ውሳኔውን በጸጋ ተቀበሉት። በዘመናችን የሚያስፈልገውም በሰዎች ላይ ሸክም ላለማክበድ በጥንቃቄ መወሰን ነው። ውሳኔ ሲወሰንና ትእዛዝ ሲተላለፍ የሰዎችን አቅም ያገናዘበ፣ ለገጠማቸው ችግር ተግባራዊ ምላሽ የሚሰጥ ከሆነ ሰዎች ችግሩን ረስተውና ከእግዚአብሔር የሚያገኙትን ጸጋ አስበው የሚጠበቅባቸውን ያደርጋሉ።

አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የቤተ ክርስቲያን ንብረት ለአገልጋዮቿ መተዳደሪያ፣ ለሐዋርያዊ ተግባር ማከናወኛና ለነዳያን መርጃ እንዲውል ከማድረግ በተጨማሪ በአገልጋዮች መካከል አለመግባባት ሲፈጠር በፍትሕ መንፈሳዊ እንዲታይ የሚያደርግ መሆኑ ተግባርና ኃላፊነቱ ከባድ መሆኑን ያስገነዝባል (ቃለ ዐዋዲ፣ ፲፱፻፺፩፣፩፤ ቃለ ዐዋዲ፣ ፳፻፱፣፪)። "ከየአህጉረ ስብከቱ የሚቀርቡ ዘገባዎች ተደምጠው በጉባኤው ውይይት የሚካሄድባቸው ሲሆን በስብከተ ወንጌል መስፋፋት፣ በልማትና በመልካም አስተዳደር የታዩ ውጤቶችና ተሞክሮዎች በሚገባ ተደራጅተውና ተቀምረው የጥቅምት የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ይመክርባቸዋል" የሚለው ዐዋጅ ነጋሪ መጽሔት በጉባኤው ከሚቀርበው ሪፖርት አጀንዳ ተቀርጾ ውይይት የሚደረግበት መሆኑን ቢጠቁምም ተግባራዊ ሲሆን ባለመታየቱ ሪፖርቱ እንደተጠናቀቀ ጊዜ ወስዶ በሚገባ ተወያይቶ ለቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ግብዓት የሚሆን አጀንዳ ማቅረብ ይገባል (ዐዋጅ ነጋሪ መጽሔት፣ቅጽ፣፱፣ገ.፲፮)። በየዓመቱ የሚነገረው የአቋም መግለጫ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ እንዲያርፍበት ከማድረግ በተጨማሪ የተላለፈው ውሳኔ በተግባር መፈጸም አለመፈጸሙን መከታተል ይገባል እንላለን።✤

# ንስሓ የገነት በር

ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "በዚያ ወራትም ሰዎች ወደ እርሱ መጥተው ጲላጦስ ደማቸውን ከመሥዋዕታቸው ጋር ስለ ቀላቀለው ስለ ገሊላ ሰዎች ነገሩት። ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው። ይህቺ መከራ ስለ አገኘቻቸው እነዚህ ገሊላውያን ከገሊላ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ተለይተው ኃጢአተኞች የሆኑ ይመስሏችኋልን? አይደለም፤ እላችኋለሁ እናንተም ንስሓ ካልገባችሁ ሁላችሁ እንደ እነርሱ ትጠፋላችሁ" በማለት ተናግሯል (ሉቃ. ፲፫፥፩-፭) ። እንዲህ ብሎ የተናገረበት ምክንያት የንስሓን አስፈላጊነት ለማስተማር ነው ።

ኃጢቾአተኛ የመሰሏቸውን ሁሉ ሊከስሱ ወደ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይዘዋቸው በሄዱ ጊዜ የተከሰሱት ሰዎች ፈጽሙት ያሉትን ኃጢአት እነርሱም ስለሚሠሩት ኃጢአተኞች በመሆናቸው ዘለዓለማዊ ሞት እንደሚጠብቃቸው ነግሯቸዋል። ከሚጠብቃቸው ሞት ሊድኑ የሚችሉበት ብቸኛው መድኃኒት ንስሓ መሆኑን አስረግጦ ነግሯቸዋል። ይህንና ቤተ ክርስቲያን ዕለት ዕለት በጥልቀት የምታስተምረውን ትምህርት መሠረት በማድረግ ስለ ንስሓ ምንነትና አስፈላጊነት በጥቂቱ ለመዳሰስ እንሞክራለን።

**ሀ. ንስሓ፡-** ነስሐ ተጸጸተ ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን መጸጸት፣ መመለስ፣ ማንባት፣ አላበጀሁም ብሎ በንስሓ አባት ፊት ኃጢአትን በመናገር ዳግም ኃጢአት ላለመሥራት መጸየፍ ማለት ነው። ንስሓ መጸጸት፣ መመለስ፣ በፈጸሙት መጥፎ ድርጊት ማልቀስ፣ ፊት የሠሩትን ሥራ ላለመድገም መወሰን ማለት ነው።

ንስሓ እግዚአብሔር ከእርሱ የራቁትን ወደ እርሱ የሚጠራበት፣ አምላካዊ ድምፅ የሚሰማበት የገነት መግቢያ በር ነው። በመጽሐፈ መነኰሳት "በከመ ይጼውኦሙ ክርስቶስ ለእሊአሁ ኀበ ንስሓ፣ ከማሁ ሰይጣንኒ ለእለ ይትኤዘዙ ሎቱ ያርኅቆሙ እምኔሃ፡- ክርስቶስ የእርሱ የሆኑትን ወደ ንስሓ እንደሚጠራቸው ሰይጣንም የሚታዘዙለትን ከንስሓ ያርቃቸዋል" (አረጋዊ መንፈሳዊ ድርሳን ፳፱) ተብሎ ተጽፏል። ሰይጣን ኃጢአት አሠርቶ ከቤተ ክርስቲያን አስወጥቶ ከእግዚአብሔር ያራቃቸውን ክርስቶስ ደግሞ ወደ እርሱ የሚያቀርባቸው በንስሓ ነውና ንስሓ ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት የድኅነት በር ነው።

**ለ. የንስሓ አስፈላጊነት፡-** ለሰው ልጅ በሕይወቱ ከሚያስፈልጉት አምላካዊ ስጦታዎች መካከል አንዱ ንስሓ ነው። አስፈላጊነቱን በተመለከተ የሚነሡ ነጥቦችን እንደሚከተለው እንመለከታን።

### ፩. ከነፍስ ሞት ታድናለች

የነፍስ ሞት ጥንቱንም የመጣው ዛሬም የሚመጣው በኃጢአት ምክንያት ስለሆነ ከዚህ በኃጢአት ምክንያት ከመጣው ሞት የሚዳነው ደግሞ በንስሓ ነው። ይህንንም አረጋዊ መንፈሳዊ "ንስሓሰ እመ ሕይወት ይእቲ፣ ብፁዕ ውእቱ ዘይትወለድ እምኔሃ እስመ ኢይመውት፤ ንስሓ የሕይወት መገኛ ናት፤ አይሞትምና ከእርሷ የሚወለድ ንዑድ ክቡር ነው" (አረጋዊ መንፈሳዊ ድርሳን ፳፱) በማለት ይናገራል።

ሞት የኃጢአት ውጤት መሆኑን መፍቀሬ ጥበብ ሰሎሞን "በሕይወታችሁ ስሕተት ለሞት አትቅኑ፤ በእጃችሁም ሥራ ጥፋትን አታምጡ። እግዚአብሔር ሞትን አልፈጠረምና፤ የሕያዋንም ጥፋት ደስ አያሰኘውምና። ነዋሪ ይሆን ዘንድ ፍጥረቱን ፈጥሮአልና፣ የዓለም መፈጠርም ለድኅነት ነውና፣ በእነርሱም ዘንድ የጥፋት መርዝ አልነበረምና፣ ለሲኦልም በምድር ላይ ግዛት አልነበረውምና። ጽድቅ አትሞትምና። ክፉዎች ግን በእጃቸውና በቃላቸው ጠሩት ባልንጀራም አስመሰሉት። በእርሱም ጠፉ። የእርሱ ወገን መሆን ይገባቸዋልና ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን አደረጉ" በማለት አስተምሯል (ጥበ. ፩፥፲፪-፲፮)።

ከዚህ ምንባብ የምንረዳው ሞት ከጥንት ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ የኃጢአት ውጤት መሆኑን ነው። ሰው ለሞት ሳይፈጠር ግን ሕግ በማፍረሱ ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ ተፈረደበት። ከላይም እንደ ተጠቀሰው መፍቀሬ ጥበብ ሰሎሞን ይህ ዓይነት ሞት ሰዎች በኃጢአታቸው ምክንያት የመጣባቸው እንደሆነ ያስረዳናል። ከዚህ በኃጢአት ምክንያት ከመጣው ሞት ነፍስ የሚዳነው ደግሞ በንስሓ ነው። በመጽሐፈ ሲራክም እንዲህ የሚል ኃይለ ቃል እናገኛለን። "ኃጢአት ሠርቼ ፍዳ አልተቀበልሁም አትበል እግዚአብሔር ብዙ ዘመን ይታገሣልና። ስለ ኃጢአትህ ንስሓ መግባትን አትፍራ የእግዚአብሔር ምሕረቱ ብዙ ነው ኃጢአቴንም ይቅር ይለኛል እያልህ በኃጢአት ላይ ኃጢአትን አትጨምር። ምሕረትም መቅሰፍትም ከእርሱ ዘንድ ይመጣልና፤ መቅሰፍቱም በኃጢአተኛ ሰው ላይ ይወርዳል" ስለዚህ ንስሓ መግባት ከሞት ያድናል አለመግባት ደግሞ ለሞት ይዳርጋልና ፈጥኖ ንስሓ መግባት ያስፈልጋል(ሲራ.፭፥፬-፯)።

ባለራእዩ ዮሐንስ "ነገር ግን አንተን የምነቅፍበት ነገር አለኝ፤ የቀድሞ ፍቅርህን ትተሃልና። ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ፣ እንግዲህ ንስሓ ግባ፤ ያለዚያ ንስሓ ባትገባ የቀድሞ ሥራህንም ባትሠራ ፈጥኜ እመጣብሃለሁ፤ መቅረዝህንም ከቦታዋ አነሣታለሁ" በማለት ከሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት አለቆች መካከል አንዱ ለሆነው ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን አለቃ መንፈስ ቅዱስ እየነገረው በጻፈው ራእዩ ላይ ያስረዳናል (ራእ. ፪፥፬-፭)። እመጣብሃለሁ ማለት በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስን፣ በርደተ መቃብር ላይ ርደተ ገሃነምን እፈርድብሃለሁ። ስለዚህ ከሞት የምትድንበትን ንስሓ ገንዘብ አድርግ እያለ በማስጠንቀቂያ መልኩ ያስቀምጣል።

ነቢየ እግዚአብሔር ሕዝቅኤል "አንተም የሰው ልጅ ሆይ የእስራኤልን ቤት እናንተ በደላችንና ኃጢአታችን በላያችን አሉ፤ እኛም ሰልስለንባቸዋል፤ እንዴትስ በሕይወት እንኖራለን ብላችሁ ተናግራችኋል በላቸው። እኔ ሕያው ነኝና ኃጢአተኛው ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት ይኖር ዘንድ እንጂ ኃጢአተኛው ይሞት ዘንድ አልፈቅድም ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ የእስራኤል ቤት ሆይ ተመለሱ፤ ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ፤ ስለምንስ ትሞታላችሁ በላቸው" (ሕዝ. ፴፫፥፲-፲፩) በማለት ከእግዚአብሔር ያገኘውን መልእክት እንደጻፈልን ንስሓ ጥንት ይሠሩት ከነበረው ክፉ ሥራ ወደ መልካም ሥራ በመመለስና በጥንቱ ክፉ ሥራ በመጸጸት ከተቃጣብን ሞት ለመዳን መዘጋጀት መሆኑን ያስገነዝበናል።

አረጋዊ መንፈሳዊም "ለሊሃ ይእቲ ርጢነ መድኃኒት ዘጠቢብ ዐቃቤ ሥራይ ሰማያዊ፤ ወኵሉ ዘይወድያ በቍስሊሁ የሐዩ በጊዜሃ፤ ሕምዘ ሞት ወሕንቃቄ ወተፈርዝዞ ሀሎ በእደ ሰይጣን፤ ርጢነ ሕይወት ወገቢረ ንስሓ ሀሎ በእደ እግዚአብሔር፤ ብልህ ባለመድኃኒት ክርስቶስ ያዘጋጃት በጎ መድኃኒት እርሷ ናት፤ ከቍስሉ ያገባት ሁሉ ፈጥኖ ይድናል፤ የሞት መርዝ፣ መቀማጠል፣ መደላደል ትዕቢት በሰይጣን እጅ አለ፤ የሚያድን መድኃኒት ንስሓ መግባት በእግዚአብሔር እጅ አለ" በማለት ያስረዳል (አረጋዊ መንፈሳዊ፣ ድርሳን ፳፱)።

ይህ ሁሉ የሚያስረዳን ንስሓ ለሰው ሁሉ መዳኛ መሆኗን ነው። የነነዌ ሰዎች የዮናስን ስብከት ሰምተው ከክፉ ሥራቸው ቢመለሱ፣ ከትንሹ እስከ ትልቁ ድረስ በአንድነት ፍጹም የሆነ ንስሓ ቢገቡ እግዚአብሔር ያመጣባቸው ከነበረው ሞት አዳናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ "እግዚአብሔርም ከክፉ መንገዳቸው እንደተመለሱ ሥራቸውን አየ፤ እግዚአብሔርም ያደርግባቸው ዘንድ ከተናገረው ክፉ ነገር ተመለሰ፤ አላደረገባቸውምም" ተብሎ የእነርሱን መመለስ የተመለከተው እግዚአብሔር ያመጣባቸው ከነበረው ሞት እንዳዳናቸው ተጽፎ እናገኛለን (ዮና.፫፥፲)። ስለዚህ ሰዎች ከኃጢአት ተመልሰው ንስሓ ሲገቡ በሥጋ ከድንገተኛ መቅሰፍት በነፍስ ደግሞ ወደ ሲኦል ከመውረድ፣ ከሞተ ነፍስ ይድናሉ።

### ፪. መንፈሳዊ ዕድገትን ታስገኛለች

መንፈሳዊ ዕድገት መለኪያውም መንፈሳዊ ተግባር ነው። መንፈሳዊ ዕድገትን በመንፈሳዊ ዐይን የሚመለከቱት፣ ዐይነ ልቡና ሲበራ የሚረዱት ነው እንጂ እንደ ሥጋዊ ዕድገት በዐይነ ሥጋ የሚታይ አይደለም። የሚገኘውም በረጅም ጊዜ ተጋድሎ ነው። የረጅም ጊዜ ተጋድሎ ከሚከናወንባቸው በርካታ አቅጣጫዎች መካከል አንዱ የንስሓ ሕይወት ነው። በንስሓ ሕይወት መንፈሳዊ ዕድገትን ገንዘብ ማድረግ እንደሚቻል አረጋዊ መንፈሳዊ "ወማይ ይእቲ እንተ ተሐፅን ዘርዐ ቅዱስ፡- ንስሓ ልዩ ዘርን የምታሳድግ መስኖ (ውኃ) ናት" በማለት ያስረዳል (አረጋዊ መንፈሳዊ ድርሳን ፳፱)። ንስሓን እንዲሁ ውኃ ብቻ ብሎ አልገለጻትም። የምስኖ ውኃ ነው ያላት። የመስኖ ውኃ ከምንጩ ተስቦ ለተለየ አገልግሎት ማለትም አትክልተኞች ስበው የሚወስዱት ነው። አትክልተኞች ተፈጥሯዊ የሆነው ዝናም እስኪወርድ ሳይጠብቁ ከምንጩ እየሳቡ አትክልታቸውን ያጠጣሉ። ንስሓም በአትክልተኛ የተመሰለው መምህረ ንስሓ ለንስሓ ልጆቹ ዕለት ዕለት እያጠጣ የሚያሳድግበት ምግበ ነፍስ ነው።

ነቢዩ ዳዊት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ፣ ዕለት ዕለት ሕገ እግዚአብሔርን እያሰበ የሚኖርን ሰው ከወንዝ ዳር በተተከለ ተክል መስሎ "የእግዚአብሔር ሕግ ብቻ ፈቃዱ የሆነ ሕጉንም በቀንና በሌሊት የሚያስብ እርሱም በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደ ተተከለች፣ ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል፤ የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል" በማለት ይገልጻዋል (መዝ.፩፥፪-፫)። የእግዚአብሔር ሕግ ደግሞ ሰው ሁሉ ንስሓ ገብቶ ከፈጣሪ ጋር ታርቆ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ለምልሞ መንፈሳዊ ዕድገትን ገንዘብ አድርጎ እንዲኖር ነው። ስለዚህ በንስሓ ሕይወት የሚመላለስ ሰው ነቢዩ ዳዊትም፣ አረጋዊ መንፈሳዊም እንደ ገለጹት መንፈሳዊ ዕድገትን ገንዘብ አድርጎ ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ ዛፍ ሆኖ ይኖራል።

በሥጋዊ ሕይወታችን የተመጣጠነ ምግብ ስንመገብ አካላዊ ጥንካሬያችን የተሻለ ይሆናል፤ ለማንኛውም በሽታ ተጋላጭ አንሆንም። አካላዊ ዕድገታችንም እንዲሁ በተገቢው መልኩ ይከናወናል። እንደዚሁም መንፈሳዊ ምግብ ስንመገብ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ጠንካራ፣ ጠላት ዲያብሎስ ለሚያመጣው የኃጢአት በሽታ የማንጋለጥ፣ መንፈሳዊ ዕድገታችን ሂደቱን ጠብቆ እየጨመረ የሚሄድ እንሆናለን። ምክንያቱም ዕለት ዕለት መንፈሳዊውን ምግብ የእግዚአብሔርን ቃል እየተመገብን ንስሓ እየገባን ስንኖር መንፈሳዊው ምግብ ሕይወታችንን ያጠነክረዋል፤ ንስሓው ደግሞ አረጋዊ መንፈሳዊ "እሳት ይእቲ እንተ ታውዒ ክርዳደ፤ ክርዳደ ኃጢአትን የምታቃጥል እሳት ናት" (ድርሳን ፳፱) በማለት እንደገለጻት የሠራነውን ኃጢአታችንን ትደመስስልናለች።

ተክሉን ዕድገቱን በተገቢው መንገድ አጠናቅቆ መልካሙን ፍሬ ያፈራ ዘንድ በየዕለቱ ውኃ ያጠጡታል። መንፈሳዊው ተክል ደግሞ የሰው ልጅ ነው፤ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ "እነሆ ምሳር በዛፎች ግንድ ላይ ሊወድቅ ተቃጥቶአልና መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል፤ ወደ እሳትም ይጣላል" (ማቴ. ፫፥፲) በማለት እንደ ገለጸው በዛፍ የተመሰለው የሰው ልጅ ነው። የሰው ልጅ መልካም የሆነውን ምግባር ካልሠራ፣ በንስሓ ሕይወት ካልተመላለሰ ይቆረጣል፤ እሳቱ ወደ ማይጠፋበት ትሉ ወደማያንቀላፋበት ገሃነመ እሳት ይጣላል። እንዲህ እንዳይሆን ማለትም መንፈሳዊውን ዕድገት በአግባቡ እንዲያከናውንና መልካሙን ፍሬ እንዲያፈራ አሳዳጊው የሆነችውን የንስሓን ሕይወት ገንዘብ ሊያደርግ ይገባል።

## ፫. ንጹሕ ታደርጋለች

በኃጢአት የጎሰቆለውና የቆሸሸው ማንነታችን ከእድፈ ኃጢአት የሚነጻው በንስሓ ሕይወት መሆኑን ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት "በጭንቀቴ ደክሜያለሁ፤ ሌሊቱን ሁሉ አልጋዬን አጥባለሁ፤ በዕንባዬም መኝታዬን አርሳለሁ" (መዝ. ፶፥፯) በማለት ገልጾታል፡፡ በሠራነው ኃጢአት በፍጹም ተጸጽተን፣ መሪር ዕንባ እያነባን እግዚአብሔርን ስንለምነው ከኃጢአታችን ያነጻናል፡፡ ነቢዩ በሌላኛው መዝሙሩ "ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ ከኃጢአቴም አንጻኝ" (መዝ. ፶፥፪) በማለት እንደገለጸው ከኃጢአታችን ነጽተን በአርባ በሰማንያ ቀን የተቀበልነውን ንጹሕ ማንነት ጠብቀን ለመኖር የንስሓ ሕይወት አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ንስሓ ከኃጢአት እንደምታነጻን ሲገልጽ "ወብፁዕሰ ዘኮነ ኬንያ ለነፍሱ እለሰ ይላህዉ ወይቴክዙ ወይበክዩ በእንተ ኃጢአቶሙ ከመ ሶበ ማየ ዮርዳኖስ ይትሐፀቡ ወይነጽሑ እምኃጢአቶሙ ይትኃደግ ሎሙ ኃጢአቶሙ እምከመ ተመይጡ እለ ተመይጡ ወነስሑ ይድኅኑ፡- ለነፍሱ ጠቢብ የሆነ ሰው ንዑድ ክቡር ነው፤ ስለኃጢአታቸው የሚያዝኑ፣ የሚተክዙና የሚያለቅሱ በዮርዳኖስ ውኃ እንደሚጠመቁ ከኃጢአታቸው ይነጻሉ፤ ንስሓ የገቡና የተመለሱ እንደ ተመለሱ ኃጢአታቸው ይቅር ይባልላቸዋል፤ ይድናሉም" በማለት ያስረዳል (ጾመ ድጓ ገጽ ፳፪) ፡፡

መንፈሳዊ ዕድገት መለኪያውም መንፈሳዊ ተግባር ነው። መንፈሳዊ ዕድገትን በመንፈሳዊ ዐይን የሚመለከቱት፣ ዐይነ ልቡና ሲበራ የሚረዱት ነው እንጂ እንደ ሥጋዊ ዕድገት በዐይነ ሥጋ የሚታይ አይደለም። የሚገኘውም በረጅም ጊዜ ተጋድሎ ነው።

አረጋዊ መንፈሳዊም በኃጢአት ምክንያት ከመቆሸሽ በንስሓ ንጹሕ መሆን እንደሚቻል "ባሕር ይእቲ እንተ ተሐጽቦሙ ለርሱሓን፣ ወምንህብ ይእቲ እንተ ታጸሪ ኵሎ ዘዝሕለ፤ ያደፉትን የምታነጻቸው ባሕር ናት፤ በኃጢአት የዛገውን ሁሉ የምታጸራ ወናፍ ናት" በማለት ያስረዳል (አረጋዊ መንፈሳዊ ድርሳን ፳፱)፡፡ ስለዚህ በጭቃና በሌላም ቆሻሻ ያደፈውን ሰውነታችንን ታጥበን እንደምናነጻው ሁሉ በኃጢአት የተዳደፈ ማንነታችንን ደግሞ በንስሓ ታጥበን እናነጻዋለን፡፡

## ፬. ነጻነትን ታሰጣለች

ኃጢአት የሚሠራ ሰው የኃጢአት ባሪያ ይሆናል፡፡ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ "ለኃጢአት ትገዙ በነበረበት ጊዜ ከጽድቅ ነጻ ነበራችሁና፡፡ በዚያን ጊዜ ሥራችሁም እነሆ ዛሬ ታፍሩበታላችሁ፤ መጨረሻው ሞት ነውና፡፡ ዛሬ ግን ከኃጢአት ነጻ ወጣችሁ፤ ራሳችሁንም ለጽድቅ አስገዛችሁ፤ ለቅድስናም ፍሬን አፈራችሁ፤ ፍጻሜውም የዘለዓለም ሕይወት ነው፡፡የኃጢአት ትርፏ ሞት ነውና" (ሮሜ ፮፥፳-፳፫) በማለት ሰው የኃጢአት ተገዥ በሆነ ቍጥር ትርፉ ሞት እንደሆነ ከዚህ ከኃጢአት ባርነት ነጻ የሚወጣው ደግሞ በንስሓ መሆኑን በማያሻማ መልኩ አስረድቶናል፡፡

ዛሬም ማንኛውም ሰው ኃጢአት ሲሠራ የኃጢአት ባሪያ ይሆናል፡፡ ከኃጢአት ባርነት ነጻ የሚወጣው ደግሞ ንስሓ ሲገባ ብቻ ነው፡፡ አረጋዊ መንፈሳዊ የሰው ልጅ በንስሓ ከኃጢአት ባርነት ነጻ እንደሚወጣ ሲገልጽ "ወለፂዉዋን እለ ተዔወዉ በእከየ ዚአሁ መድኃኒቶሙ ይእቲ፤ ወግዕዛኖሙ፤ ለአግብርት እለ በፈቃዶሙ አግነዩ ሎቱ ግዕዛኖሙ ይእቲ፣ ታገብኦሙ ኀበ ርስቶሙ፤ በእርሱ ኃጢአት ለተማረኩ መድኃኒታቸው ናት፤ ለሰይጣን ከመገዛት ነጻ የምታደርጋቸው ናት፤ ወደው ለሰይጣን የተገዙ ሰዎችን ነጻ የምታወጣቸው ናት፤ ወደ መንግሥተ ሰማያት ታገባቸዋለች" (አረጋዊ መንፈሳዊ ድርሳን ፳፱) በማለት ያስረዳል፡፡

በአጠቃላይ ንስሓ በድንገተኛ መቅሰፍት ከሚመጣ ሞት በዋናነት ግን ከሞተ ነፍስ ታድናለች፤ ነጻነትን ታጎናጽፋለች፤ በመንፈሳዊ ሕይወት የሚፈለገውን ዕድገት ታስገኛለች፡፡ ንስሓ መንፈሳዊ ንጽሕናን የምታለብስ አስቀድመን እንደጠቀስነው ሰዎችን ለመክሰስ ወደ ክርስቶስ የሄዱትን ሰዎች የመለሰላቸው "እናንተም ንስሓ ካልገባችሁ ትጠፋላችሁ" በማለት ነበር፡፡ በሃይማኖት ጸንተን፣ በጎ ምግባር ሠርተን ንስሓ ገብተን ዕለት ዕለት ሥጋውን በልተን፣ ደሙን ጠጥተን፣ ከክርስቶስ ጋር ያለንን አንድነት አጽንተን፣ እንድንኖር በመጨረሻም የመንግሥቱ ወራሾች፣ የስሙ ቀዳሾች እንዲያደርገን የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የድንግል ማርያም አማላጅነት፣ የቅዱሳን ሁሉ ተራዳኢነት ይለየን፡፡ አሜን!!✥

# “ጽዮንን ባሰብናት ጊዜ አለቀስን”

**(መዝ. ፻፴፮÷፩)**

*መ/ር ግሩም ወ/መድኅን*

ይህን ቃል የተናገረው ነቢዩ ዳዊት ሲሆን የተናገረበት ምክንያትም ፭ኤል ከ፮፻፭ እስከ ፭፻፷፪ ዓ.ዓ ድረስ ነግሦ በነበረው በናቡከደነጾር ተማርከው ወደ ባቢሎን በወረዱ ጊዜ ጊዜው ሳይደርስ እንደ ደረሰ ሆኖ በመንፈስ ቅዱስ ተገልጾለት የዘመረው መዝሙር ነው፡፡ ትሩፋን ተማርከው ባቢሎን ሲወርዱ ዘመድ ከዘመዱ፣ ወንድ ልጅ ካባቱ፣ ሴት ልጅ ከእናቷ ሳይለያዩ በአንድነት ወርደዋል፤ ከባቢሎን ወንዝ ሲደርሱ በሚለያዩበት ጊዜ እንግዲህ ወዲህ መሰንቆ ለባሪያ ምኑ ነው? የቆመውን መቁረጥ የወደቀውን መፍለጥ ነው እንጂ ብለው በገናቸውን ከአሃያ ዛፍ ላይ ሰቅለው ተላቅሰው ተለያይተዋልና “በባቢሎን ወንዞች አጠገብ በዚያ ተቀምጠን ጽዮንን ባሰብናት ጊዜ አለቀስን” ብሎ በትሩፋን ተገብቶ ዘመረ፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ባቢሎን እየተባለች የተጠራችው ሀገር የዛሬዋ ኢራቅ ስትሆን በዕብራይስጥ “ባቤል” ይሏታል፡፡ ትርጒሙም ድብልቅልቅ ማለት ነው፡፡ ይኸውም ጥንት ሰናኦር ይባል የነበረው አካባቢ ነው፡፡ ከጥፋት ወኃ በኋላ ሰዎች ስማቸውን ለማስጠራት ትልቅ ግንብ መሥራት ጀመሩ እግዚአብሔርን ሳይፈሩ ይህንን ስላደረጉ እግዚአብሔር ቋንቋቸውን ደባለቀባቸው፤ ከዚያም በምድር ላይ በተናቸው፡፡ ያም ቦታ ባቢሎን ተባለ፡፡ “ኑ እንውረድ አንዱ የሌላውን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው፡፡ እግዚአብሔርም ቋንቋቸውን ለያየ ከዚያም በምድር ፊት ሁሉ በተናቸው፤ ከዚያም በኋላ ከተማዪቱንና ግንቡን መሥራት ተዉ፡፡ ስለዚህ ስሟ ባቢሎን ተባለ እግዚአብሔር ከዚያ የምድርን ቋንቋ ሁሉ ደባልቋና ከዚያም እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ፊት እነርሱን በትኗቸዋል” እንዲል (ዘፍ. ፲፩÷፯-፱)፡፡

ባቢሎን በጣኦት አምልኮ ከታወቁ ሀገራት አንዷ ናት፡፡ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ቢገሥጻትም በእንቢተኝነት ጸንታ ቆይታለች፡፡ በእርሷ የሚኖሩ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከባቢሎን ግብር ማለትም መለያየት፣ ጣኦት አምልኮ፣ በደልና ርኵሰት እንዲወጡ እግዚአብሔር በነቢያቱ እያደረ ብዙ ተናግሯል፡፡ “ከባቢሎን መካከል ሽሹ፤ እያንዳዳችሁ ነፍሳችሁን አድኑ፤ በበደሏ አትጥፉ፤ የእግዚአብሔር በቀል ጊዜ ነውና እርሱም ብድራቷን ይከፍታልና ባቢሎን በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ምድርን ሁሉ ያሰከረች የወርቅ ጽዋ ነበረች፡፡ አሕዛብ ከጠጇ ጠጥተዋል፤ ስለዚህም አሕዛብ ተንገዳግደዋል” (ኤር.፶፩÷፯-፰)፡፡ በነቢያት ጸሎትና መሥዋዕት የማትፈወስ መሆኑንም ሲገልጽ “ባቢሎንን ፈወስናት እርሷ ግን አልተፈወሰችም ፍርዷ እስከ ሰማይ ደርሷልና እስከ ከዋክብትም ድረስ ከፍ ከፍ ብሏልና እንተዋት ሁላችንም ወደ ሀገራችን እንሂድ” (ኤር.፶፩÷፱-፲)፡፡ እግዚአብሔር የተዋት እኛም ልንተዋት የምትገባ ዓለም ባቢሎን የማትፈወስ በቋንቋ፣ በኀሳና በሰፈር የተደበላለቀችና መለያየት የበዛባት ዓለም ስለሆነች እንድንተዋትና ጥለናት እንድንወጣ ነቢዩ ይመክረናል፡፡

## ጽዮን

ጽዮን የቃሉ ትርጒም አምባ መጠጊያ መሸሸጊያ ማለት ሲሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ተደጋግመው ከተጠሩ (ከተጻፉ) ቃላት አንዱ ነው፡፡ እንደየ አገባቡም ብዙ ዓይነት ትርጒም ይዞ፣ ለብዙ ነገርም ተሰጥቶ እናገኘዋለን፡፡ ይህ ዓይነቱ ጉዳይ በመጽሐፍ ቅዱስ የተለመደ ነው፡፡ ለምሳሌ ቆመ (መቆም) የሚለውን ቃል ስንመለከት የተነሣንበት ቃል በልዩ ልዩ ዐውድ ሲገባ ልዩ ልዩ ትርጒም ሊኖረው እንደሚችል በመጽሐፍ ቅዱስ የተለመደ መሆኑን ያሳየናል፡፡

**፩. በእግር ቀጥ ብሎ መቆም፡-** በመጽሐፍ ቅዱስ “እርሱም የሰው ልጅ ሆይ በእግርህ ቁም እኔም እናገርሃለሁ አለኝ” (መዝ.፪÷፩) ፤ “ሊቃነ ካህናትና ሸንጎውንም ሁሉ እንዲመጡ አዘዘ፡፡ ጳውሎስንም አምጥቶ በፊታቸው አቆመው” የሚሉ ምንባባትን እናገኛለን (ዮሐ. ፳፪÷፴)፡፡ እነዚህን በእግርህ ቁም፣ በፊታቸው አቆመው የሚሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስንመለከት በተፈጥሮ እግር መቆምን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

**፪.ማማለድ፡-** መቆም ማማለድን ያመለክታል “አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት ገና ቆሞ ነበር” (ዘፍ. ፲፰÷፳፪) ፤ “ስለ ሕዝብ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል” (ዳን.፲፪÷፩) ፤ “እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ” (ሉቃ፩÷፲፱) ፤ “የተመረጠው ሙሴ በመቅሠፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ ባጠፋቸው ነበር” (መዝ.፻፭÷፳፫) ፤ “መሴና ሳሙኤል በፊቴ ቢቆሙ ልቤ ወደዚህ ሕዝብ አያዘነብልም ” (ኤር.፲፭÷፩) እነዚህን እና ሌሎችንም ቃላት ብንመለከት መቆም ማማለድ መሆኑን አብርሃም ለሰዶምና ለገሞራ፣ ቅዱስ ሚካኤልና ቅዱስ ገብርኤል ለሰው ልጆች ሁሉ፣ ሙሴ ከግብፅ ባርነት ተላቀው በጉዞ ለነበሩ እስራኤል፣ ሙሴ እና ሳሙኤልም የሕዝቡ አማላጆች መሆናቸውን፣ ይህም ማለት መቆም ማማለድ መሆኑን ያስረዳል፡፡

**፫.መገለጥ፡-** “እግዚአብሔር በአማልክት ማኅበር ቆመ” (መዝ.፹፩÷፩) ፤ “በቆመ ጊዜ ምድርም ትናወጣለች (ዕብ.፫÷፯)፤ “የእግዚአብሔር መልአክ ሊቋቋመው በመንገድ ላይ ቆመ (ዘፍ.፳፪÷፳፪) ፤ የሚሉትን ቃላት ስንመለከት መቆም መገለጥ ተብሎ እንደሚተረጐም እንረዳለን፡፡

**፬. መጽናት፡-** “ቃል ኪዳኔን ካንተ ጋር አቆማለሁ” ዘፍ ፤ “ንቁ በሃማኖት ቁሙ” (፩ኛቆሮ.፲፮÷፲፫)፤ “በእምነታችሁ ቆማችኋል” (፪ኛቆሮ.፩÷፳፬) ፤ “በሰላም ወንጌል በመዘጋጀት

እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ" (ኤፌ.፮፥፲፭) እነዚህን ቃላት ስንመለከት ደግሞ መቆም መጽናት ተብሎ እንደሚተረጐም እንረዳለን። ጽዮን የሚለው ቃል ብዙ ትርጉም ያለው፣ ብዙ ምሥጢራትንም ያዘለ፣ ብዙዎችም ለቃሉ የተለያየ ትርጉም የሰጡት፣ ይልቁንም ከኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውጪ ያሉ አካላት እንደሚፈልጉት እየተረጐሙ ምእመናንን ለማሳሳት ከሚጠቀሙባቸውና ከሚያጣምሟቸው ቃላት መካከል አንዱ ነው።

ጽዮን የሚለው ቃል በፈርጅ በፈርጁ እንደ አገባቡ ሲተረጐም በመጽሐፍ ቅዱስ ለስድስት ነገር ተሰጥቶ እናገኘዋለን። ይህንን በሚገባ ማወቅ በራስ ስሜት፣ አረዳድና የዕውቀት ደረጃ ከመነዳትና ከተጻፈበት ዐውድና አሳብ ወጥቶ በመተርጐም ድምዳሜ (ውሳኔ) ላይ ከመድረስና ከመሳት ይጠብቃል። ቅዱስ ጴጥሮስ በመልእክቱ እንደራሳችን አሳብ ከተጻፈበት ዐውድ ወጥተን እንዳንተረጉም "ይህንን በመጀመሪያ ዕወቁ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን ቅዱሳን ሰዎች ከእግዚአብሔር ተልከው በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው ተናገሩት እንጂ" በማለት ያዘናል (፪ኛጴጥ.፩፥፳-፳፩)።

ሐዋርያው በዚሁ መልእክቱ "በእነዚያ ዘንድ ለማስተዋል የሚያስቸግር ነገር አለ፤ ያልተማሩትና የማይጸኑትም ሰዎች ሌሎችን መጻሕፍት እንደሚያጣምሙ እነዚህን ዳግም ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ። ወንድሞቻችን ሆይ እናንተስ አስቀድማችሁ ይህንን ዕወቁ፤ በማይጠቅም ትምህርትም እንዳትስቱና ከጸናችሁበት እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ" በማለት አንድን ጉዳይ በገዛ ፈቃዳችን መተርጐም እንደማይገባ ያስረዳናል (፪ኛጴጥ. ፫፥፲፮-፲፰)።

**፩. ጽዮን የዳዊት መናገሻ፡-** በመጽሐፍ "ነገር ግን ዳዊትም አንባዪቱን ጽዮንን ያዘ እርሷም የዳዊት ከተማ ናት" ተብሎ እንደተጻፈ (፪ኛሳሙ. ፭፥፯)። ንጉሥ ዳዊት በኬብሮን ነግሦ ሳለ የእስራኤል ሽማግሌዎች ወደ እርሱ መጥተው በእነርሱ ላይ እንዲነግሥ ለመኑት። እርሱም የዳዊት ሰዎችም በሀገሩ ወደሚኖሩት እያቡሴውያን ሂዶ ብዙ ተቃውሞዎችንም አልፎ አንባዪቱን ጽዮንን ተቈጣጠረ፤ ከተማውንም ከተቈጣጠረ በኋላ በአቢዳራ ቤት ይኖር የነበረውን ለአቢዳራ ቤት በረከት የሆነውን ታቦት ወደ ከተማው አስመጣ "ለንጉሥ ዳዊት እግዚአብሔር የአቢዳራን ቤትና የነበረውን ሁሉ ስለ እግዚአብሔር ታቦት ባረከ ብለው ነገሩት ዳዊትም ሄዶ የእግዚአብሔርን ታቦት ከአቢዳራ ቤት ወደ ዳዊት ከተማ በደስታ አመጣት›› እንዲል (፪ኛሳሙ.፮፥፲፪)።

እስራኤላውያን የበረከት የረድኤት ከተማ ከሆነችው ከጽዮን በናቡከደነጾር ተማርከው ወደ ባቢሎን ሲወርዱ ስለ ሀገራቸው ስለጽዮን ዘምረዋል። "በባቢሎን ወንዞች አጠገብ በዚያ ተቀምጠን ጽዮንን ባሰብናት ጊዜ አለቀስን በአኻያ ዛፎቿ ላይ መሰንቆቻችንን (በገናዎቻችንን) ሰቀልን የማረኩን በዚያ የዝማሬ ቃል ጠይቀውናልና የወሰዱንም የጽዮንን ዝማሬ ዘምሩ አሉን የእግዚአብሔርን ዝማሬ በባዕድ ሀገር እንዴት እንዘምራለን? ኢየሩሳሌም ሆይ ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ" (መዝ.፻፴፮፥፭) በማለት ለመዘመርም በገና ለመደርደርም እግዚአብሔርን ለማሰብም ሀገር፣ ነፃነት እንደሚያስፈልግ እነዚህ ሁሉ በምርኮ በስደት እንደማያምሩ ማመስገኛ አጸዳቸው የቃል ኪዳን ቦታቸው ጽዮንን ጥለው በመሄዳቸው የዘመሩት ዝማሬ ነው። ስለዚህ በመጀመሪያው አገባብ ጽዮን የዳዊት መናገሻ የዳዊት ከተማ ማለት ነው።

**፪. ጽዮን ሕዝበ እስራኤል፡-** በጽዮን በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች " ጽዮን" ይባላሉ " ተንሥእ እግዚኦ ወተሣሃላ ለጽዮን- አቤቱ ተነሥ ጽዮንንም ይቅር በላት" (መዝ.፻፩፥፲፫) የሚለው ቃል በጽዮን የሚኖሩትን ሲል ነው። በማደሪያው አዳሪውን በአዳሪው ደግሞ ማደሪያውን ወክሎ መጥራት የመጽሐፍ ልማድ ነውና በቦታዋ ሰዎቹን መናገሩ ነው፡ ተራራዋን ከተማዋን ነው እንዳንል እርሷ ኃጢአት ልትሠራ አትችልም። በመጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ያሉ ተመሳሳይ አገላለጾች አሉ። ለምሳሌ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር፤ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" (መዝ.፷፯፥፴፩) በዚህ የመጽሐፍ ክፍል ኢትዮጵያ የተባሉ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ሰዎች ወይም ኢትዮጵያውያን ናቸው። ተራራው ኮረብታው ወንዙ ሸለቆው ቆላው ደጋው ነው እንዳንል መሬት የሚዘረጋ እጅ የላትም።

ሌሎችንም ተጨማሪ መረጃዎችን ለመጥቀስ "አቤቱ በውዴታህ ጽዮንን አሰማምራት" (መዝ. ፶፥፲፰) ፤ "እግዚአብሔር ጽዮንን ያድናታል(መዝ ፷፰፥፴፭) "ጽዮን በፍርድ ከርሷም የሚመለሱ በጽድቅ ይድናሉ (ኢሳ.፩፥፳፯) ፤ "ጽዮን እግዚአብሔር ትቶኛል ጌታም ረስቶኛል አለች"(ኢሳ.፵፱፥፲፬)፤ " አንቺ ከባቢሎን ቤት ልጅ ገራር የምትኖሪ ጽዮን ሆይ ኮብልዪ"(ት.ዘካ. ፪፥፯)፤ "ጽዮን ሆይ አትፍሪ እጆችሽም አይዛሉ" (ሶፎ.፫፥፲፮) እነዚህን የመሳሰሉትን አገላለጾች ስንለመከት ጽዮን የሚለው ቃል በጽዮን ለሚኖሩ ሰዎች ተሰጥቶ እናገኘዋለን።

**፫. ጽዮን ጽርሐ አርያም፡-** ከሰባቱ ሰማያት አንዱ ጽርሐ አርያም ጽዮን ተብሎ ተጠርቷል። "ዘምሩ ለእግዚአብሔር ዘየኀድር ውስተ ጽዮን ወንግርዎሙ ለአሕዛብ ምግባሮ፤ በጽዮን ለሚያድር ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤ ለአሕዛብም ሥራውን ንገሩ" (መዝ.፱፥፲፩) በዓለም ምሉዕ የሆነው እግዚአብሔር በጽርሐ አርያም በኪሩቤል ዙፋን ተቀምጦ ከሱራፌልም ምስጋናን ዕጣንን እንደሚቀበል አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ እንዲህ ብሏል። "ጽርሐ አርያም ማኅፈዱ፤ መካነ ትጉሃን አጸዱ፤ ካህናተ ሰማይ ቅውማን በዐውዱ፤ አክሊላቲሆሙ ያወርዱ ቅድመ መንበሩ እንዘ ይሰግዱ፤ ይርእዱ ወኢይዘብጠሙ ሶበ ይበርቅ ነዱ፤ ጽርሐ አርያም አዳራሹ ነው፤ የትጉሃን መላእክት ቦታ መመስገኛው ነው፤ ካህናተ ሰማይ በዙሪያው ቆመዋል፤ እሳታዊ ከሆነው ባሕርየ መለኮቱ የሚወጣው ነበልባል እንዳያቃጥላቸው በመንበሩ ፊት ሲሰግዱ አክሊላቸውን ያወርዳሉ›› በማለት የተናገረላት የክርስቶስ የመመስገኛ አጸዱ ጽርሐ አርያም መሆኗን ነቢዩ ዳዊት ጽዮን ብሎ የጠራት እርሷ እንደሆነች በግልጽ መረዳት ይቻላል። (መጽሐፈ ሰዓታት)

**ለዚህም ተጨማሪ ማሳያ ለመጥቀስ ያህል፡-** "ከክብሩ ውበት

ከጽዮን እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል" (መዝ. ፵፱፥፪) "እግዚአብሔር በጽዮን ያድራል (ኢዩ.፫፥፪)፤ "እኔ በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን የምቀመጥ አምላካችሁ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ታውቃላችሁ (ኢዩ. ፫፥፲፯)።

**፬. ጽዮን መንግሥተ ሰማያት፡-** በመጨረሻው እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ያዘጋጃት አዲሲቷ ሰማይና አዲሲቷ ምድር ዓይን ያላያት፣ ጆሮም ያልሰማት፣ በሰው ልቡናም ያልታሰበች፣ እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ያዘጋጃት የከበረች ሰማያዊት ኢየሩሳሌም መንግሥተ ሰማያት ጽዮን ተብላ ተጠርታለች። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን ምእመናን በላከው መልእክቱ ምእመናን ወደ ማን መሰብሰብ ወዴት መድረስ እንዳለብን ሲገልጽ እንዲህ ይላል። "እናንተ ግን የሕያው እግዚአብሔር ከተማ ወደምትሆን ወደ ጽዮን ተራራ በሰማያት ወደ አለችው ኢየሩሳሌም ደስ ብሎአቸው ወደሚኖሩ አእላፍ መላእክት ደርሳችኋል። ስማቸው በሰማያት ወደተጻፉ ወደ ማኅበረ በኵርም ሁሉን ወደሚገዛ ወደ እግዚአብሔር ወደ ፍጹማን ጻድቃን ነፍሳት የሐዲስ ኪዳን መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ ከአቤል ደም ይልቅ የሚሻለው? ወደሚናገር ወደ ተረጨው ደም ደርሳችኋል" እንዲል። (ዕብ.፲፪፥፳፪-፳፬) ትጉሃን መላእክት የበኵራት ማኅበር ሰማዕታት ቅዱሳን ጻድቃን የሚሰበሰቡባት ሰማያዊት ኢየሩሳሌምን ጽዮን በማለት ጠርቷታል።

**፭. ጽዮን ድንግል ማርያም፡-** በዚህ አግባብ ደግሞ ጽዮን ለእመቤታችን ተሰጥቶ እናገኘዋለን። መዝሙረኛው ዳዊት "እምነ ጽዮን ይብል ሰብእ ወብእሲ ተወልደ በውስቴታ ወውእቱ ልዑል ሣረራ፤ ሰው ሁሉ እናታችን ጽዮን ይላል በውስጧ ሰው ተወልዷልና እርሱ ራሱም ልዑል መሠረታት" (መዝ.፹፮፥፭) በማለት ዘምሯል። በዚህ ዐውድ ነቢዩ ጽዮን በማለት የጠራት ተራራዋን ወይም ሌላውን አይደለም። ሰው የሆነ ራሱንም የሰው ልጅ እያለ የጠራ፣ በእኛ ባሕርይ የተወለደውን ክርስቶስን የወለደች ድንግል ማርያምን ነው። እግዚአብሔር ለተዋሕዶ የመረጣት፣ ከሦስቱ አካላት አንዱን አካል እግዚአብሔር ወልድን በኅቱም ድንግልና ፀንሳ በኅቱም ድንግልና የወለደች ድንግል ማርያምን ሰው ሁሉ እናታችን ይላታል። ስለዚህም "ነኪር ነገሩ በእንቲአኪ ሀገረ እግዚአብሔር፤ የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ ስለ አንቺ የተነገረው ነገር ድንቅ ነው" ተብላ ተገልጻለች (መዝ.፹፮፥፫)። እመቤታችን እግዚአብሔር ስላንቺ የተናገረው ድንቅ ነው ማለት ያለዘር ያለሩካቤ መውለዷን መናገር ነው በእመቤታችን ያመኑ በቤተ ክርስቲያን የተወለዱትን እመቤታችን እናታችን እግዚአብሔር ወልድን አባታችን ይላሉ።

ጌታ ከእመቤታችን በሥጋ ተወለደ" በማለት ሙሉ መዝሙሩን ለእመቤታችን ሰጥተው ተርጕመውታል "እስመ ኀረያ እግዚአብሔር ለጽዮን ወአብደራ ከመ ትኩኖ ማኅደሮ ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም ዝየ አኀድር እስመ ኀረይክዋ፤ እግዚአብሔር ጽዮንን መርጧታልና ማደሪያው ትሆነው ዘንድ ወድዷታልና ይህቺ ለዘለዓለም ማደሪያዬ ናት መርጫታለሁና በዚች አድራለሁ" (መዝ.፻፴፩፥፲፫) እግዚአብሔር ጽዮንን መርጧታልና ሲል" ጽዮን ብሎ የጠራት እመቤታችንን ቅድስት ድንግል ማርያምን ነው። የእመቤታችን ለእናትነት ለአምላክ ማደሪያነት መመረጥ በሰው ዘንድ ሳይሆን በራሱ በእግዚአብሔር ዘንድ መሆኑንና ለእናትነት ያዘጋጃት፣ ዘለዓለሙ ማደሪያው እንድትሆን የለያት፣ ያከበራትና ከአዳማዊ በደል የጠበቃት እርሱ እግዚአብሔር እንደሆነ እርሷም አምባ መጠጊያ የድሆች መሸሸጊያ ጽዮን ድንግል ማሪያም መሆኗን የሚያስረዳ ነው። "ለዘለዓለም ማደሪያዬ ናት" ሲል ለዘለዓለም ወላዲተ አምላክ ስትባል የምትኖር ስለሆነ፣ ከዚህ በተጨማሪም ከእርሷ የነሣው ሥጋ ለዘለዓለም የሚኖር ስለሆነ ነው።

ነቢዩ ኢሳይያስ "የአስጨናቂዎችሽም ልጆች እየተንቀጠቀጡ ወደ አንቺ ይመጣሉ የናቁሽ ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ የእስራኤል ቅዱስ የእግዚአብሔር ከተማ ጽዮን ተብለሽም ትጠሪያለሽ" (ኢሳ.፷፥፲፬) ብሎ ተናግሯል። በዚህ ዐውድ ጽዮን ብሎ የጠራት ድንግል ማርያምን ነው። ተራራው ነው እንዳንል ለተራራ እግር የላትም "ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ" ሲልም በክብር በባለሟልነት በጌታ ቀኝ ለምትቆመው ለእመቤታችን እንደሚሰግዱ ሲያስረዳ ነው።

**፮. ጽዮን ታቦተ ጽዮን፡-** ታቦቱ የቃል ኪዳኑ ታቦት፣ የሕጉ ታቦት፣ የምስክሩ ታቦት፣ የኪዳኑ ታቦት፣ የእግዚአብሔር ታቦት፣ የእስራኤል አምላክ ታቦት፣ የአምላካችን ታቦት፣ እየተባለ በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ቦታ ተጽፎ እናገኘዋለን። መጽሐፍ ቅዱስ ታቦተ ጽዮን እያለ የሚጠራት የሙሴ ጽላት ስሟ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ቦታ ላይ ብቻ ተጽፎ እናገኘዋለን። ይህም፡- "ቤተ መቅደሳችን እንደ ፈረሰ፤ መሠዊያችን እንደ ተሰባበረ አታዩምን? ግናያቱ (ምስጋናው) እንደጠፋ፣ ምስጋናችን እንደቀረ፣ ዘመራ ዘውዳችን እንደወደቀ፣ ተድላ ደስታችን እንደጠፋ፣ የሕጋችን ማደሪያ ታቦተ ጽዮን እንደተማረከች፣ ንዋየ ቅድሳታችን እንዳደፈ፣ ምልክታችን እንደቀረ፣ ጌቶቻችን እንደጎሰቆሉ፣ ካህናቱ እንደተቃጠሉ፣ ሌዋውያን እንደተማረኩ፣ ሴቶች ልጆቻችን እንደሞቱ፣ ሚስቶቻችንን እንደቀሙን፣ መምህሮቻችን እንደተጎተቱ፣ ሚስቶቻችንና ጎልማሶቻችን እንደተገዙ፣ ወንዶች ልጆቻችን እንደተቀሙ፣ ዐርበኞቻችን እንደደከሙ አታዩምን? ከዚህ ሁሉ የሚበልጥ ጽዮን እንደወጣች ቀረች። ከርሷም ንዋየ ቅድሳቷ ተማርኮ ሄደ በጠላቶቻችን በባቢሎናውያን እጅ ወደቅን" እንዲል (ዕዝ. ሱቱ.፱፥፳-፳፫)።

እነ ዕዝራን ታስቆጫቸው የነበረችዋ ታቦተ ጽዮን ዛሬ በኢትዮጵያውያን ምድር ላይ ትገኛለች። ወደ ኢትዮጵያም የገባችው በንግሥት ሳባ ዘመን በልጇ በንጉሥ ምንሊክ ነው። ታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ ስትገባ ዐሥራ ፲፪ የእስራኤል በኵራትና ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት ሌዋውያን አብረው መጥተዋል። ታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ የገባችበት ኅዳር ሃያ አንድ ቀን መከበር ጀመረ። ሌዋውያን ካህናት የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ የሆነችውን ታቦተ ጽዮንን በዓመት በዓመት በሚያከብሩበት ጊዜ ለጽዮን የሚገባውን መዝሙር በከበሮና በጸናጽል እያሸበሸቡ በዓሉን ከፍ ባለ ሥነ ሥርዓት ያከብሩ ነበር። በጽዮንም ፊት በየመዓርጋቸው ቆመው "እግትዋ ለጽዮን ወሕቀፍዋ፤ ጽዮንን ክበቧት በዙሪዋም ተመላለሱ" በሚለው የዳዊት መዝሙር ያመሰግኑ ነበር።✥

# አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ለሐዋርያዊ አገልግሎትና ለማኅበራዊ አንድነት

## ተግባርና ኃላፊነት

**ዲ/ን አሻግሬ አምጤ**

አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በወንጌል አምናችሁ ንስሓ ግቡ የሚለውን አምላካዊ ቃል ለአመኑት አድርሶ በእምነት ለማጽናት፣ ያላመኑትን አስተምሮ ከሥላሴ ልጅነትን እንዲያገኙ በመወያየት ለቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ አጀንዳ የሚያቀርብ፣ አፅራረ ቤተ ክርስቲያንን እንዴት ማስታገስ እንደሚቻልና ብልሹ አሠራርን ከቤተ ክርስቲያን ነቅሎ ለመጣል በሚቻልበት ጉዳይ ላይ ተወያይቶ አቅጣጫ የሚያስቀምጥ የክርስቲያኖች ጉባኤ ነው:: ጉባኤ የሚካሄደው የተከናወነውን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ገምግሞ፣ በምእመናንና በቤተ ክርስቲያን ላይ እየደረሰ ያለውን ችግር በጥልቀት መርምሮ የመፍትሔ አቅጣጫ ለማስቀመጥ ነው:: ይህ ብቻ ሳይሆን የተሳሳተውን አስተካክሎ፣ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበትን ለማስቀጠል አሳብ አቅርቦ በቃል የተነገረው በተግባር እንዲፈጸም የሚሠራ በካህናትና በምእመናት ኅብረት የሚቋቋም ነው:: ካህናት ስንል ከፓትርያርኩ ጀምሮ በየደረጃው የሚያገለግሉ አባቶችንና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን የሚያካትት መሆኑን ማስገንዘብ እንፈልጋለን::

አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ያልተሠራው እንዲሠራ፣ ተጀምሮ የቀረው እንዲጠናቀቅ የተዘነጋው እንዲታሰብ የሚመከርበት ጉባኤ ሲሆን ጠንካራው ለደከሙት ልምድ በማካፈል መንፈሳዊ ቅንዓት አድሮባቸው ለአገልግሎት እንዲነሣሡ የሚደረግበት ነው:: ከዚህ በተጨማሪም አቅም ያለው የሌለውን፣ ሀብት ያለው ችግረኛውን ማገዝ እንዲችል አቅጣጫ የሚቀመጥበት ነው:: ያላመኑትን በወንጌል እመኑ ከማለት በተጨማሪ አምነው ከሥላሴ ልጅነትን ተቀብለው የሚኖሩት በዐበይትና ንኡሳን ኃጣውእ ሲሰነካከሉ ደግሞ ንስሓ ግቡ በማለት የሚያገኙትን ሰማያዊ ጸጋ አሳይቶ እንዳይፈሩ በማበረታታት፣ እንዳይደፋፈሩ በመገሠጽ ወደ ትክክለኛው መስመር መግቢያ መንገዱን የሚያመለክት፣ ክርስቲያኖች እንዴት ራሳቸውንም፣ ሌሎችንም ማገልገል እንደሚገባቸው ብልሃት የሚጠቁመው አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ነው:: የሚፈቀደውን ከሚከለከለው፣ የሚደረገውን ከማይደረገው ለመለየት ሐዋርያት በ፶ ዓመተ ምሕረት የፈጸሙትን አብነት አድርጎ የሚሠራ፣ ለአገልጋዮች የሚሆነውንና ለሐዋርያዊ አገልግሎት የሚውለውን በመለየት እንዳይደበላለቅ አሳብ የሚያቀርብ፣ የተቸገሩትን ለመርዳት የሚያስፈልገውን መከታተልና መቈጣጠር ከአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ እንደሚጠበቅ ቃለ ዐዋዲው ያስገነዝባል::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በ፵ኛው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ባስተላለፉት አባታዊ ቡራኬ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን ተግባርና ኃላፊነት የገለጡት "በመጀመሪያው የሐዲስ ኪዳን ክፍለ ዘመን በኢየሩሳሌም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በስምንት ሺህ ማኅበረ ካህናት እና ምእመናን አባላት ለመጀመሪያ ጊዜ የተመሠረተው እና በዚያው ቅጽበት ወደ ሀገራችን ወደ ኢትዮጵያ የመጣው የክርስትና ሃይማኖት እና ማኅበራዊ አንድነት አስተዳደራዊ አቋሙን በማጠናከር የማኅበረ ካህናት ወምእመናን አንድነት መገለጫ የሆነው አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ለተገኘው ዘርፈ ብዙ በረከት ዋና ማእከል እና የቤተ ክርስቲያናችን የህልውናዋ ምሰሶ ሆኖ መኖሩ ግልጽ ነው" በማለት ነው::

በቅዱስነታቸው ቃለ በረከት ውስጥ ብዙ ቁም ነገሮች ተካትተዋል:: የመጀመሪያው ጉዳይ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን ከሐዋርያት የተቀበለችው ሳይበረዝና ሳይከለስ በቅብብሎሽ ከዘመናችን መድረሱን መግለጡ ነው:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምሮም ሆነ ማኅበራዊ አገልግሎት ከመላው ዓለም ቀድማ ከሐዋርያት በተቀበለችው ሃይማኖት የተቃኘ መሆኑን ማሳወቁ ነው:: ጉባኤው በካህናትና በምእመናን አንድነት የተመሠረተ መሆኑንም ያስገነዝባል:: ካህናትና ምእምናን እጅና ጓንት ሆነው ተባብረው ካልሠሩ ለቤተ ክርስቲያን ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት መስጠት አይቻልም:: በካህናትና በምእመናን አንድነት ተቋቁሞ አገልግሎት መስጠት እንደጀመረ ብዙም ሳይቆይ ወደ ሀገራችን ገብቶ የክርስትና ሃይማኖትንና ማኅበራዊ አንድነትን ተክሎ እንደኖረም ያስገነዝባል:: ይህ ጉዳይም በአገራችን ክርስትና እንዲስፋፋ ከማድረግ በተጨማሪ ክርስቲያናዊ ባህል ሥር እንዲሰድ ማድረጉም የታወቀ ነው:: በካህናትና ምእመናን አንድነት የተመሠረተው ሃይማኖትንና ክርስቲያናዊ ማኅበራዊ አንድነትን የፈጠረው አስተምህሮ የቤተ ክርስቲያን የህልውናዋ ምሰሶ በመሆኑ አገልግሎቷ ዘመኑን የዋጀ እንዲሆን ምሰሶውን ማጽናት ከአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አባላት ሁሉ የሚጠበቅ ከባድ ኃላፊነት ነው::

በየዓመቱ ለጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚዘጋጀው ዐዋጅ ነጋሪ የተሰኘው መጽሔት የአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን ተግባር የገለጠው "የቤተ ክርስቲያን የሥራ ውጤት በትውልደ ትውልድ ሲዘከር የሚኖረው አገልግሎቷ ከዘመን ዘመን እየተሻሻለ እና እየጠነከረ ዘመኑን በሚዋጅ መልኩ መቀጠል የሚገባው በመሆኑ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በዓመት ውስጥ የፈጸመችውን አገልግሎት የምትገመግምበት፣ በአዲሱ ዓመት መከናወን የሚገባቸውን ዋና ዋና ሥራዎች የምታቅድበት፣ በአህጉረ ስብከት መካከል የልምድ ልውውጥ የሚደረግበት ዓመታዊው ሰበካ አጠቃላይ መንፈሳዊ ጉባኤ ነው" በማለት ነው (፴ኛ ዓመት፣ ቁጥር ፲፪፣ ገ. ፲፯)::

ለሠላሳ አራተኛው አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የተዘጋጀው ዐዋጅ ነጋሪም "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ በሃይማኖታዊ፣ በመንፈሳዊና ማኅበራዊ ዘርፎች የምታከናውናቸው ዐበይት ተግባራት፣ የተመዘገቡ ውጤቶችና ያጋጠሙ ችግሮች እንዲሁም ላጋጠሙ ችግሮች የተሰጡ የመፍትሔ አሳቦችና የወደፊት ዕቅዶች በዓመት አንድ ጊዜ በሚካሄድበት አጠቃላይ የሰበካ ጉባኤ እየቀረቡ ከተመከረባቸውና የውሳኔ አሳብ ከቀረበባቸው በኋላ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ እንዲያርፍባቸው ይደረጋል" (ዐዋጅ ነጋሪ፣ ገ. ፲፯) ይላል።

## ጉባኤ የማድረጉ ዓላማ

በ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ተዘጋጅቶ በቅርቡ በተሻሻለው የተተካው ቃለ ዐዋዲ የአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የመካሄዱን ዓላማ "የኢትጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በካህናትና ምእመናን ኅብረት በሰበካ ጉባኤ እንድትደራጅ ቤተ ክርስቲያን በማኅበረ ካህናትና ምእመናን መደራጀቷ፣ በሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አስተዳደር መመራቷ ከጥንት ያለ እንጂ አዲስ አለመሆኑን ግብረ ሐዋርያትን መሠረት በማድረግ አመራሯና አስተዳደሯ በኢየሩሳሌም በተደረገው በሐዋርያት ጉባኤ ተሞክሮ እና ተወስኖ በተላለፈው ሕግና ሥርዓት ይመራና በማኅበረ ካህናቱ እና ምእመናኑ ጠቅላላ ጉባኤ በተመረጡ መንፈስ ቅዱስ ባደረባቸው ኃላፊዎች ሥራ አስፈጻሚነት ይካሄድ እንደነበር በመገንዘብ ሀብቷና ንብረቷ ከምእመናን በአስተዋጽዎ ተሰብስቦ ለአገልጋዮቿ መተዳደሪያ፣ ለሐዋርያዊ ሥራ ማስኬጃና ለችግረኞች መርጃ እንዲውል በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ውስጥ አለመግባባት ቢፈጠር በፍትሕ መንፈሳዊ ታይቶ እንዲወሰን" ማድረጉን ያስረዳል (ቃለ ዐዋዲ፣ ፲፱፻፺፩፣ ፩)።

የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በግብረ ሐዋርያት ተጽፎ የምናነበውን መነሻ አድርጎ ከጥንት ጀምሮ ሲሠራበት የኖረ እንጂ እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ አይደለም። ሐዋርያዊ አገልግሎቱ እንዲጠናከር የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ይወጣል ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከምእመናን የሚሰበሰበው ገንዘብ ለአገልጋዮች መተዳደሪያ፣ ለሐዋርያዊ አገልግሎት ማጠናከሪያ እና ለችግረኞች መርጃ እንዲውል፣ አለመግባባት ቢፈጠር በፍትሕ መንፈሳዊ ታይቶ ርትዕት የሆነ ፍትሕ እንዲሰጥ ያደርጋል። በቃለ ዐዋዲው የተጠቀሰው በትክክል ተግባራዊ ቢሆን ኖሮ ቤተ ክርስቲያን እንኳን በልጆቿ በኢአማንያን ዘንድም በጎ ተጽዕኖ ባሳደረች ነበር። በቃለ ዐዋዲው የተቀመጠው ወደ ጎን ተገፍቶ ካለ ሕግና ሥርዓት መሠራቱ ሐዋርያዊ አገልግሎቱ እንዲዳከም ምክንያት ሆኗል። ቤተ ክርስቲያን ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት ለመፈጸም የምትችለው ግን ለቤተ ክርስቲያን ገቢ የሚሆነው ገንዘብ በቃለ ዐዋዲው በተቀመጠው መሠረት አገልግሎት ላይ ሲውልና ካህናትና ምእመናን አንድነት ፈጥረው ሐዋርያዊ አገልግሎቱ የሚጠናከርበትን ተግባር ሲፈጽሙ ነው።

የአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ተሳታፊ ካህናትና ምእመናን "ባለፉት ፴ ዓመታት በየደረጃው ያሉ የቤተ ክርስቲያንን ሁለንተናዊ ተልእኮ ለማሟላት የቃለ ዐዋዲው ድንጋጌ በየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ከዓላማውና ከተግባሩ በመነጨ አንድነት ከላይ እስከታች ባለው የሥራ መዋቅር በመናበብ በርካታ ሥራዎችን አከናውነናል።ለወደ ፊቱም በወሬ የማይፈታ፣ ፈተናን የሚቋቋም ትውልድ በማነጽ ይህንኑ አንድነታችንን በማጠናከርና በማስተማር የቤተ ክርስቲያናችንን የህልውና አንድነት ክብርና ልዕልና ለማስጠበቅ መንጋውን የመከታተልና የመቈጣጠር ሥራ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በአርቆ አሳቢነት በመሥራት አደራችንን እንወጣለን። የቃለ ዐዋዲውም ሕግ በተጀመረው አግባብ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች ተተርጉሞ ለሀገር ውስጥና ለውጭው ዓለም በበቂ ሁኔታ እንዲሰራጭ እየጠየቅን ቅዱስ ሲኖዶስም የቃለ ዐዋዲው መመሪያ በውጭ ሀገራት ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ እንዲውል ጥብቅ መመሪያ እንዲሰጥ እንጠይቃለን" በማለት ያስተላለፉት መልእክት ተግባራዊ ከሆነ ቤተ ክርስቲያን ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት መስጠት ትችላለች።

## አሠራርን ለማዘመን ሕግና ደንቦችን ማሻሻል

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሰው ልጅ ሁሉ መንግሥተ ሰማያትን እንዲወርስ ከማድረግ በተጨማሪ አገር ሰላም ውላ እንድታድር፣ ማኅበራዊ አንድነት እንዲጸና፣ ካህናትና ምእመናን እጅና ጓንት ሆነው ማገልገል እንዳለባቸው ታስተምራለች። ፴፰ኛው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በማጠቃለያው "ቤተ ክርስቲያናችን አስተዳደሯን የምትመራበት ቃለ ዓዋዲ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ጊዜውንና ወቅቱን ባገናዘበ መልኩ እንዲሻሻል ቢደረግም አሁንም ሰፊ ክፍተት ያለው በመሆኑ ቃለ ዓዋዲውን ጨምሮ አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሕጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የሠራተኛ መተዳደሪያ ደንቦች በባለሙያዎች አስፈላጊው ጥናት እየተደረገ ለመልካም አስተዳደር ምቹ በሆነና ሊያሠራ በሚችል መልኩ በድጋሚ ማሻሻያ እንዲደረግባቸው እንጠይቃለን" በማለት ያወጣው የአቋም መግለጫ የጎደለው እንዲሞላ፣ የጠመመው እንዲቀና አሳብ ያቀረበበት ነው።

ከዚህ መግለጫ መረዳት የሚቻለው በወረቀት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ ብቻውን ለውጥ የማያመጣ መሆኑን ነው። ወረቀት ላይ የሚደረገው ማሻሻያ ተግባራዊ ሥራ ለመሥራት አቅጣጫ የሚጠቁም ነው። ለሥራ እንቅፋት የሆነውን ማስተካከል አስፈላጊ ቢሆንም በዚህ ብቻ መርካት የተከሠተን ችግር አይፈታውም። ቃለ ዐዋዲውንም ሆነ ሌሎችን ሕጎችና መመሪያዎች ለአስተዳደር ምቹ እንዲሆኑና ሊያሠሩ እንዲችሉ አድርጎ በማዘጋጀት በተግባር ላይ ማዋል የተፈጠረን ችግር ከሥሩ ለመንቀል ያግዛል። በችግር ጊዜ ቀድሞ መድረስና ሠርቶ ማሠራት ዘመኑ የሚጠይቀው ሐዋርያዊ ተግባር በመሆኑ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሲካሔድም ይህን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሊሆን ይገባዋል።

በያዝነው ዓመት በ፴ኛው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ማጠቃለያ "በየደረጃው የሚገኘውን የቤተ ክርስቲያቱን ሀብትና ገንዘብ ካለው የሰው ኃይል ጋር በማቀናጀት በቁጠባና በማብቃቃት በመጠቀም ብኩንነትን የሚጋብዙ አሠራሮችን በማስወገድ ገንዘብና የቤተ ክርስቲያን አስፈላጊነቱ በተለያዩ ጊዜያት በተካሄዱ ጉባኤያት

ተነሥተው መመሪያ የተሰጠባቸው ቢሆንም አሁንም አልፎ አልፎ ምርመራ በተደረገባቸው ቦታዎች በዚህ ዘርፍ ያለው ችግር አለመቀረፉን የሚያሳይ ሪፖርት በንባብ ተሰምቷል፡፡ስለሆነም አስተዳደራዊ ኃላፊነታችንን ከፍ በማድረግ የቤተ ክርስቲያንን ሀብት በቆጣቢነት ለመጠቀምና ውሳኔና መመሪያን በማክበር በባለአደራነት ተግባራዊ እናደርጋለን" የሚለው የዛሬ ሁለት ዓመት የተነገረው ለውጥ አለማሳየቱን የሚያስገነዝብ ነው፡፡

ቤተ ክርስቲያን ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት የምትሰጠው አሠራሯ ሲዘምን ነው፡፡ ለዚህም "የነገዪቱን ቤተ ክርስቲያን የሚረከቡና ዛሬም የቤተ ክርስቲያን ውበት የሆኑት የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶችን በመንከባከብ፣ በማስተማርና ከጠላት ወረራ እንዲጠበቁ በማድረግ ከአባቶች የተማሩትን ያልተበረዘ ንጹሕ ትምህርት በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናቱ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ሁሉ ለማስተማር ያሉትን ለማጠናከር ባልተቋቋሙባቸው አብያተ ክርስቲያናትም ለማቋቋም ቃል እንገባለን፡፡ ከዚህም ጋር በማኅበረ ቅዱሳን በኩል በየአህጉረ ስብከቱ በሚገኙ ወረዳዎችና አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ለልማት ሥራ የሚውል የገንዘብና ሙያዊ ድጋፍ መደረጉ ከየሪፖርቶቹ ማዳመጥ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ማኅበሩ ለቤተ ክርስቲያን የሚያደርገውን ድጋፍ ወደ ፊትም ማእከላዊ አሠራርን በጠበቀ መልኩ አጠናክሮ እንዲቀጥል ጉባኤው ያሳስባል" የሚለው አጠቃላይ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ተሳታፊዎች ያወጡት መግለጫ ማሳያ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መገናኛ ብዙኃን ጥቅምት ፲፰ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ቅዱስ ሲኖዶስ እየመከረበት ያለውን ጉዳይ "ምልዓተ ጉባኤው ፵ኛው የጠቅላላ መንበረ ፓትርያርክ ሰበካ ጉባኤ ባወጣው የአቋም መግለጫ ላይ ጥልቅ ውይይት በማድረግ ማስተካከያ ሊደረግባቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ እርማት በመስጠት በቃለ ጉባኤ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ፣ የቤተ ክርስቲያንን ጉዳዮች በውጭና በውስጥ በማለት በሁለት መንገድ የተመለከተው ቅዱስ ሲኖዶስ በሃይማኖታቸው ምክንያት ከቀያቸው ስለሚፈናቀሉና እየደረሰባቸው ላለው ሥቃይ እንዲሁም የመስቀልና የጥምቀት በዓል በሚከበርባቸው የቤተ ክርስቲያን ይዞታዎችን በተመለከተ በመወያየት ላይ እንደሚገኝ" መግለጡ ተገቢ ቢሆንም አዎንታዊ ምላሽ እስከሚገኝ ድረስ ከሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ጋር መሥራት፣ የችግሩን ጥልቀት ለመንግሥት ማስገንዘብ ይገባል፡፡

### ሰላም እስከሚሰፍን ሳይታክቱ መሥራት

የቤተ ክርስቲያን ተግባር ሰላም ማስፈን መሆኑ የተገለጠውም ዜጎች ውለው እንዲገቡ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲወርሱ ሰላም አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡ ሰላም እንዲሰፍን በካህናትና ምእመናን አንድነት የተቋቋመው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ከመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን አንሥቶ እየሠራ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ የቤተ ክርስቲያንን ይዞታ እየነጠቁና ምእመናንን ከመኖሪያቸው እያፈናቀሉ ሰላም እንደማይገኝ ለ፵ኛው ሰበካ

**ያላመኑትን በወንጌል እመኑ ከማለት በተጨማሪ አምነው ከሥላሴ ልጅነትን ተቀብለው የሚኖሩት በዐበይትና ንኡሳን ኃጣውእ ሲሰነካከሉ ደግሞ ንስሓ ግቡ በማለት የሚያገኙትን ሰማያዊ ጸጋ አሳይቶ እንዳይፈሩ በማበረታታት፣ እንዳይደፋፈሩ በመገሠጽ ወደ ትክክለኛው መስመር መግቢያ መንገዱን የሚያመለክት፣ ክርስቲያኖች እንዴት ራሳቸውንም፣ ሌሎችንም ማገልገል እንደሚገባቸው ብልሃት የሚጠቁመው አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ነው።**

መንፈሳዊ ጉባኤ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ "ቤተ ክርስቲያን በአየር የተንሳፈፈች ነገር ሳትሆን በማኅበረ አማንያን ልቡና ውስጥ ተጠልላ የምትገኝ መንፈሳዊት መንግሥተ እግዚአብሔር ናት፤ ይህም ባሕርይዋ ከአማንያን ህልውና ጋር ያቆራኛታል፤ አማንያንም ያለ ሀገር ህልውና ስለሌላቸው ቤተ ክርስቲያን በተከታዮቿ አማካኝነት ከሀገር ሰላም ጋር ትተሳሰራለች፣ ይህ ብቻም አይደለም፤ የዓለሙን ሰላምና ፍቅር አስተማሪ፣ ሰባኪና ተምሳሌት በመሆን የሰው ልጆችን ሁሉ የመጠበቅ ኃላፊነትም አለባት፤ ይህንም ስታደርግ እንደ እናትም፣ እንደ መምህርም፣ እንደ ሽማግሌም ማእከላዊት ሆና ሥራዋን ማከናወን እንዳለባት ይታወቃል፡፡ይሁንና ቤተ ክርስቲያናችን በአሁኑ ጊዜ በፈተና ተከባ፣ ልጆችዋም እርስ በእርስ እየተጣሉ እንደሚገኙ ዓለም ሁሉ የሚያውቀው ነው፡፡

እነዚህ ወገኖቻችን ቤተ ክርስቲያን ልጆቼ ብላ የተቀበለቻቸው፣ በልጅነት ያከበረቻቸውና ለእግዚአብሔር መንግሥት ዕጩ ያደረገቻቸው፣ በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠሩ ክቡራን ሰዎች ናቸው፤ ቤተ ክርስቲያን በዚህም በዚያም ያሉ ሁሉ ልጆቿ ናቸውና ስለእነርሱ ይገዳታል፤ ይሰማታል፤ ያሳስባታልም፤ በመሆኑም ብትችል መክራና አስተምራ፣ ገሥጻና ቀጥታ፣ ካልሆነም ልባዊ የሆነ ጸሎት ወደ እግዚአብሔር በማቅረብ ከእርስ በእርስ ግጭት ተላቀው በአንድነት፣ በሰላምና በፍቅር እንዲኖሩ በጸሎትና በምሕላ ፈጣሪን መማፀን አለባት፤ ይህን ስናደርግ የኖላዊነት ኃላፊነታችንን በአግባቡ እየተወጣን ነው ማለት እንችላለን፤ በመሆኑም ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያስተላልፈው ቀኖናዊ መልእክት ገዳማቱ፤ አድባራቱና አብያተ ክርስቲያናቱ በጸሎትና በምሕላ ተጠምደው ስለ ሕዝብ፣ ስለ ምእመናንና ስለሀገር ደኅንነት አጥብቀው ፈጣሪን እንዲማፀኑ በዚህ ጉባኤ ፊት አባታዊ መልእክታችንን እናስተላልፋለን" በማለት የተናገሩት ከካህናትና ምእመናን የሚጠበቅ ብዙ ነገር መኖሩን የሚያስገነዝብ ነው፡፡

"...እምነትንና ማንነትን መሠረት ያደረገ ጥፋት በቡራዩ፣ ይህን ተከትሎ በምሥራቅና ምዕራብ ወለጋ፣ በሻሸመኔ፣ በዝዋይ፣ በመተከል፣ በጉራ ፈርዳ፣ ምዕራብ አርሲ፣ በባሌ፣ በምዕራብ ሐረርጌ፣ በድሬዳዋ ተከታታይ ጭካኔ የተሞላበት ጭፍጨፋ በመፈጸሙ ቤተ ክርስቲያኗን አሳዝኗል፡፡ በወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሑመራ፣ ማይካድራ፣ ምዕራብ ጎንደር መተማ፣ ሰሜን ጎንደር ጭና አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ ማእከላዊ ጎንደር፣ በደቡብ ጎንደር ጨጨሆ መድኃኔዓለም፣ ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ዋግ ኽምራ፣ ራያና ኮረም፣ በጅማ፣ በሊሙ ኮሳ፣ በሊሙ ሰቃ ወረዳዎች፣ በሰሜን ሸዋ በአጣዬ፣ በሸዋ ሮቢት፣ በካራ ቆሬ፣ በማጀቴ አካባቢዎች አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል፡፡ የቤተ መቅደስ ካህናት ካህኑ ዘካርያስ በቤተ መቅደስ በተሠዋበት አምሳል በአገልግሎት እንዳሉ ታርደዋል፡፡

ምእመናንና ምእመናት በሀገራችን ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ጸታ ሳይለይ እመጫቶችን፣ ነፍሰ ጡሮችን፣ ቀኛና ግራ፣ ፊትና ኋላ፣ እሳትና ውኃ የማይለዩ ሕፃናት በአሠቃቂ ሁኔታ እንዲገደሉና ብዙዎች ሀብት ንብረታቸው ወድሞ ለስደት እንዲዳረጉ ሆኗል፡፡ ለብዙ ዘመናት የተገነቡ ከተሞች፣ የሕዝብና

የሀገር ሀብት ወድመዋል፡፡ የተቀጠፈው የሰው ሕይወት፣ የወደመው የሀብት መጠን በውል ማወቅ በማይቻልበት ሁኔታ በቤተ ክርስቲያንም ላይ ሊተካ የማይችል ዘግናኝ ኪሳራ ደርሷል፡፡ ይህ ክሥተት በ፳ኛው ምእት ዓመት ዘመነ ሰማዕታት ተብሎ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተመዝግቦ ከምናነበው ታሪክ ጋር የሚመሳሰልበት፣ ክርስቲያኖች በዋሉበት እንዳያድሩ፣ በአደሩበት እንዳይውሉ የተደረገበትን ታሪክ የሚያስተውልና የሚያረጋግጥ፣ ቤተ ክርስቲያንን የሚፈትን በሰቆቃ የታጀበ አባቶችንና ሁላችንን ለሰማዕትነት የሚያዘጋጅ ዘመን ነው፡፡

ስለሆነም እንዲህ ዓይነቱ ክፉ ዘመን አሁን በምናየው አህጉረ ስብከት በመተባበርና በመረዳዳት መንፈስ በመተጋገዝ፣ በመተዛዘን እግዚአብሔር አምላክ የምሕረትና የሰላም እጁን ይልክልን ዘንድ በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት ንጹሕ መሥዋዕትን በማቅረብ ምሕረትን መጠየቅ ስለሚገባ በዚህ ዘርፍ ያለመታከት ጠንክረን ለመሥራት ቃል እንገባለን" ተብሎ በሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ተሰብሳቢዎች የተላለፈው መግለጫ በቤተ ክርስቲያን ላይ የደረሰው መከራ እንዲቀንስ ተባብረን በመሥራት ችግሩን ማስገንዘብ የሚኖርብን መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ይህም ከአባቶች ሊቃነ ጳጳሳት፣ ከካህናት፣ ከሊቃውንት፣ ከሰባክያነ ወንጌል፣ ከምእመናን የሚጠበቅ ኃላፊነት መኖሩን ስለሚያስገነዝብ ተግባራዊ ሥራ የሚከናወንበትን ዕቅድ አውጥቶ መተግበር እንደሚገባ ይጠቁማል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ካህናትንና ምእመናንን አስተባብራ በመሥራት በልጆቿ ብሎም በመላ ሀገራችን ላይ እየነደደ ያለው እሳት እንዲቀዘቅዝ የሚጠበቅባትን ሁሉ ማድረግ ከቻለች ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት ሰጠች ማለት ነው፡፡ ይህን በተግባር ከገለጠች ተሰሚነቷና ተቀባይነቷ ይጨምራል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ዜጎች ሲጎዱ ቀድማ ከመድረስ በተጨማሪ የሠራችውን በብዙኃን መገናኛ ማሳወቅ ይኖርባታል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ለሰላም መስፈን የማይገዳት፣ ሰው ሲቸገር ለመርዳት ርኅራኄ የሌላት አስመስለው የሚያስወሩትን የመከራ እሳት እየጫሩ አዛኝ የሚመስሉ መሠርያንን አፍ ማስያዝ የምትችለው በመታገሥ ብቻ ሳይሆን የሠራችውን በማሳወቅና ከሚመለከታቸው ጋር ሁሉ ተባብራ በመሥራት ጭምር ነው፡፡

አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ መምከርና አሳብ መስጠት የሚኖርበት ለእንደዚህ ዓይነት ተግባር ጭምር እንጂ ለሐዋርያዊ አገልግሎትና ከምእመናን የሚሰበሰበው ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ መዋል አለመዋሉን ለመከታተልና ለመቈጣጠር ብቻ አለመሆኑን መረዳት ይገባል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ነገ የምትሠራውን ለማለም ትላንት የገጠሟትን ፈተናዎች እንዴት እንዳለፈቻቸው መርምሮ እንድንማርበት ማድረግ ከሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡ ከትላንቱ ለዛሬውና ለነገው አገልግሎት መጠናከር የሚያግዘንን ቁም ነገር አግኝተን ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት ለመስጠት እንችላለን፡፡✤

# አርአያነት ተግቶ በመሥራት

ቢኒያም ወልዱ

በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት ዕለቱን ተፈጥረው፣ ዕለቱን ያልሳቱት አባታችን አዳም እና እናታችን ሔዋን በምክረ ከይሲ ከመውደቃቸው በፊት ለሰባት ዓመታት የኖሩት በገነት ነበር። ገነት በኖሩባቸው ሰባት ዓመታት ሲጠብቋት፣ ሲፈጽሟትም የነበረች ሕግ ተሰጥታቸው ነበር። ለአባታችን አዳም የተሰጠችውን ሕግ በአንድ ቃል እንጥራት ብንል ሥራ ወይም የመሥራት ሕግ ትባላለች። የመሥራት ሕግ ለሌሎች አርአያ መሆንን፣ ሠርቶ ማሠራትን፣ ለደከሙት ምርኩዝ መሆንን ገንዘብ የምናደርግበት ነው። ይህችን ሕግ አስቀድሞ በተግባርና በቃል ያስተማራት እግዚአብሔር ነው። ይህች ሕግ ከሰው ልጅ ውድቀት በፊትም ሆነ በኋላ ጸንታ የኖረች፣ ከ፲ ትእዛዛትና ከስድስቱ ቃላተ ወንጌልም ጋር የነበረች በዳግም ምጽአትም የሰው ልጅ "አይቴ ነበርከ ምንተ ገበርከ፡- የት ነበርክ? ምን ሠራህ?" ተብሎ የሚጠየቅባት ሕግ ናት። ምን ሠራህ የሚለው? ትእዛዝ ምግባርን የሚገልጥ፣ በተሰጡት መክሊት ማትረፍን የሚያጠይቅ ነው።

ብሉይ ኪዳን የተጻፈላቸው እስራኤላውያን ፲ ቃላተ ኦሪትን፣ የሐዲስ ኪዳን ሰዎች ወይም ክርስቲያኖች በብሉይ ኪዳን ከተሰጠው በተጨማሪ ስድስቱ ቃላተ ወንጌልን ጨምረው ስለመፈጸምና አለመፈጸማቸው ይጠየቃሉ። ይህም ማለት የሰው ዘር ሁሉ ቀዳማዊት ሕግን ስለመፈጸምና አለመፈጸሙ ይጠየቃል ማለት ነው። የሚጠየቀውም በቃል የተማረውን በሥራ መግለጥ አለመግለጡን እንዲናገር በማድረግ በየዘመኑ የሚነሣውን ትውልድ ማስተማር ነው።

ስለ ሥነ-ፍጥረት የሚናገረው መጽሐፈ ኩፋሌ አዳምና ሔዋን በኃጢአት ከመውደቃቸው አስቀድሞ እንዴት በገነት እንደኖሩ መጠነኛ ፍንጭ የሚሰጠን "በመጀመሪያው ሱባኤ በመጀመሪያ ኢዮቤልዩ አዳምና ሚስቱ በገነት ሰባት ዓመት ሲኖሩ/ሲገዙ ሕጉንም ሲጠብቁ ኖሩ። ሥራንም አስተማርነው ለማገልገል ተገልጦ የሚታየውን ሥራ ሁሉ ስናስተምረው ኖርን። እርሱም ሲያገለግል ኖረ.....ተክልንም ከአራዊትና ከወፎች፣ ከእንስሳትም ይጠብቅ ነበር" በማለት ነው (ኩፋ.፬፡፲፬-፲፫)። በመጀመሪያው ሱባኤ የሚለው የመጀመሪያውን ሰባት ዓመት ነው። የመጀመሪያው ኢዮቤልዩ ማለት ደግሞ ሰባት ጊዜ ሰባት ሱባኤ አርባ ዘጠኝ ዓመት ተቈጥሮ ኀምሳኛው ዓመት ማለት ነው።ስለዚህ ምንባቡ የሚነግረን በመጀመሪያው ኀምሳ ዓመት (ሰባት ሱባኤ) ውስጥ በመጀመሪያው ሰባት ዓመት (አንድ ሱባኤ) አዳምና ሔዋን ምን በመሥራት ያሳልፉ እንደነበር ነው። ከመላእክት የተማሩትን ሠርቶ አርአያ መሆንና በሥራ እግዚአብሔርን ማስደሰት ሲፈጽሙ ኖረዋል። ለአዳምና ለሔዋን ሥራ ያስተማሩ መላእክት ሥራ ፈትቶ በመቀመጡ ሰይጣን በአሳብ ሲፈትነው ለነበረው ለአባ እንጦንስም አስተምረውታል። ይህ ሕግ ክርስቲያኖች ሠርተው ማትረፍ እንጂ ከሰው መቀበልን እንዲጠየፉ ሲያደርጋቸው ኖሯል። የክርስቲያኖች አርአያነት የሚገለጠው ሠርቶ በመብላት ብቻ ሳይሆን ሠርቶ ለሌላቸውና አቅም አጥተው ለወደቁ በመስጠት ጭምር ነው።

የመጀመሪያ ማኅበራዊ ኑሮ መሥራቾች አዳምና ሔዋን በመጀመሪያው ሱባኤ ፍጥረቱን እና ገነትን ማለትም በውስጧ የሚገኙትን ዕፀዋቱንም፣ አትክልቱንም፣ እንስሳቱንም፣ አራዊቱንም በመግዛት ሕጉን ሲጠብቁ ኖረዋል። ሲገዙ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍቺው ከሁለቱ በቀር ማንም በሌለበት ገነት ሲሸጡ፣ ሲለውጡ ነበር ማለት አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ "በደሙ ገዛን" ማለቱ በፍቅሩ ዋጀን፣ በሞቱ ሞትን አጥፍቶ ሕይወትን ሰጠን ማለት እንደሆነ ሁሉ ሲገዙ ኖሩ ማለትም ተክሎችን ሲንከባከቡ፣ እንስሳቱንም ውኃ ከመነጨበት፣ ለምለም ከበቀለበት እያዋሉ ሲጠብቋቸው ነበር ማለት ነው እንጂ። የሚሠራው ሥራ ሲፈጠር ሠራተኛም ይከተላልና ገነት እንደተፈጠረች ሠራተኞቹ አዳምና ሔዋን ተከትለው ተገኝተዋል። ለምን የሚል ጥያቄ ቢነሣ መልሱ ሊገዟት የሚል ይሆናል።

ጸሓፊው ይገዙ ነበር በማለት ብቻ አላበቃም። ሕጉንም ሲጠብቁ ነበር በማለት አክሏል። እርግጥ በእነዚያ የመጀመሪያ ዘመናት ይጠብቋት ዘንድ የተሰጠቻቸውን የቃልም ሆነ የጽሑፍ ሕግ ልናገኛት አንችልም። ነገር ግን በልቡናቸው ሠሌዳ ተጽፋ የምትገኝ ሕግ ነበረቻቸው። ይህችም ሕግ በልቡናቸው ጽላት የተጻፈች፣ በተግባርም የምትገለጥ ትእዛዝ ነበረች። ምንባቡ አዳምን ሥራን አስተማርነው፤ ተገልጦ ያገለግል ዘንድ የሚታየውን ሥራ ሁሉ ስናስተምረው ኖርን የሚለው ክርስቲያኖች በሥራ ሲጠመዱና መልካም ሲያደርጉ መልእክት እንደማይለዩዋቸው ተስፋን የሚሞላ ቃል ነው። ይገርማል በመጀመሪያዎቹ ሰባት ዓመታት እግዚአብሔር አዳምን ሥራ ሲያስተምር የሰው ልጅ ደግሞ ተክልን ከአራዊት፣ ከወፎች እና ከእንስሳትም ሲጠብቅ ነው የኖረው። እግዚአብሔርን የሥራ ባለቤት/መሥራች፣ ሥራንም የመጀመሪያው ትእዛዝ ያሰኘው ይህ ነው። "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም፣ ይጠብቃትም ዘንድ በኤደን ገነት አኖረው" የተባለው የሚገልጠውም ይህን ነው(ዘፍ. ፪፥፲፭)።

በዚህ የቅዱስ መጽሐፍ ቃል እንደምንመለከተው እግዚአብሔር ሰውን ወስዶ በገነት ያኖረው መኖሪያው ገነትን ያበጃትና ይጠብቃት ዘንድ ነው።መጠበቅ እንዳይበላሽ መከላከል፣

ማበጀትም፣ ማቆየት እንደ አስፈላጊነቱ መንከባከብና የተበላሸውን በመጠገን ማስተካከል እንደማለት ነው። እንግዲህ አትክልት ጥበቃ የመጀመሪያው ሞያ መሆኑን ልብ ይሏል። አዳም ግን በገነት ሲኖር ወደ ገነት የመጣበትን ዓላማ ጠብቆ መቆየት አልቻለም። እንዳትነካ ጠብቃት ከተባለችው በገነት መካከል ከነበረችው የበለስ ፍሬ ቆርጦ በላ። የተሰጠው ኃላፊነት ከሌሎች መጠበቅ ቢሆንም ተግባሩን ዘንግቶ ራሱ ቆረጣት።የተቀጣውም ብላ ያለውን ትቶ አትንካ የተባለውን ቆርጦ በመብላቱ ነው።

አዳም ያልተፈቀደለትን ቆርጦ በመብላቱ ራሱ ተክሎ እንዲበላ ለዚያውም ጥበቃውን ያጎደለባት መሬት ሥራ እንድታበዛበት ከእርግማን ሥር ተሰጠችው። እግዚአብሔርም "በሕይወት ዘመንህ ሁሉ በድካም ከእርሷ ትበላለህ። እሾህና አሜኬላንም ታበቅልብሃለች። የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ፤ ወደ መጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ፤ አፈር ነህና ወደ አፈርም ትመለሳለህና" (ዘፍ.፫፣፲፯) በማለት ቁርጡን ነገረው። አምላካችን እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን ከባድ ቃል የሚናገው የታዘዙትን የማይፈጽሙትን፣ ወገናችሁን ታደጉ ሲባሉ መክሊታቸውን ለማውጣት የሚነፍጉትን ለመውቀስ ነው።

እግዚአብሐርም ምድር እሾህና አሜኬላ በማብቀሏ "ወደ መጣህባት ምድር እስክትመለስ በሕይወት ዘመንህ ሁሉ እንጀራህን በድካምህ ትበላለህ" ሲለው የመሥራት ሕግ ተጠናክራ እስከሞት ድረስ እንደምትቀጥል የሚያሳይ ነው (ዘፍ.፫፣፲፯)። ስለዚህ ሠርቶ መብላት እስከሞት ድረስ ልንጠብቀው የሚገባ የሕይወት ዘመን ሕግ ነው ማለት ነው።ከውድቀት በኋላ ከገነት የተባረረው አዳም ሰባት ዓመታት ከኖረባት ርስቱ ከገነት የተረፈው ውርስ በጣርና በጋር መሥራት ብቻ ነበር። ሰው የኑሮውን ሁለተኛ ምዕራፍ የጀመረው በዚህች ትእዛዝ ነው። ስለዚህም የሙሴ መጽሐፍ እንዲህ ይለናል "እግዚአብሐርም የሠራውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ፤ በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ" (ዘፍ.፪፣፪)።

እግዚአብሐር በመጀመሪያዎቹ ስድስት ቀናት ሁሉን ፈጥሮና አዘጋጅቶ ምድርን አበጃት።በሥራው ፍጻሜ ዕለት ዐርብም አዳምን ከምድር አፈር በአርአያውና በአምሳሉ ፈጠረው። እርሱም ስድስት ቀን ሠርቶ በሰባተኛው ቀን እያረፈ ሲያቀናት ኖረ። እግዚአብሐር ከስድስት ቀናት ሥራ በኋላ ያረፈው የሚደክም ባሕርይ ኖሮት ማረፍ አስፈልጎት ሳይሆን በአርአያውና በአምሳሉ ፈጥሮ ምድርን እንዲያበጃት፣ እንዲጠብቃትም ሥልጣንና ኃላፊነት ለሰጠው ለአዳም የሚሠራበትንና የሚያርፍበትን ሥርዓት ሲሠራለት ነው። አዳም ከዚህ በኋላ ለሁሉም ፍጥረት ኃላፊነት ስለ ነበረበት እግዚአብሐር ቀስ በቀስ ሥራ ያስተምረዋል። ከዚያም የአዳም ዘር በሙሉ ለትውልደ ትውልድ ምድርን ለማበጀት የየራሱን ጸጋ እየያዘ የሚወለድ ሆኗል።

ማኅበራዊ ኑሮን "ሀ" ብሎ የጀመረው የመጀመሪያው ቤተሰብ ምድርን ያበጃት ዘንድ የተለያየ የሥራ ክፍፍል ነበረው። አቤል

ጠብቃት ከተባለችው በገነት መካከል ከነበረችው የበለስ ፍሬ ቆርጦ በላ። የተሰጠው ኃላፊነት ከሌሎች መጠበቅ ቢሆንም ተግባሩን ዘንግቶ ራሱ ቆረጣት።

በግ አርቢ ሲሆን ቃየን፣ ደግሞ ገበሬ ነበር። ያንዱ ሥራ ከሌላው ጋር ተመጋጋቢ ነበር። አቤል ያረባቸው የነበሩ በጎች የቃየልን ዕፀዋት በልተው ይኖሩ ነበር። ዕፀዋቱ ከእግዚአብሔር የሚያገኙትን የፀሐይ ኃይልና ከሰው የሚያገኙትን የተቃጠለ አየር ተጠቅመው ለራሳቸው ምግብ ሠርተው ያድጉና ለሰው ሕይወት የሚያስፈልጉትን ምግብና እጅግ ወሳኙን ያልተቃጠለ አየር ይሰጣሉ። እንዲህ እንዲህ እያለ በእንስሳትና በዕፀዋት፣ በሰውና በሌሎቹ ፍጥረታት መካከል የሚኖረው ግንኙነት ይጎለብታል። ይህ በእግዚአብሔር የመግቦት ጥበብ የተከናወነ ሥነ ፍጥረታዊ ሂደት የሚመራው በሥራ ሕግ ነው። አቤል እንስሳትን ሲያረባ፣ ቃየል ዕፀዋትን ባይንከባከብ ኖሮ በአጠቃላይ አዳም ምድርን ባይንከባከብ ኖሮ የፍጥረት ሁሉ በሕይወት መቀጠል ሕልም ሆኖ ይቀር ነበር። እንግዲህ የሰው ልጅ ይህን እንዲፈጽም የታዘዘው የሕይወት ሂደት እንዳይስተጓጎል ነው።

ግብርናና እንስሳት ርባታ የምግብ ምንጭ በመሆን ለመኖር የሚያስፈልጉ ዋነኛ ሞያዎች ናቸው። "ምድሩን የሚያርስ እንጀራ ይጠግባል" ተብሏልና(ምሳ.፳፱፣፲፱)። "የእጅህን ድካም ትበላለህና ምስጉን ነህ፤ ድኅነትም ትሆንልሃለች" በማለት ነቢዩ የተናገረው የሚገልጠው የሥራን አስፈላጊነት ነው (መዝ.፻፳፯፣፪)። ቀድሞ አዳምን ጸጋ እግዚአብሔር ሸፍኖት ነበርና ልብስ አያስፈልገውም ነበር።ትእዛዝ ባፈረሰ ጊዜ ጸጋው ከተገፈፈ በኋላ ግን ልብስ አስፈለገው።ስለዚህም የመጀመሪያውን ልብስ እግዚአብሔር ራሱ ለአዳም አለበሰው። ከዚያም ራሱ እየሠራ መልበስ ጀመረ።ሴት ፈትላ፣ ወንድ ሸምኖ መልበስ ተወጠነ ማለት ነው።

ሥራ የማኅበራዊ ኑሮ መሠረት የሚሆነውም ለዚህ ነው። ይህን የሥራ ልምድ እመቤታችን በቤተ መቅደስ እየፈተለች በማደጓም ልንረዳው እንችላለን። አበው በብሂላቸው "ሰው ካልበላ ሬሳ፣ ካልለበሰም እንስሳ ነው" እንደሚሉት ማለት ነው። ይህም ሰው ደክሞ፣ ሠርቶ ካልበላ ሕይወት እንደሌለው፣ ፈትሎ፣ ሸምኖ ካልለበሰም እንደ እንስሳ መሆኑን የሚያመለክት ነው። ሌሎቹ ፍጥረታት በተፈጥሯዊ ሂደት ምግብና ልብሳቸውን ሲያገኙ አእምሮ ልቡና ያለው አዳም ግን ይህን ፍላጎቱን የሚያሟላው የመሥራት ሕግን በመፈጸም ነው።

በምድሪቱ ነዋሪዎች ሲበዙ፤ ማኅበራዊ ኑሮው ሲሰፋ አዳምም ከእግዚአብሔር ጋር በመጣላቱ፤ ፍጥረታትም ተጣልተውት ነበርና እንዳይበሉት፤ ሰውነቱ በመራቆቱ ዋዕየ ፀሐዩን፣ ብርድና ቆፈሩን የሚከላከልበት ቤት አስፈለገው። ስለዚህም አናጺነት፣ ግንበኝነት፣ በሞያ ስሙ ምሕንድስና የሚባለው ተጀመረ። ሰው እየበዛ በቅርበት በቃል ለመነጋገር የሚያስችል ሁኔታ ሲመናመንም በጽሑፍ አሳብን ለመግለጥ ይቻል ዘንድ እግዚአብሔር ለሄኖስ በጸፍጸፈ ሰማይ ጽሕፈትን አሳየው።

ለሙሴም በጽላት አሥሩን ቃላት ጽፎ ሰጠው። ሙሴ ኃጢአት በሠሩት በሕዝበ እስራኤል ተበሳጭቶ ጽላቱን ከሰበረው በኋላም እንደገና ሠርቶ እንዲያመጣ አዞት ጽላቱን ቀርጾ ሲያመጣ በላዩ ላይ ትእዛዛቱን ጽፎ ሰጠው። ለሰው ልጅ እጅግ ከሚያስፈልጉት ነገሮች አንዱ የጽሕፈት ሞያ በእግዚአብሔር አስተማሪነት፣ በሄኖስ እና በሙሴ ተማሪነት ተጀምሮ ከዘመናችን ደርሷል። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ካስተማራቸው ታላላቅ ሞያዎች አንዱ የሆነው የጽሕፈት ሥራ በሰው ሕይወት ውስጥ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው።

በተለይ የእግዚአብሔርንና የሰው ልጅን ግንኙነት የሚወስኑትን ቅዱሳት መጻሕፍትን ስንመለከት የጽሕፈት ሥራ ትሩፋት ምን ያህል የተቀደሰ ተግባር መሆኑን እንረዳለን። የሰው ሕይወት ዋና ዋና መለያዎች የሆኑት ሃይማኖትና ቀኖና፣ ጽድቅና ኩነኔ ሁሉ ተሰንደው የተቀመጡት በጽሑፍ ነው። በላይኛው ሀገር የሚጠብቀን ዕድል ፈንታችን፣ ጽዋ ተርታችን የተቀመጠው በጽሑፍ ነው። በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተገለጠው ሙሴ "ሕዝብህን የማትምርልኝ ከሆነ እኔን ከመጽሐፈ ሕይወትህ ሰርዘኝ" ብሏል። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመዋዕለ ትምህርቱ ሐዋርያትን መከራውን ይለማመዱ ዘንድ እንዲያስተምሩ ልኳቸው በነበረ ጊዜ ተልእኳቸውን ፈጽመው ሲመለሱ "አጋንንት ተገዙልን" ብለው ደስ አላቸው። እርሱ ግን "አጋንንት ስለተገዙላችሁ ደስ አይበላችሁ፤ ስማችሁ በሰማይ ስለተጻፈ ደስ ይበላችሁ እንጂ" ብሏቸዋል። እነዚህ ምንባቦች በሰማይ ያለው ጽድቅና ኩነኔ የሚገለጠው በጽሑፍ መሆኑን ይነግሩናል።

ከላይ በተመለከትናቸው የተወሰኑ የሥራ ዘርፎች በመጀመሪያ ራሱ ሠርቶ እያሳየ ቀጥሎም እያስተማረ ሥራ ያለማመደው ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ተረድተናል። የሁላችን አባት አዳምም በአምሳሉ በመፈጠሩ የተማረውን ፈጥኖ በመቀበልና በመተግበር ምድሪቱን በማበጀትና ቀዳሚቱን ትእዛዝ በመፈጸም ለሰው ዘር ሁሉ አስተላልፏል። የሰው ልጆች ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት በሚለው አምላካዊ ቃል መሠረት በዝተው ምድርም በልጽጋ በነበረችበት በዘመነ ኖኅ ከትእዛዘ እግዚአብሔር ገሸሽ ባሉት የሰው ልጆች ኃጢአት ምክንያት ዓለም ልትጠፋ ሲሆን ከጥፋቱ ለመዳን የእግዚአብሔር ሰው ኖኅ የታዘዘው መርከብ እንዲሠራ ነበር።

ኖኅ ገና የተባለው ዝናብ ሳይመጣ ደመናውም ሳይታይ እግዚአብሔር የነገረውን ቃል ብቻ አምኖ ለሁሉ የሚሆን መርከብ ሠራ። ኖኅ መርከቡን ሲሠራ ያገዙት ጥቂት ናቸው። ከጥፋት ውኃ ለመዳን ወደ መርከቡ እንዲገቡ የጋበዛቸው ግን ብዙ ነበሩ። ለመሥራት ሰንፈው ሲስቁበት የነበሩት የዘመኑ ሰዎች ስንፍና ለምደባቸው መጠለያ ሠርተው ለመግባት ከመቶ ዓመት በኋላ እየቀጠሩ ኃጢአት መሥራታቸውን ቀጠሉ። ለነገ ከማለት የከፋ ኃጢአት ላይ ወድቀው አንገባም አሉ። የኖኅ ዘመን ሰዎች ያልተረዱት የሥራ ጊዜ ዛሬ ይልቁንም አሁን መሆኑን ነው። መልካም ማድረግና ሰዎችን መርዳትም ለነገ የሚቀጠር አይደለም። ለሥራ ቀጠሮ መስጠት አያስፈልግም። ጊዜ ለነገ ብለው የማይቆጥቡት፣ ይመለስልኛል ብለው የማያበድሩት፣ እንዳገኙት ብቻ የሚጠቀሙበት ጸጋ ነው።✤

***ይቆየን***

# ርእሰ አድባራት ደብረ ኮሪራ ቅድስት ማርያም

**ክፍለ ማርያም**

ጥንታዊት የሆነችው ርእሰ አድባራት ደብረ ኮሪራ ቅድስት ማርያም /ታቦተ ጽዮን/ ቤተ ክርስቲያን የምትገኘው በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት በመርሐ ቤቴ ወረዳ ኮራ ታሞ በተባለ ቀበሌ ተራራማ ቦታ ላይ ነው። የደብረ ኮሪራ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በተመሠረተችበት ቦታ ከክርስቶስ ልደት በፊት መሥዋዕተ ኦሪት ይቀርብበት እንደ ነበር ይነገራል። በዚህ ምክንያት ርእሰ አድባራት የሚል ስያሜ እንደ ተሰጣት የገዳሙ የቃል ትውፊት ያስረዳል።

ቤተ ክርስቲያኗ ጥንታዊ መካን መሆኗን ታሪክ የሚያስረዳው ቦታዋ የኦሪት መሥዋዕት ይሠዋባቸው ከነበሩት አክሱም ጽዮን፣ ጣና ቂርቆስ፣ መርጡለ ማርያም፣ ተድባበ ማርያምና ብርብር ማርያም ጋር የምትጠቀስ በመሆኗ ነው። አሁን ቤተ ክርስቲያኗ በምትገኝበት ኮራ በተባለው መስቀለኛ ቅርጽ ባለው ተራራማ ቦታ ላይ አገራችን ክርስትናን እስከተቀበለችበት ጊዜ ድረስ መሥዋዕተ ኦሪት ሲሠዋበት፣ ሕገ ኦሪት ሲፈጸምበት ቆይቷል። ዘመኑም እስከ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን መሆኑ ይነገራል።

የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ ስትመራበት በቆየችው ሕገ ኦሪት ላይ ሕገ ወንጌልን ተቀብላ በመሥዋዕተ ኦሪት ፋንታ መሥዋዕተ ወንጌልን ወይም የሐዲስ ኪዳኑን ሥርዓተ ቊርባን በመቀበል አገልግሎት ስትሰጥ ኖራለች። በአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ቅዱሳን ነገሥታት አብርሀና አጽብሐ የክርስትና ሃይማኖትን ለማስፋፋት በመላ ኢትዮጵያ እየተዘዋወሩ ቀድሞ የነበሩትን ሲያድሱና አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት ሲተክሉ ይችንም ቤተ ክርስቲያን አሠርተዋል። በዘመኑ በነበሩ አባቶች ብርታት አብርሀና አጽብሐ ያሠሯት ቤተ ክርስቲያን ስትተርፍ ሌላው ቅርሷ እና ታሪኳ በግራኝ ወረራ በሙሉ ተቃጥሎ ወድሟል። የቤተ ክርስቲያኗን ቅርስ ከነታሪኳ ያወደመው የግራኝ ወራሪ ሠራዊት እንደተሸነፈ ቤዛነ ወልድ የተባለ ሰው ከጎንደር መጥቶ ቤተ ክርስቲያኒቱን ጥንት በነበረችበት ቦታ ላይ እንደ ጥንቱ አድርጎ አሠርቷታል።

ቤዛነ ወልድ ቤተ ክርስቲያኗን አሠርቶ ታቦቱን ካስገባ በኋላም በፈጸመው አገልግሎት ሳይወሰን ቤተ ክርስቲያን የምትተዳደርበትን ሥርዓት ሠርቷል። እንዲሁም ርስትና ጉልት በመትከል እንድትገለገል አድርጓል። የተሰጣት ርስትም በቤተ ክርስቲያኗ አጥቢያ ክልል ሳይወሰን መርሐ ቤቴ ተብሎ በሚጠራው አውራጃ ላይ ቤትና ታች ቤት ወረዳ ከዘረት ደባ እስከ ማርያም ሠርቃ /ከርግቢኦት እስከ ገደልጌ/ ከሚገኙት አጥቢያዎች ለዚህች ቤተ ክርስቲያን መገልገያ የሚሆን የርስት መሬት እየተከለለ ተሰጥቷል።

ቤዛነ ወልድ ለ፳ መምህራን፣ ለ፯ ሰሞነኞች/ቀዳስያን/፣ ለ፲ ሰዓታት ቋሚ፣ ለ፪ ዘይነገሥ አድራሽ፣ ለዐቃቢ እና ለቀራፊ፣ ለበር ጠባቂ፣ ለመጋረጃ ፈታይ፣ ለብረት ሠራተኛና ለሸክላ ሠሪ ለእያንዳንዳቸው መተዳደሪያ በመወሰን ባለ ርስት፣ ባለጉልት አድርጎ በመትከል የተሟላ መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲሰጥባት አድርጓል። ከዚህም በተጨማሪ ለመገበሪያ /መሥዋዕት/ ችግር ከተባለው ቦታ፣ ለዕጣንና ለጧፍ ቃባ ከተባለው ቦታ የኩዳድ መሬት እንዲሰጥ አድርጓል። ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠው የኩዳድ መሬት በአጥቢያው ሕዝበ ክርስቲያን እየታረሰና አዝመራው እየተሰበሰበ የሚገኘው ምርት ለመገበሪያ፣ ለዕጣንና ለጧፍ መግዣ ይሆን ነበር።

ቤዛነ ወልድ ሥርዓት ሠርቶ፣ ርስት ጉልት ወስኖ ትክሉን ከአመቻቸ በኋላ እሱ ሲሞት ወልዱ የተባለ ክርስቲያን ተተክቶ ቤዛነ ወልድ የተከለውን ሥርዓት ሁሉ በማጠናከር በሥራ ላይ እንዲውል አድርጓል። በዚህ መልኩ ለአገልጋዮች አንድ ዓይነት የደመወዝ አከፋፈል እንዲሰጥ አድርጓል። ይህም ለላይ ቤትና ታች ቤት በመርሐ ቤቴ የመስፈሪያ ልክ እንዲሆን በመደረጉ እስካሁን ድረስ የወልዱ ቁና እየተባለ ይጠራል።

የቤተ ክርስቲያኒቱ መተዳደሪያ ከላይ እንደ ተገለጸው በመሬት ሥሪትና ትክል እንደ መሆኑ በዚህ ትክልና ሥሪት እስከ ፲፱፻፴፯ ዓ.ም. ስትገለገል ቆይታ በ፲፱፻፴፯ ዓ.ም. የመሬቱ ግብር ወደ ገንዘብ ተለውጦ ሲገመት የቤተ ክርስቲያኗ መተዳደሪያ ሆኖ የቆየው ርስት በሰሞን መሬት ተገምቶ ገቢው የግብር ገንዘብ የአሥራት ተመላሽ እየተባለ ከቤተ ክህነት ውጭ ሆኖ እየተከፈለ ከመሬቱ የሚያገኙት ጥቅም ሳይቀር እስከ ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ድረስ ለአገልጋዮች ሲከፈል ቆይቷል።

ከቤዛነ ወልድ ቀጥሎ በወልዱ በይበልጥ የተጠናከረችው ቤተ ክርስቲያን የወልዱ የልጅ ልጅ በሆነችው በወ/ሮ በዛብሽ ደጀን ጊዜ እንደተሠራች በዚህችው ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊ የብራና መጽሐፍ "ዛቲ መቅደስ ዘተሐንጸት በዘመነ ሉቃስ በመንግሥተ ኃይለ መለኮት በፈቃደ ወለተ ማርያም ወ/ሮ በዛብሽ ደጀን / ወልዱ ዘሐነጽዋ ፩. ኪዳነ ወልድ፣ ፪. ወልደ ጊዮርጊስ ሠርፀ ወልደ አባ ጉራች ፫. ወልደ ማርያም የምሩ በወርኃ መጋቢት ፳፰ መዓልት ፲፩ ሠርቀ ሌሊት" በማለት ተመዝግቦ ይገኛል። የታነጸችውም ከአንኮበርና ከሌሎችም ቦታዎች በመጣ የጽድና የዝግባ እንጨት እየተጠረበ እንደነበር ይነገራል።

በዚህ ዓይነት በብዙ ድካም የታነጸችው ቤተ ክርስቲያን ታሪካዊነቷን እንደያዘች ሥርዓቷን ጠብቃ የወልዱ የልጅ ልጅ

ከሆኑት ወ/ሮ በዛብሽ ደጀን እስከ ዓፄ ምኒልክ ዘመን ደርሳለች። ጥንታዊትና ቀዳማዊት የሆነችው ቤተ ክርስቲያን በአያቶቻቸው

**በዘመኑ በነበሩ አባቶች ብርታት አብርሀና አጽብሐ ያሠሯት ቤተ ክርስቲያን ስትተርፍ ሌላው ቅርሷ እና ታሪኳ በግራኝ ወረራ በሙሉ ተቃጥሎ ወድሟል።**

የተሠራውን ሥርዓት፣ የተተከለውን ጉልት የተረዱት ዓፄ ምኒልክ በዘመነ መንግሥታቸው የትክል ሥርዓት ጎልቶ ርእሰ አድባራት መሆኗ በቤተ መንግሥት መዝገብ እንዲመዘገብ እንዲሁም ቀድሞ ከተሰጣት መተዳደሪያ በተጨማሪ የጋርዳ ቅዳሜ ገበያ ቀረጥ በአጥቢያዋ ክልል የአፋቺ፣ የተፋቺ፣ የዳኝነት ገቢ ለቤተ ክርስቲያኒቱ መተዳደሪያና መርጃ እንዲውል አድርገዋል።

ከዚህም በተጨማሪ በአጥቢያዋ ወይም በሰበካዋ ክልል ውስጥ የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳዳሪ ካልሆነ በቀር የዘገር /ሥጋዊ/ ዳኛ አገረ ገዥ እና ምስለኔ የመሳሰሉት ዳኝነት የመዳኘት፤ ጠርቶ የመጠየቅ ሥልጣን እንዳይኖር በሰበር እንዳይገባ ሥርዓት ሠርተውለታል። ማንኛውም ወንጀለኛ በቤተ ክርስቲያኗ ክልል ውስጥ በመግባት ከደወለ (በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብቶ ማሩኝ ብሎ ከደወለ) አገረ ገዥም ሆነ ዳኛ አጠፋ ብሎ አይቀጣውም ነበር። ዳኝነቱ የደብሩ አስተዳዳሪ ስለነበር ግራ ቀኙን አስቀርቦ ያስታርቃል። ተበዳዩም ስለታቦተ ጽዮን ክብር ሲል አልታረቅም ማለት ስለማይችል ከባለጋራው ይታረቃል።

ለቤተ ክርስቲያኑ የሚሾመው አስተዳዳሪ ከቤተ ክህነት ጋር በተቀናጀ አሠራር በመንግሥት ሲሆን ለመተዳደሪያ የሚከፈለው ገንዘብ (ምንዳም) ጋሻ መሬት የሚባል የግብረ ጠል፣ የምልምል፣ የውድቅና የጠፍ መሬት ከግዴታ ድግስ የሚተርፍ ገቢ ነው። ለአስተዳዳሪው ረዳቶች ምንዳ የሚከፈለውም ከተገኘው ገቢ ነበር። በአስተዳዳሪው እየታዘዙ የቤተ ክርስቲያኒቱን አገልግሎት የሚያከናውኑ ፲፪ የመሬት አለቆች ነበሩ።

አሥራ ሁለቱ አለቆች በየዓመቱ በጭቃ ሹምነት በገበዝነት፣ በፈረቃ በዓመት በዓመት በአስተዳዳሪው እየተሾሙ በውጭ የቤተ ክርስቲያኒቱን ሥርዓት ይቈጣጠራሉ፤ያስከብራሉ። ከዚህ በቀር የጥር ቅዴታና የሰኔ ቀዴታ የሚባል በዓመት ሁለት ጊዜ የሚከፈል በጥር ፳ ዳውላ፣ በሰኔ ፳ ዳውላ እህል እንደ ዓመት ግብር ተቈጥሮ ከሚገብሩት ያሰባስባሉ። የጥር ቀዴታ ለጥምቀት፣ ለትንሣኤና ለሰኔ የሚያስፈልገውን የጉልበት አገልግሎት በጭቃ ሹሙ እየታዘዘ ያስፈጫሉ፤ ያስነክራሉ፤ ጠላ ያስጠምቃሉ፤ ያስጋግራሉ፤ ዳስ ይጥላሉ። በአጠቃላይ የድግሱን ሥራ ያከናውናሉ።ከአስተዳዳሪው የሚሰጠውን ትእዛዝ ይፈጽማሉ፤ ያስፈጽማሉ። በውስጣቸው ያሉት ንኡሳን ገባሮች መሥራት የሚገባቸውን በትክክል መፈጸማቸውን ይቈጣጠራሉ።

የውስጥ አገልጋይ የመሬት ትክለኞች ቀዳስያን፣ ሰሞነኞች፣ የሌሊትና የመዓልት ሰዓታት ቋሚዎች መስጠት የሚገባቸውን አገልግሎት በትክክል ማገልገላቸውን አስተዳዳሪው በሚሾማቸው ገበዝና መርጌታ አማካኝነት የመቈጣጠሩ ኃላፊነት የአስተዳዳሪው ድርሻ ነበር። በሌላ በኩል በፈታይነት የተቀጠሩት ሴቶች ለደብሩ መጋረጃ የሚሆን ጥጥ ፈትለውና አሚልተው ማቅረባቸውን፣ ብረት ሠሪው ደግሞ ለድግስ ጊዜ የሚሆን ቢላዋ፣ ለግብርና አገልግሎት የሚሆን ማረሻና ማጭድ፣ ለቤተ ክርስቲያኑ ሥራ

ችንካር ሠርቶ ማቅረቡን፣ ሽክላ ሠሪዋም ለጠጅ መጣያ እና ለጠላ መጥመቂያ የሚሆን ጋን፣ ለውኃ መቅጃ የሚሆን እንስራ፣ ለወጥ መሥሪያ የሚሆን ሰታቴና ሌላም ነገር ሠርታ ማሟላቷን፣ በር ጠባቂው ደግሞ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ የሚያስገባው አንድ በር ብቻ በመሆኑ በሩን በትክክል መጠበቅ አለመጠበቁን የሚቈጣጠሩ ከአሥራ ሁለቱ የመሬት አለቆች በፈረቃ የሚሾሙት ሰዎች ኃላፊነት ነበር።

ጥንታዊት የሆነችው የደብረ ኮሪራ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በወረዳው ውስጥ ካሉት አብያተ ክርስቲያናት ለየት የሚያደርጋት ከክርስቶስ ልደት በፊት መሥዋዕት ኦሪት ይሠዋባት የነበረች፣ ሕገ ኦሪት የተሠራባት ቀዳሚ በመሆኗ ነው። ሌላው ለየት የሚያደርጋት ዐቢይ ነጥብ የቅዳሴ አገልግሎት የሚከናወነው ምን ጊዜም በሰባት ልኡካን መሆኑ ነው። በቤተ ክርስቲያኗ እንደሌሎች አብያተ ክርስቲያናት በአምስት ልኡካን መቀደስ የተከለከለ ነው። ቅዳሴውም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከዓመት እስከ ዓመት አይስተጓጎልም ነበር።

ስለደብረ ኮሪራ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከአባቶች ተያይዞ ሲነገር የመጣው ሌላው አስደናቂ ታሪኳ ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም በስደቷ ጊዜ መርሐ ቤቴ ደርሳ እንደነበር፣ ስለስደቷ የሚያስነብበው የሊቀ መላእክት ቅዱስ ዑራኤል ድርሳን መነገሩ ነው። በዘመኑም እመቤታችን በዚህች ቅድስት ቦታ ገብታ እንደ ዐረፈችና አካባቢውን እንደባረከችው ከአባቶች ተያይዞ ሲነገር የመጣው ታሪካዊ ትውፊት ያስገነዝባል። በዚህች ቦታ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታን ታቅፋ እንደተቀመጠች የሚያስረዳው የልጇ የወዳጇ እግር ዐርፎበት በነበረ ድንጋይ ላይ እንደማኅተም ታትሞ በመቅረቱ እስከ ዛሬ ድረስ የሚታይ ሕያው ምስክር በመሆኑ ነው።

ለክብሩም በየሳምንቱ እሑድና በታላላቅ በዓላት ይታጠናል። ከዚህም በተጨማሪ የጌታ መቀመጫ እየተባለ የሚነገርለት፣ እመቤታችን ያረፈችበት የድንጋይ ወንበር ታሪካዊነቱን እንደያዘ ይገኛል። ቤተ ክርስቲያኗ ከከፍተኛ ቦታ ላይ የምትገኝ በመሆኗ በአካባቢው በአራት ማዕዘን የሚገኙትን ወረዳዎች ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ክፍላተ ሀገራትን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእናቱን መደሰት ተመልክቶ ይህችን ሀገር አሥራት አድርጌ ሰጥቼሻለሁ ብሎ ቃል ኪዳን የገባላት በዚያች ተራራ ላይ መሆኑም ይነገራል።

በጀማ ፊት በኩል ከቤተ ክርስቲያኗ በስተ ምዕራብ በፈለቀው የእመቤታችን ፈዋሽ ጸበል ተጠምቀው ከልዩ ልዩ ደዌ እንደዳኑ፣ ዐይናቸው እንደበራላቸው፣ ጸበሏንም የቀመሱ ብዙ ሰዎች ቃለ እግዚአብሔር እንደተገለጸላቸው መስክረዋል። ከዚህ በተጨማሪም ለቤተ ክርስቲያኗ የሚነገርላት ታሪክ አለ። ይኸውም የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ግማደ መስቀሉ ወደ ኢትዮጵያ በገባ ጊዜ "አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል፤ መስቀሌን በመስቀለኛ ቦታ ላይ አስቀምጥ" ተብሎ ከተነገረለት ግሸን ደብረ ከርቤ እስከሚደርስ ተመሳሳይ በሆኑ ቦታዎች በሚያርፍበት ጊዜ የመስቀል ቅርጽ ከአለበት ተራራ ላይ ዐርፎ ሦስት መዓልት፣ ሦስት ሌሊት ውሎ አድሮ እንደነበር ከአባቶች በቅብብሎሽ እየተነገረ ተያይዞ ከዘመናችን መድረሱ ነው።

በግራኝ ወረራ ጊዜ በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ የነበረው ቅርስና ታሪኳን የሚገልጠው ነገር ሁሉ ሲቃጠል የተወሰነ ጉዳት የደረሰበት ደወል ከዚህ ከፍታ ቦታ ላይ ሆኖ ሲደወል ያሰማ የነበረው ድምፅ ኮራ ማርያም ተደወለ እየተባለ በአካባቢው በነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ቀስቃሽ እንደነበር ይነገራል። ይህ ታላቅ ደወል በደረሰበት መጠነኛ ጉዳት አገልግሎት መስጠት ቢያቆምም ታሪካዊ ምስክርነቱን እንደ ያዘ በቤተ ክርስቲያኒቱ ዕቃ ቤት ይገኛል። ይህም የተቃጠሉ ብዙ ቅርሶች መኖራቸውን ከሚመሰክሩ ቅሪቶች አንዱ ነው። ከግራኝ ወረራ በኋላ እስከ ዓፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ድረስ በየጊዜው በተነሡ ነገሥታትና መሳፍንት ርዳታ እየተደረገላት የተጠናከረ አገልግሎት ስትሰጥ ኖራለች፤ ይሁን እንጂ ይህች ቀዳማዊት የሆነች ቤተ ክርስቲያን ለረጅም ዘመናት የቆየችው አስተማማኝ ባልሆነ የሳር ክዳን ተከድና ነበር ።

ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ የነበረው ቅርስና ታሪኳ ከጽላቱ በቀር በተለያዩ ጊዜያት በተነሡ ዐላውያን መጀመሪያ በግራኝ ከዚያም ወዲህ በፋሽሽት ኢጣሊያ ወረራ ተቃጥሎ ቢወድምም "ዝ ጽላት ዘመጽአ እም ኢየሩሳሌም" የሚል ጽሑፍ ያለበትን ጽላት ምስጋና ይድረሳቸውና መከራ ሲከሠት አባቶች ከዋሻ ወደ ዋሻ ይዘው እየዞሩ ከጉዳት በማትረፍ ለተተኪው ትውልድ እንድትደርስ አድርገዋል።

ለረጅም ዘመናት በሣር ክዳን ስታገለግል የኖረችውን ቤተ ክርስቲያን ያሠሯት ኑሯቸውን በአዲስ አበባ የአደረጉት እማሆይ ፋናይቱ የተባሉ የአካባቢው ተወላጅ ናቸው። እርሳቸውም ቆርቆሮ አስለብሰዋት ለብዙ ዓመታት ሲያገለግል ኖሯል። ቆርቆሮው በጊዜ ብዛት አርጅቶ በመፍረሱ በቅርብ ጊዜ የአካባቢውን ምእመናን እና በአዲስ አበባ የሚኖሩትን የአካባቢው ተወላጆች በማስተባበር በዘመናዊ ሁኔታ ታንጻለች። ይሁን እንጂ አስቀድሞ እንደተገለጸው የቤተ ክርስቲያኒቱ መሬት በመወሰዱ ቀድሞ ይሰጥ የነበረው አገልግሎት እየተዳከመ መጥቷል። እየተዳከመ የመጣው አገልግሎት የበለጠ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ክርስቲያኖች ለቤተ ክርስቲያኗ የቻሉትን ድጋፍ ቢያደርጉ በረከትን ያገኛሉ። አምላካችን እግዚአብሔር ከተቀደሰው ቦታ በረከት ይክፈለን። አሜን!!✤

# እግዚአብሔርን የሚያስወድስ፣ ሰውንም የሚቀድስ አገልግሎት

**ዲ/ን ማለደ ዋሲሁን**

በቤተ ክርስቲያን ማኅበራዊ አገልግሎት ተብሎ የሚወሰድ ቤተ ክርስቲያንን ከቤተሰቧ ባሻገር ከተለያዩ አካላት ጋር የሚያስተሳስር አገልግሎት አላት።ማኅበራዊ አገልግሎት ሲባል ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓለም ሳለች ሰው ለሆነ ሁሉ ወገን ሳትለይ ለችግሩ ሁሉ የምትደርስበት አገልግሎት ነው።ይህም ለሀገርና ለወገን የሚሰጥ የበጎ አድራጎት ተግባር ሲሆን ከአስተምህሮዋ የማይጣላ፣ አገልግሎቷንም የማያስተጓጉል ብርቱ ስምሪት የሚጠይቅ ነው።

ሰዎች በዚህ ዓለም ሲኖሩ ቢራቡ ቢጠሙ፣ ቢታረዙ፣ ቢሰደዱ፣ ቢታመሙ፣ ቢታሰሩ በራሳቸውና በቤተሰባቸው ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ለመቀነስ የምታደርገው ጥረት እግዚአብሔርን ያስደስታል፤ የታመመ ሰውንም ይፈውሳል። ሰዎች በመስረቅ፣ በጦርነት በማሳደድና በሌሎች ምክንያቶች በራሳቸውና በቤተሰባቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊደርስባቸው ይችላል።ችግር በገጠማቸው ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በተለያየ መንገድ ልትደርስላቸው ግዴታ አለባት።ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ማድረጓ አስተምህሮዋ እንዲገለጥ፣ ልጆቿ በአምላካቸው ላይ ያላቸው ትውክልት እንዲጸና ያደርጋል።

### የአስተምህሮ መሠረት

በክርስቲያኖች የሚፈጸም ማኅበራዊ አገልግሎት በፍቅር የሚፈጸም ነው።የቤተ ክርስቲያን ማኅበራዊ አገልግሎት ከነገረ ድኅነት ጋር የሚዛመድባቸው ዋነኛ መሠረቶች ፍቅርና ትሕትና ናቸው።ፍቅርና ትሕትና የመንፈስ ፍሬዎች በመሆናቸው (ገላ. ፭፥፳፪) ሥራውንም መንፈሳዊ ያደርገዋል።መንፈሳዊ አገልግሎት ሁሉ ዋጋ የሚያሰጥ ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ የሰውን ልጅ ሥጋ ተዋሕዶ ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር በተመላለሰበት ጊዜ ያስተማረው፣ የሠራው፣ ያሳየው ሁሉ ለሰው ልጆች በጎ ማድረግን የሚያስተምር ነው።ጌታችን ከሠራውም ሆነ ከተናገረው ለሰዎች መዳን የማይጠቅም አልነበረም። አርአያነቱን አሳይቶን ከሄደባቸው ጉዳዮች አንዱ ለሰዎች በጎ ማድረግ ነው። ሃይማኖታችን የሚገለጠው በክርስቲያናዊ ምግባር ነውና። አምላካችን የፍቅር አገልግሎት የሆነውን ማኅበራዊ አገልግሎት ዘወትር በመፈጸም እንድንኖር "ከታናናሾቹ ለአንዱ ያደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁ" ብሎናል (ማቴ.፲፥፵፪)። እንድንፈጽመው ማዘዝ ብቻ ሳይሆን በአርአያነት ሠርቶ አሳይቶናል።

ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን የምትረዳው እገሌ ከእገሌ ብላ ባለመለያየት መሆኑን "ለታናናሾች ሁሉ ያደረጋችሁት›› የሚለው ቃል አስረጅ ነው። ለክርስቲያኖች ብቻ፣ ለአይሁድ ብቻ ወይም ለእገሌ ብቻ አላለንም። ይህም ለሰው ሁሉ በጎ እንድናደርግ መፈለጉን፣ እኛም ለሌሎች መልካም ነገር ስናደርግ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን እንዲያውቋት እየሠራን መሆኑን መረዳት ይኖርብናል። ለእንደዚህ ዓይነቱ አገልግሎት ደጉ ሳምራዊ አብነት ሆኖ ይጠቀሳል።

ደጉ ሳምራዊ የፈጸመውን መልካም ተግባር ሌዋዊውና ካህኑ እንዲፈጽሙት ይጠበቅባቸው የነበረ ቢሆንም አላደረጉትም። ተደብድቦ የወደቀውን ሰው ማንሣት ሰው ከሆነ ሁሉ የሚጠበቅ ተግባር ነው።ሳምራዊውም የወደቀውን ሰው ማንነት ሳይመረምር ወድቆ ስላገኘው አዝኖ ማስታመሙ በክርስቶስ ዘንድ የፍቅር መገለጫ ሆኖ ተጠቅሷል።ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተራቡትን ማጥገቡ እርሱ ያደረገውን እንድንናገር ብቻ ሳይሆን እኛም ማድረግ እንደሚገባን የሚያስገነዝብ ነው። ደቀ መዛሙርቱን "ለሕዝቡ የሚበሉት ስጧቸው›› በማለት ማዘዙ (ሉቃ. ፱፥፲፫) ቤተ ክርስቲያን ለድኅነተ ሥጋም ለድኅነተ ነፍስም፣ በሥጋም፣ በነፍስም ለተራቡት የምትራራ እናት መሆኗን የሚያስገነዝብ ነው።

ቅዱሳን ሐዋርያትም በአገልግሎት ዘመናቸው አስተምረው በስሙ ለሰበሰቧቸው ክርስቲያኖች የፍቅርና የርኅራኄ ሥራ ይሠሩ ነበር።‹‹የዕለት የዕለቱን ምግብ ሲያካፍሉ ባልቴቶቻቸውን ቸል ይሉባቸው ነበርና›› እንደተባለ በጊዜው ተከሥቶ በነበረው የአስተዳደር ችግር አድልዎ ተፈጽሞባቸው ለነበሩ ወገኖች በመራራት ዲያቆናትን ሾመው የአሠራር ሥርዓት ዘርግተው ለዚያች ጉባኤ አባላት ይደርሱ ነበር (የሐዋ.፮፥፩)። ይህ ባይሆን በስሙ የተጠሩ በቃሉ የተሳቡ ምእመናን ጌታችን ‹‹እንደራባቸው ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ ባሰናብታቸውም በመንገድ ይደክማሉ››እንዳለ የሕይወት መዛል ይደርስባቸው ነበር (ማር.፰፥፫)።

ስለዚህ እንዲህ ያለው አገልግሎት ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ የመንፈሳዊ አገልግሎቱ አካል በመሆኑ በቸልታ የሚታለፍ አይደለም። ማኅበረ ካህናትም፣ ማኅበረ ምእመናንም የሚሳተፉበት የሕይወት አገልግሎት እንጂ ያለዋጋ የሚደረግ ተራ ዓለማዊ ተግባር አይደለም። ካህናትም ሆኑ ምእመናን በቤተ ክርስቲያን ታናናሾች ለሚባሉ በዚህ ዓለም ምግብና መጠለያን ላጡ፣ ጤና አጥተው በሥጋ ሕማም ለሚሰቃዩ፣ አልባሽ አጉራሽ አጥተው ለታረዙ፣ በጥፋት ምክንያት ወይም በግፍ በእስራት ላሉ ወገኖች ያለ አድልዎ፣ ያለመለየት መንፈስ ቅዱስ በሰጠን ጸጋ፣ በገንዘባችን፣ በሙያችን፣ በዕውቀታችን በፍቅር መርዳት ክርስቲያናዊ ግዴታችን ነው። በማኅበራዊ ሕይወት

የሚገለጠው የፍቅር አገልግሎት እያንዳንዱ እንደሥራው መጠን ከአምላኩ ዋጋውን የሚቀበልበት በመሆኑ ለካህናቱ ብቻ የሚተው አይደለም። ምእመናን በመተባበርም፣ በተናጠልም ሳይታክቱ የሚፈጽሙት ተግባር ጭምር ነው።ከእግዚአብሔር ሌላ የማንንም ፈቃድ የማይጠይቁበት ነፍስን ለማዳን የሚፈጸም ተግባር ነው።

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በታሪክ መዝገብ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አሐቲ፣ ቅድስት፣ ኵላዊት፣ ሐዋርያዊት ናት። ወንጌልን ስታስተምር ማኅበራዊ ሕይወትን፣ መልካም ዕሴትንና ሥርዓትን በማስተዋወቅ ምሳሌም፣ መሪም ሆና ኖራለች። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ ተቋማትን በማቋቋም፣ ማኅበረሰብን በልዩ ልዩ መንገድ በማስተካከል፣ ኢኮኖሚን በማልማት፣ ተፈጥሮንም በመጠበቅ፣ አገራችን ያላትን ለዓለም በማስተዋወቅ ድርሻዋ ከፍተኛ ነው።

ቤተ ክርስቲያን አገር እንድትጠበቅ፣ ሕዝብ በሰላም ውሎ እንዲገባ ‹‹ዕቀብ ሕዝባ ወሠራዊታ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ....››እያለች ትጸልያለች።ከዚህ የሚበልጥ የፍቅር መገለጫና አገልግሎት የለም።የሀገር ፍቅር ስሜትን ለመፍጠርም ሰንደቅ ዓላማዋ የተከበረ፣ ሠራዊቷ የማይደፈር፣ ታሪኳ የታወቀ እንዲሆን፣ ካህናትና ምእመናን በወረራ ጊዜ በዐርበኝነት ቆሞ ጠላት አጥፍቶ በነፃነት እንዲኖር ግንባር ቀደም ሚና ተጫውታለች። የሀገር መሪዎች በቅንነትና በጥበብ እንዲመሩ የዕውቀትን ብርሃን ስታበራ ኖራለች። የነገሥታት ልጆችን በአንድ ቦታ ሰብስባ ስታስተምር የኖረችው እነርሱን ከሠራቻቸው እነርሱ ደግሞ አገራቸውን እንደሚሠሩ በማመን ነው። ወንድማማች ነገሥታቱን አብርሀና አጽብሐን ያስተማራቸው አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን፣ ይኲኖ አምላክን አቡነ ኢየሱስ ሞዐ፣ ዐፄ ይስሐቅን፣ ቀዳማዊ ቴዎድሮስን እና ዘርዐ ያዕቆብን ያስተማራቸው አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ነበር። የነገሥታት ልጆች ከንግሥና በፊት በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ሲማሩ ማደጋቸው አስተሳሰባቸው ሁሉን አቀፍ እንዲሆንና ከወገንተኝነት የጸዱ እንዲሆኑ የራሱ አስተዋጽኦ ነበረው።

መሪዎቹን ማብቃት ብቻ ሳይሆን የሚሠሩበትንም ተቋም በመቅረጽ የቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነበር። የቤተ መንግሥቱን የአስተዳዳር ሥርዓት መመሪያና ደንቦችን የሚያረቁት፣ የሚያሥጡኑት፣ የሚያስከብሩት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ነበሩ።በቀድሞው ዘመን የሀገር መተዳደሪያ ሕጎችን የሚያወጡት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እንደነበሩ ፍትሐ ነገሥትንና ክብረ ነገሥትን አንብቦ መረዳት ይቻላል። ሕግን በመተርጎምም ዳኝነትን የሚሰጡ የፍትሐ ነገሥት ሊቃውንት ነበሩ። የሚያስፈጽሙትም ነገሥታት፣ መኳንንትና መሳፍንት ሲሆኑ የሚተረጕሙት ደግሞ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ነበሩ።

የቤተ ክርስቲያን ማኅበራዊ አገልግሎት በዚህ ብቻ የተገደበ አይደለም። ለነገሥታቱ ሥርዓተ መንግሥትን በማስተማር ፍትሕን እንዲጠነቅቁ ከማድረግ በተጨማሪ ለዘመናት ትምህርት ሚንስቴር ነበረች። ፊደልን፣ ቍጥርን፣ ንባብን በማስተማር አስፋፍታለች። የአብነት ትምህርት ቤቶችን በመክፈት ከሕፃንነት ጀምራ በማስተማር እስከ ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ድረስ ዘልቃለች። ለሥነ ጽሑፍ፣ ኪነ ሕንፃ፣ በሥነ ሥዕል፣ በሥነ ከዋክብትና ሌሎች ዕውቀቶች እንዲራቀቁ ስታደርግ ኖራለች።

## የሚበረታቱ ተግባራት

በዘመናችን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትውልዱን በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር በማነፅና ሰላም እንዲሰፍን ያበረከተችውና ወደፊትም የምታበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ከአበርክቶዋ መካከልም የቅርስ ጥበቃና የቱሪዝም መስሕቦችን በመጠበቅ ለአገልግሎት ዝግጁ ማድረግ፣ ደንን ማልማትና መጠበቅ፣ ዘመናዊ ትምህርት ቤቶችን በመክፈት ወጣቶች ዕውቀትን ከምግባር አጣምረው እንዲይዙ በማድረግ ላይ ትገኛለች። ከዚህ በተጨማሪም በየቦታው የሕፃናት ማሳደጊያዎችንና የአረጋውያን መርጃ ተቋማትን ማቋቋም፣ የውኃ እጥረት ያለባቸው የመጠጥ ውሃ እንዲያገኙ ማድረግ፣ በኤች አይቪ ኤድስና በሌሎች በሽታዎች ለተጎዱት የሚያስፈልጋቸውን ማቅረብ፣ ኮቪድ-፲፱ በተከሠተ ጊዜ ወደ አምላኳ በጸሎት ከማሳሰብ ጀምሮ ምእመናን ራሳቸውን እንዲከላከሉ ማስተማር፣ በቤተ ክርስቲያን ተቋማትና በአጥቢያዎች ክርስቲያኖች በሙያቸው እንዲያገለግሉ ማድረግ፣ ገዳማት የሚያከናውኗቸው የግብርና ልማቶች ጥቂቶች ናቸው።

## ቤተ ክርስቲያን ዛሬና ነገ

ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትንና ምግባርን ብቻ ሳይሆን ልጆቿ አእምሯቸውን በዕውቀት በማልማት ሀብት አፍርተው ራሳቸውንም አገራቸውንም እንዲጠቅሙ፣ ያልሠሩበትን እንዳይወስዱ፣ በሌሎች ውድቀት የሚደሰቱ ከንቱዎች እንዳይሆኑ ታስተምራለች። የራሳቸው ያልሆነውን እንዳይነኩ ብቻ ሳይሆን ተግተው በመሥራት ለሌሎች አርአያ እንዲሆኑም ታስተምራለች። ያለአድልዎ የሚሠራ፣ ታማኝና ሀገር ወዳድ ዜጋ ለማፍራት የትውልድን አእምሮ ማልማት ቤተ ክርስቲያን ከትናንት እስከ ዛሬ ስትፈጽመው የኖረችው ተግባር ነው። ቤተ ክርስቲያን ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት ለመስጠት ትናንት የገጠሟትን ፈተናዎች እንዴት እንዳለፈቻቸው በመመርመር ጥብዓትን ከቀደምቶቹ፣ አሠራርን ደግሞ ከዘመኑ በመማር ለነገ የሚሸጋገር ተግባር እንዲፈጽም ማዘጋጀት ይጠበቅባታል። የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ መማር የሚጠቅመውና ትናንትን መጥቀስ የሚገባውም ለዚህ ነው።

ልጆቿ በሚገባ ተምረው ሕግ አውጪ፣ ሕግ ተርጓሚና ሕግ አስፈጻሚ የሆነውን የመንግሥት አካል በማገዝ ልጆቿ አላግባብ ተጽዕኖ እንዳይደርስባቸው ማትጋት ለነገ የማይባል ተግባር ነው። ይህን ለመሥራት እያንዳንዱ ምእመን ዘንድ ለመድረስ የሚያስችል መዋቅር አላት። በነፍስ አባት የእያንዳንዱን ክርስቲያን ሕይወት ስለምትመራ ይህን መልካም አጋጣሚ ተጠቅማ ክርስቲያኖች ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን የደከሙትን ለማገዝና ለሌሎች አርአያ እንዲሆኑ ታስተምራለች። በቃለ ዐዋዲው በተቀመጠው መሠረት ካህናትና ምእመናን ተባብረው ከሠሩ ቤተ ክርስቲያን የገጠማትን ፈተና ተቋቁማ በማዕበል

ውስጥ ሳትናወጥ የምትጓዝ መርከብ መሆኗን በተግባር ትገልጣለች።

መንግሥት ፖሊሲ ሲያወጣ ልጆቿ እንዲሳተፉ ማስገንዘብ ያስፈልጋል። ቤተ ክርስቲያን እንደ ተቋም የሚጠበቅባትን ተሳትፎ በማሳደግ በትምህርት፣ በጤናና መሰል ጉዳዮች እንዲሳተፉ ማድረግ ጠቀሜታው በቃላት ተዘርዝሮ የሚፈጸም አይደለም። ቤተ ክህነት ዘመኑን የዋጀ የአሠራር ሥርዐት በመዘርጋት አፈጻጸሟ እንዲዘምን በማድረግ ተቋማዊ ምሳሌነትና መልካም ስም እንዲኖራት ጠንክራ መሥራት ጊዜ የማይሰጠው ተግባር ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከትናንት በተሻለ ዛሬም ከፍተኛ የማኅበራዊ አገልግሎት ኃላፊነት ይጠበቅባታል።ስለዚህም እስከ አሁኑ በተሻለ ተቋማዊ አደረጃጀት፣ በጠነከረ መንፈሳዊ ትጋትና በክርስቲያናዊ ፍቅር፣ በክርስቲያናዊ ተጋድሎና ጥብዓት አገልግሎቷን ማጠናከር ይገባታል።ለዚህም አስቸኳይ ምላሽ ለሚያስፈልጋቸው ለሚከተሉት አንገብጋቢ ጉዳዮች አፋጣኝ ምላሽ መስጠት ይኖርባታል።

**፩ኛ. እየተባባሱ የመጡ አገራዊ ችግሮች፡-** ያለንበት ዘመን ሀገራችን ውስብስብ ማኅበራዊ ችግሮችን የተጋፈጠችበት ነው።በዘረኝነት፣ በፖለቲካና በሃይማኖት ልዩነት ምክንያት ግጭቶችና ጦርነቶች ተከሥተዋል። በዚህም ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት፣ ልጆቻቸውን ያጡ አረጋውያን ብዙ ናቸው።በርካቶች እየሞቱ ቀባሪ አጥተው ሜዳ ላይ ውለው እያደሩ ነው። የሟች ቤተሰቦች አጽናኝና አረጋጊ ይሻሉ።ከዚህ በተጨማሪም በተፈጥሮ አደጋ በቅጽበት ሰዎች ሕይወታቸውንና ንብረታቸውን አጥተው ሲቸገሩ እያየን ነው። መጠለያ፣ የዕለት ምግብና የዓመት ልብስ አጥተው ይቸገራሉ።ፍትሕ በማጣት በእስር የሚጉላሉና አገር ለቀው የሚሰደዱም ብዙዎች ናቸው።

**፪ኛ. ሰባክያነ ወንጌል የሞራል ልዕልናን ማስጠበቅ፡-** አሁን በአገራችን የሚታየው ከመቶ ዓመታት በፊት ከነበረው በእጅጉ ይለያል። ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ተፈራርቀው እጅግ የተራራቀ ፍላጎት ያለው ትውልድ ተፈጥሯል። የልቡና ስብራት ደርሶባቸው የተጎዱ በርካታ የማኅበረሰብ ክፍሎች ካሉበት ዘመን ላይ ደርሰናል። የተለያዩ የእምነት ድርጅቶችም ነፃነትን ተገን አድርገው ሰዎችን በግብዝነት ወደየ ቤተ እምነቶቻቸው ለመሳብ በጎ አድራጎት የሚመስሉ ተግባራትን ለመፈጸም ይጥራሉ። ይህ ድርጊት ሥጋዊ ፉክክር ወይም ውድድር ስለሚመስል ሰይጣን ሰዎችን ለማጥመድ የዘረጋው ሌላ ፈተና ነው።ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የዜጎችን ችግር የሚያስወግዱ ዘርፈ ብዙ ማኅበራዊ አገልግሎት መስጫዎችን መዘርጋት ይጠበቅባታል። መናፍቃንና ኢአማንያን በሰዎች ችግር ዓላማዎቻቸውን ማሳካት እንደሚፈልጉ ቤተ ክርስቲያን መረዳት ይገባታል።

**፫ኛ. ትውልድ የሚጠብቅባትን መለየት፡-** የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በርካታ ቊጥር ያለው አማኝ ብቻ ሳይሆን ከምእመናን የምትደርስበት የተደራጀ መዋቅር አላት።ይህም ትጉና ሀገር ወዳድ ኢትዮጵዊ እንዲፈጠር አድርጓል። በመሆኑም ለመንግሥትም ሆነ የአገራችን ዜጎች ለገጠማቸው ችግር መፍትሔ መስጠት ይገባታል። ለተከሠተ ችገር ምላሽ አለመስጠት ቅቡልነትን ያሳጣልና።

**፬ኛ/ ክርስቲያኖች ለችግር የተጋለጡበት ጊዜ ነው፡-** በዘመናችን በርካታ የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ተነሥተዋል።የተለያየ የፖለቲካ ትርክት ይዘው ክርስቲያኖችን የሚያሳድዱበት አጋጣሚ በዝቷል። አብያተ ክርስቲያናት ይቃጠላሉ፤ የምእመናን ሀብት ንብረታቸው ይወድማል፤ ሕይወታቸው ይቀጠፋል። ድርጊቱ ከፍተኛ ማኅበራዊ ቀውስ የሚያስከትል በመሆኑ አፋጣኝ ምላሽ የሚፈልግ ነው። ስለሆነም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በምእመኖቿ ላይ ለሚደርስ ጉዳት ፈጥና መድረስ መንፈሳዊ ግዴታዋ ነው።

## ከወጣቱ ትውልድ የሚጠበቅ ኃላፊነት

አስቀድመን እንደጠቀስነው አሁንም ሆነ ወደፊት ኦርቶዶክሳዊው ወጣት ትውልድ በግልም፣ በመደራጀትም መወጣት የሚገባው ማኅበራዊ ኃላፊነት መኖሩን መረዳት ይኖርበታል። አገልግሎቱም መሥዋዕትነትን የሚጠይቅ በመሆኑ ስለቅድስት ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ርትዕት ሃይማኖቱ እንደቀደሙ አባቶቹ ለመሠዋዕትነት መዘጋጀት ይጠበቅበታል። ከሙስና የጸዳ፣ ግብረ ገብነት ያለው፣ በሥራ የማይታክት ዜጋ ለመሆን ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረውን መስማት ይኖርበታል። ኢትዮጵያ ሰላሟ የተጠበቀ፣ አንድነቷ የጸና እንዲሆን ከሚሠሩ አካላት ጋር ተባብሮ መሥራት፣ ከሌሎች ቤተ እምነቶች ጋር በመከባባርና በመተባበር ሀገር ለመገንባት ዝግጁ መሆን ይገባል። ወጣቱ አገራችን ብቁ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲኖሯት፣ በቴክኖሎጂና በፈጠራ ሥራ ቀዳሚ እንድትሆን ሳይታክት በመሥራትና በመመራመር አገሩን ማስከበር ይኖርበታል።

ወጣቱ በወሳኝ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በጋራና በተናጠል የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ይገባዋል። የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ እና ቅርስ ለመጠበቅ፣ አጥንቶ ለማስተዋወቅ፣ ሳይታክት መሥራት ይጠበቅበታል። አሳዳጊ ያጡ ሕፃናትን፣ ጧሪ የሌላቸው አረጋውያንን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ የአእምሮ ሕሙማንን የሚደግፉ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ለማቋቋም አጥንቶ ማቅረብ፣ አባቶች የሚያዝዙትን በቅንነት መሥራት ከአገር ተረካቢው ወጣት የሚጠበቅ መልካም ተግባር ነው። የአረጋውያንን ልብስ ማጠብና የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ በማቅረብ መንከባከብ ከክርስቲያን ወጣት የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው። እንዲህ ያለው ተግባር በእግዚአብሔርም፣ በመሪዎችና በዜጎችም ፊት ሞገስ ያስገኛል። ተሰሚነት ያላቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች እንዲበዙ ከካህናትና ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ጋር ተባብሮ መሥራት ይኖርባቸዋል። ቤተ ክርስቲያን ነገ መስጠት የሚገባትን አገልግሎት የተሳካ ለማድረግ እግዚአብሔርም፣ ሰውም የሚወደውን የማኅበራዊ አገልግሎት ድርሻዋን ለመወጣት ወጣቱ መፍጠን፣ ቀልጣፋ መሆን፣ መትጋት፣ መጠበብ ይጠበቅበታል።✥

# በአንድ ላይ ስንጓዝ ከዓይኔ ተሠወረ

ዲ/ን አሻግሬ አምጤ

የእመቤታችን የአሥራት አገር በተባለችው በኢትጵያ የማይሰማ ታሪክ የለም። ከሐምሌ ፲፱፻፹፯ እስከ ፲፱፻፺ ዓ.ም መጨረሻ በድሮው ሞጣ አውራጃ፣ በቢቡኝ ወረዳ የአንደኛ ደረጃ መምህር ሆኜ ባገለገልኩባቸው ዓመታት አገሬንም ቤተ ክርስቲያኔንም ለማወቅ ዓይኔ የተገለጠበት ነበር ማለት እችላለሁ። በአካባቢው ይገጥመኝ የነበረውን አስቸጋሪ ነገር ሁሉ ያቀሉልኝ የነበሩት ቄስ እንግዳ ይሁኔ ነበሩ።

ነበሩ የምለው ያለምክንያት አይደለም። ቦታውን በለቀቅሁ በ፴ ቀኑ መስከረም ወር መጨረሻ በወርኀ ጽጌ ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ዋሸራ ማርያም ደርሰው ሲመለሱ ጉማራ የሚባለው ወንዝ ወስዷቸው ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ነው። መጠሪያቸው ስለሆነ እንጂ ውኃው በጣም ኀድሎ እንደነበር ድርጊቱ በተፈጸመበት ዕለት አብረዋቸው የነበሩ ሰው የነገሯቸው መሆኑን ባለቤታቸው አጫውተውኛል። አካሄዳቸው ከመስከረም ፳፯ ጀምሮ በገዳሙ የምትገኘው ቅዱስ ሉቃስ የሣላት የምትባለውን የእመቤታችን ሥዕል ለማየት ነበር። የእግዚአብሔርን ሥራ ከማደንቅበት ነገር አንዱም ይህ ነው። ካለ እርሳቸው ቦታው ለእኔ ምን እንደሚሆን የሚያውቀው እግዚአብሔር አስቀድሞ መኖሪያ ቦታየን ቀይሮ እርሳቸውን ወደ ራሱ ጠራቸው።

ቄስ እንግዳ ብዙ መንፈሳዊ ጉዳዮችን ያጫውቱኝ የነበረ ቢሆንም ከብዙዎች መካከል አንዱን ሳስታውሰው እኖራለሁ። እሑድ እሑድ እኔና እሳቸው እስከ ስድስትም፣ እስከ ሰባትም ሰዓት ብቻችንን ከቤተ ክርስቲያኑ አጸድ ውስጥ እንቆይ ነበር።ጨዋታችን ሳያልቅ ይበቃናል ቀሪውን ሳምንት እንጫወተዋለን ብለው በእሳቸው ቤት በኩል ሄጄ አብረን ምሳ ከበላን በኋላ ተጨዋውተን ይሸኙኛል።ዐልፎ፣ ዐልፎም በ፲፰ኛው ክፍለ ዘመን ድል ሞገሳ በምትባል ሴት እንደታነፀ ከሚነገርለት ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ቆይተን እኔም ወደ ቤቴ የሚያደርሰኝን መንገድ፣ እሳቸውም ወደ ቤታቸው የሚወስዳሳቸውን ቁልቁለት ይዘው ይጓዛሉ።

ከቤተ ክርስቲያን እስከ ቤቴ ድረስ ለሚፈጅብኝ ከአንድ ሰዓት ያላነሰ የሚፈጀው መንገድ ስንቅ የሚሆነኝ ከእርሳቸው ጋር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስንጫወት የቆየነው ቃለ እግዚአብሔር ነበር። እኔ ካለአቅሜ ለመኖር ፈልጌ አንድ ጉዳይ ሳማክራቸው እሳቸው ደግሞ ቀስ እያልሁ እንዳድግ ሲመክሩኝ ሳናውቀው አንድ ታሪክ ጠቅሰው ስንጫወት ቀኑ ይጋመሳል።

በአንድ ወቅት አጫውተውኝ በአእምሮዬ ታትሞ የቀረ አንድ አስገራሚ ታሪክ አለ። እንዴት እንደ ጀመሩት ትዝ ባይለኝም እንዲህ በማለት ትርካቸውን ቀጠሉ። "ከዕለታት አንድ ቀን እርሻ ውየ በጣም ደክሞኝ ወደ ቤቴ ስመለስ የተበጣጠሰ ልብስ የለበሱ፣ መናጢ ድሃ የመሰሉ ሰው ከደጅ ተቀምጠው አገኘሁ። እኔን እንዳዩኝ ከመቀመጫቸው ሊነሡ ሲሞክሩ "አይገባም በእግዜር" አልሁና የተሸከምሁትን ሞፈርና ቀንበር አወረድሁ። ባለቤቴንም ምነው የእግዚአብሔር እንግዳ ከደጅ ተቀመጠ? ከቤት ገብተው ቢቆዩ ምን አለበት? በማለት ተናገርኳኋት።እርሷም "እኔስ ይግቡ ብያቸው ነበር፤ ወንድ በሌለበት ቤት አልገባም አሉኝ እንጂ" በማለት መለሰችልኝ።

ሰውዬው ልብሳቸው ከላያቸው ላይ የረገፈ፣ ጥፍራቸው በጣም ያደገ፣ በሰውነታቸው ላይ ቅማል የሚሄድባቸው ነበሩ። ከተወለድኩ እንደ እርሳቸው ያለ ሰው አይቼ አላውቅም። ድሃ መሆናቸውን እንዲህ ነው ብሎ ለመግለጥ ይከብዳል። ግን ደግሞ ወዘናቸውና የፊታቸው ደስተኛ መሆን ለሚመለከታቸው ያስገርማል። ፍጹም ችግረኛ አይመስሉም። እንዲህ ዓይነት ሰው ከየት እንደመጡ ለመገመት ተቸግሬ የእግዚአብሔርን ሥራ እያደነቅሁ ከቤት እንግባ ማለትን እስከ መዘንጋት ደርሼ ነበር። ቀና ብለው ሰው ለማየት አይደፍሩም። ቃለ እግዚአብሔርን ማወቅ ቀርቶ መንፈሳዊነትን እንኳን ግብሩን ስሙንም የሚያውቁ አይመስሉም። ያነጋግሩኝ የነበረው መሬት፣ መሬት እየተመለከቱ ነበር። ሁኔታቸው እያስገረመኝ ይበሉ ይነሡና ከቤት እንግባ አልኳቸው። እርሳቸውም ከተቀመጡበት ተነሥተው ተከትለውኝ ከቤት ሲገቡ ቤት ለእምቦሳ አሉ። እኔና ባለቤቴም እንቦሳ ይሰሩ ብለን መልሰንላቸው። ከዚያም ከመደብ ላይ ተነጥፎ ከነበረ የበግ አጎዛ ላይ እኔና እርሳቸው ጎን ለጎን ተቀመጥን።

ራት እስከሚቀርብ ቆሎ ነገር ቀርቦልን እየቆረጠምን ስንጨዋወት ቆይተን የእግር ውኃ በመቅረቡ የእንግዳውን እግር ለማጠብ ውኃና ገበታ ይዤ ቀረብ አልኩ። ከፊታቸው በርከክ ስል እግሬን ካህን አያጥበኝም። የክርስቶስን ሥጋና ደም በሚያቀብሉበት እጅዎ መታጠብ አልችልም? በማለት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ። እኔም ካህን መሆኔን ባለቤቴ የነገረቻቸው ስለመሰለኝ የተናገሩትን ትኩረት አልሰጠሁትም ነበር። ብለምናቸው ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ባለቤቴ አጠበቻቸው። ሁል ጊዜ ከቤታችን እንግዳ ሲመጣ ሁለትና ከዚያ በላይ ከሆኑ እያንዳንዳቸውን ተከፋፍለን፣ አንድ ከሆነም አንድ እግሩን እኔ፣ ሌላ እግሩን እርሷ እናጥብ ነበር። በዚያ ልማድ ነበር እንግዳውን ለማጠብ የተነሣሁት። አልታጠብም ቢሉኝም እኔም አጠብኳቸው፣ እርሷም አጠበቻቸው በረከቱ የሁላችንም በመሆኑ አልታጠብም በማለታቸው ለእርሷ ለቅቄ ከቦታዬ ተቀመጥሁ። ባለቤቴ ትሁንም እግራቸውን አጠበቻቸው። ከዚያም እራት ቀርቦ ተመግበን እኔና እንግዳው ከቆጥ ላይ ስንተኛ፣ ትሁን ልጆችን ይዛ ዐልጋ ላይ ተኛች።

ሰውየው እኔን እንቅልፍ የወሰደኝ ሲመስላቸው የተወሰነ ጊዜ ጠብቀው ጸሎት ጀመሩ። ጸሎት ያደርጉ የነበረው በአማርኛ ነበር። በዚህም ግእዝ የማይችሉ ምእመን መሆናቸውን ተረዳሁ። ምንም ሳይተኙ ጸሎት እያደረጉ ነጋ።እኔም እንቅልፍ የወሰደኝ መስየ ዐልፎ ዐልፎ እየተገላበጥኩ የሚያደርጉትን ስከታተልና ሳደምጥ ዶሮ ደጋግሞ ጮኸ። እኔም እንዳስለመድሁት ኩራዝ

አብርቼ ዳዊቴን ደግሜ ስጨርስ የሰውየውን እርቃን ለመሸፈን የሚሆን ልብስ ለመስጠት አሰብሁ፡፡

**እንዲህ ዓይነት ሰው ከየት እንደመጡ ለመገመት ተቸግሬ የእግዚአብሔርን ሥራ እያደነቅሁ ከቤት እንግባ ማለትን እስከ መዘንጋት ደርሼ ነበር፡፡ ቀና ብለው ሰው ለማየት አይደፍሩም፡፡**

በየዓመቱ የደብረ ዘይት የንስሓ ልጆቼን ሰብስቤ ቤተ ክርስቲያን አስተምራቸዋለሁ፡፡ እነርሱም በዕለቱ ባዶ እጃችንን የአባታችንን ፊት አናይም ብለው የሚችሉትን ብር ይዘው ይመጣሉ፡፡ ልጆቼ የሚያመጡትን ብር የሚሰበስቡ ሰዎች ተመርጠው ገንዘቡ መግዛት የሚችለውን ሁለትም፣ ሦስትም ነጠላ ገዝቼ አስቀምጥና ባዕድ ዘመድ ሳልመርጥ በድብቅ ለታረዘ ሰው እሰጠው ነበር፡፡ በአንድ የደብረ ዘይት ዕለት በተሰበሰበው ገንዘብ ከተገዙት ነጠላዎች መካከል ለድሃ ሰጥቻቸው የተረፈች አንድ ነጠላ ከቤት ስለነበረች በጣም ተደሰትሁና ትሁንን ጠርቼ በምልክት ስጠይቃት እሷም አስባው ኖሮ እኔም አስቤዋለሁ አባ አለችኝ፡፡ እኔ ያሰብሁትን እሷ በማሰቧ ተደንቄ እንድታቀርበው ነገርኋትና ካስቀመጠችበት አውጥታ ሰጠችኝ፡፡

ነጠላውን በሁለት እጄ ይዤ ለብሰው እርቃናቸውን እንዲሸፍኑበት ልሰጣቸው ቀረብ ስል እንደማይቀበሉ ነገሩኝ፡፡ ብለምናቸው እንቢ አሉ፡፡ ካልተቀበሉኝ ብዬ ግድ ስላቸው እሳቸውም አልቀበልም ብለው በአሳባቸው ጠኑ፡፡በመጨረሻም እኔን የሚያሸንፉበት ምክንያት አገኙ፡፡ በቤቱ የታረዘ ሰው ስላለ ለእርሱ ይሁን አሉኝ፡፡ንግግራቸው አልገባኝ ብሎ ድንግር እንዳለኝ ልጆቼ እንደሆነ ከአንድም፣ ሁለት፣ ሦስት ልብስ አላቸው፡፡ የታረዘ ሰው በቤታችን ውስጥ ስለሌለ እባክዎ ይቀበሉኝ ብላቸው በጄ ስላላሉኝ እያዘንሁ እንድታስቀምጠው ለባለቤቴ ሰጠኋት፡፡ እሷም እንደኔው እያዘነች አስቀመጠችው፡፡

ሰውየውን ለመሸኘት ከቤት ወጥተን ከቤታችን በላይ ያለውን አቀበት እየተጫወትን ወጣነው፡፡ ዋናው ጎዳና ከቤታችን በላይ በምዕራብ በኩል በመሆኑ ከመንገድ ስንደርስ ደኅና ይሁኑ አባ ብዬ እሳቸውም መርቀው ልንለያይ ስንል አንድ ሰው ጠራኝና የጠየቀኝን መልሼ ዘወር ስል ሰውየው ከፊቴ የሉም፡፡ወደፊት ብሮጥ፣ ወደ ኋላ ብመለስ ላገኛቸው አልቻልሁም፡፡አሁን የት ገቡ ይባላል እያልኩ ወዲያ ወዲህ እንቀሳቀስ የነበረው በፍርሃት እየተንቀጠቀጥኩ ነበር፡፡ በዕለቱ የተሰማኝን ድንጋጤ በቃል ለመግለጥ አይቻለኝም፡፡

እግዚአብሔር አላዋቂውን ሊቀሥፈኝ ይሆን? በምን አቅሜ፣ በምንስ መንፈሳዊ ብቃቴ የሚሠወር ሰው አሳደርሁ እያልሁ በፍርሃትና በጭንቀት ወደ ቤት ተመልሼ የሆነውን ለትሁን ስነግራት እሷም ደነገጠች፡፡በድንጋጤ ውስጥ በሰነበትንበት አንድ ዕለት ሩቅ ቦታ ይኖር የነበረ የሩቅ ዘመዳችን ከቤታችን መጣ፡፡ ልብሱ በሰውነቱ ላይ ረግፎ ሳየው በጣም ደነገጥሁ፡፡ለካ ምንም የሌላቸው ድሃ መስለው ከቤታችን በእንግድነት ያደሩት የእግዚአብሔር ሰው ለቤቱ ሰው ይስጡልኝ ያሉኝ ለአንተ ኖሯል በማለት ሰጠነው፡፡

እግዚአሔር አድሎኝ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "እንግዶችን መቀበልን አትዘንጉ፤ አንዳንዶች ሳያውቁት መላእክትን እስከ መቀበል ደርሰዋልና" በማለት ያስተማረው አምላካዊ ቃል ቢፈጸምልኝ እያልኩ አስባለሁ (ዕብ.፲፫፣፩)፡፡ "ሐዋርያው እንግዶችን ከቤታቸው የሚያሳድሩ ሰዎች የሚያገኙትን መንፈሳዊ በረከት የገለጠው በተግባር ተርጕመነው እንድንጠቀም

ነው ልጄ:: እንግዳ መቀበልን ከአጎቱ እያየ ያደገው ጻድቁ ሎጥ መላእክትን እንግድነት በመቀበሉ በሰዶምና በገሞራ ሰዎች ላይ የወረደባቸው የመከራ እሳት አላገኘውም"::

"እንግዳ በመቀበሉ ሊደርስበት የሚችለውን መከራ እያወቀ መልካም ማድረግን በማስቀደሙም ሰዎችን አውጥተህ ስጠን ባሉት ጊዜ ብትፈልጉ ለወንድ ያልደረሱ ሴት ልጆች አሉኝ:: እነርሱን ወስዳችሁ እንደፈለጋችሁ አድርጓቸው እንጂ የእግዚአብሔር እንግዳ ብለው ከቤቴ የተጠለሉትንስ አውጥቼ አልሰጣችሁም በማለት መልሶላቸዋል:: በክፉታቸው ቢጸኑ እንኳ የፈለጋችሁትን አድርጉብኝ እንጂ እነርሱን ዐሳልፌ አልሰጣችሁም ያላቸውን ክርስቲያኖች እያሰብን እንግዶችን እንቀበላለን አሉኝ:: ለቀጣይ ትውልድ ምሳሌ መሆኑን ያረጋገጡት መላእክትም እምነቱ የሚጸናበትን፣ የኋላ ትውልድም እንግድነት በመቀበሉ እግዚአብሔር ለመከራ አሳልፎ እንደማይሰጠው አስተማሪ የሆነ ተግባር ፈጸሙ:: አካባቢውን በድኝ እሳት አቃጥለው እርሱንና ልጆቹን ይዘው ወጡ:: እንግዳ መቀበል የሚያስገኘው በቍዔት እንዴት ዓይነት እንደሆነም ተግባራዊ ትምህርት እንድናገኝ አደረጉ (ዘፍ.፲፱፥፩) በማለት አሳባቸውን አጠቃለሉ::

ቄስ እንግዳ መንፈሳዊ ጨዋታ ከጀመሩ ደከመኝ ቀርቶ ሰው ይደክመዋል አይሉም ነበር:: ሥራ አለብኝ፣ ጉዳዬ ሊቀር ነው፣ ሌላም ምክንያት የማይሰጡ ሰው ነበሩ:: እርሳቸው በቃል ያስተማሩትን ባለቤታቸው በተግባር ይተረጉሙት ነበር:: ከዚህ ታሪክ ጋር የሚመሳሰል አንድ ቄስ ያጫወቱኝን ልጨምርና ጽሑፌን ላጠቃልል:: ታሪኩ እንዲህ ነው:: በዘመናዊ ትምህርት ገፍቶ እስከ ዩኒቨርሲቲ የተማረ ወጣት ነበር:: በማኅበረ ቅዱሳን የተተኪ መምህራን ሥልጠና በተደጋጋሚ ጊዜ መሳተፉን ቄሱ ነግረውኛል:: ኀበዝ የሚባል ተማሪ እንዳልነበረም ጨምረው አውግተውኛል:: ከዩኒቨርሲቲ ተመርቆ መሠረተ ልማት ከሌለበት ሩቅ ወረዳ ተመድቦ ለሥራ ወደዚያ ይሔዳል:: በዚያም የመንግሥት ሠራተኛ ሆኖ ሲያገለግል ይቆያል:: ከዕለታት አንድ ቀን ምሽት ላይ በቀበሌው የሚገኘው ደብር ገበዝ ወደ ቤቱ ይመጣሉ::

ገበዙ ባለቤታቸው ዐርፈው ብቻቸውን የሚኖሩ ነበሩ አሉ:: ወደ መንግሥት ሠራተኛው ቤት የሄዱት ምሽት ላይ ስለነበር የመንግሥት ሠራተኛው እንግዳ ስለመጣለት ደስ ብሎት ምግብ ማዘጋጀት ይጀምራል:: ካህኑም ልጄ መሽቷል ቶሎ ራት አቅርብ ይሉታል:: ወጣቱም እሺ ብሎ የሠራውን ምግብ ያቀርባል:: የቤተ ክርስቲያኑ ገበዝም ወጣቱን የመንግሥት ሠራተኛ ከቤታቸው እንደሄደ ሁሉ በደንብ ብላ ይሉታል:: ደግመው በደንብ እንዲበላ ይነግሩታል:: ለሦስተኛ ጊዜ ይነግሩትና እሱም የሚችለውን ያህል በደንብ ተመገበ:: ከዚያም ማዕዱ ተነሥቶ ካህኑና የመንግሥት ሠራተኛው ለጸሎት ቆሙ:: ከጸሎት በኋላ ተከተለኝ ብለውት እርሳቸው ከፊት፣ ከፊት፣ እሱ ከኋላ ከኋላ ተከታትለው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ተጓዙ:: ከቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ከገቡ በኋላ የተደረገውንና ከዚያም በኋላ እስከ ተወሰኑ ወራት የተፈጸመውን አያስታውስም::

ጥቂት ቆይቶ ጉባኤ ቤት ገብቶ ብሉያትንና ሐዲሳትን ተማረ:: ከዚያም በአገራችን ከሚገኙ ታላላቅ ገዳማት በአንዱ መንኵሰው አባ ተባሉ:: የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሳሉ በተደጋጋሚ ጊዜ ያሠለጠኗቸው ቄስ ጉባኤ አዘጋጅተው ኖሮ ሰባኬ ወንጌል አጥተው ሲጨነቁ ጭንቀታቸውን የሰማች አንዲት ሴት ትደውልላቸዋለች:: ቄሱንም እገሌን ታስታውሰዋለህ ወይ? ትላቸዋለች:: እርሳቸውም ምግባሩ ደግ ቢሆንም ያንን ሰነፍ ዲያቆን እንዴት እረሳዋለሁ ብለው ይመልሱላታል:: እሷም የሚገርም ሰባኪ ሆኗል አሉ፤ እስቲ ስልኩን ፈልጌ ልላክልህ:: ደውልለትና በጉባኤው ያስተምር ትላቸዋለች:: ቄሱም አንቺ ደግሞ የማታውቂ ይመስል እንዴት ሊቃውንት ከበዙበት ቦታ ግእዝ መጥቀስ የማይችል ዲያቆን መምህር ብዬ እጋብዛለሁ ይሏታል:: እሷም በአቋሟ ትጸናና ሞክረኸው ካልሆነ ይቀራል ትላቸዋለች:: በሕዝብ ጉባኤ የሚያስተምር መምህር የሚፈልጉት ቄስም በተደጋጋሚ ያሠለጠኑት የሚያስገርም መምህር ሆኗል የተባለውን ዲያቆን አንድም ለመፈተን፣ ሁለትም መምህር በማጣታቸው አገኘሁ ለማለት ያህል ሊጋብዟቸው ይስማሙና ስልካቸውን ልትልክላቸው ይስማማሉ::

ሴቲቱም የቀድሞውን ዲያቆን፣ የአሁኑን መነኰሴ ስልክ አፈላልጋ ትልክላቸዋለች:: እርሳቸውም ደውለው ማንነታቸውን ሲነግሯቸው የድሮ መምህራቸው ድምፅ ነበር:: ሰላምታ ሰጥተው የሚጠይቋቸውን አዳምጠው አይቻለኝም እንጂ ከተቻለኝ እታዘዛለሁ:: ግን ከዚያ ከሊቃውንት ቦታ እንዴት አድርጌ ቆሜ አስተማራለሁ ይላሉ:: ቄሱም የምትችለውን አድርግ ብለዋቸው እሳቸውም ተስማምተው ስልኩን ይዘጋሉ:: በተቃጠሩበት ዕለት ከተባለው ቦታ ይሄዳሉ:: ጋባዡም ጥንት በሚያውቋቸው ተማሪ መለወጥ ተገርመው ተቀብለው ወደ ተዘጋጀላቸው ማረፊያ ቦታ ይወስዷቸዋል:: የጉባኤ ሰዓት ሲደርስ አብረው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደው ያስተምራሉ:: ተማሪ በነበሩበት ወቅት የተፈጸመውን አስታውሰው "በሰማሁት ነገር ከመደነቁ የተነሣ ይህን ሰው አውቀው ነበር እንዴ" ብየ ራሴን ጠይቄያለሁ አሉኝ:: ከሊቃውንት መጻሕፍት ሲጠቅስ ያስገርማል:: እሱ የማይሆንለት ማሕሌት እንጂ ብሉያት፣ ሐዲሳት ይሁን ሊቃውንት ሲያመሠጥረው ያስገርምሃል:: ከጉባኤ በኋላ እንዴት ሊለወጥ እንደቻለ ስጠይቀው የሆነውን ሁሉ ነገረኝ::

"መንፈሳዊ መሆን አቅቶኝ የሰው መንፈሳዊ ተጋድሎ እና የእግዚአብሔርን ምርጫ እያሰብኩ እደነቃለሁ:: ሌላ ሰው ቢነግረኝ አላምንም ነበር፤ ግን አምላካችን እግዚአብሔር የማውቀውንና በዕውቀት እበልጠዋለሁ የምለውን ሰው ለክብር አበቃው:: እግዚአብሔር ማንን እንደሚመርጥ የሚያውቀው ራሱ እንጂ እኛ አይደለንም" በማለት ጨምረው ነገሩኝ:: አሁን ያሉበትን ሁኔታ ራስህ ዓይተህ የምትፈርደው በመሆኑ አልነግርህም በማለት አሳባቸውን አጠቃለሉ:: እኔም የዘመናችን ትውልድ ምክንያት እንዳያበዛ እንማርባቸው ዘንድ እግዚአብሔር የሚፈጽማቸውን ተአምራት አድንቄ ሌሎች ይማሩበት ዘንድ እንዲህ አቀረብኩት:: አንብበን እንድንጠቀም የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የእመቤታችን አማላጅነት፣ የቅዱሳን ሁሉ ተራዳኢነት አይለየን:: አሜን!!✠

## በዝግጅት ክፍሉ

የተከበራችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ማስነበባችን ይታወቃል። ቀጣዩን ደግሞ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።



አባ ፍቅረ ማርያም

**ሐመር መጽሔት፡- በጽዋ ማኅበር ውስጥ ይቀሥፋል የሚል ምእመናንን ከጽዋ ማኅበር ሱታፌ የሚያርቅ የማስፈራሪያ አሳብ ይነገራል። ለዚህ ጉዳይ ቤተ ክርስቲያን ያላት አስተምህሮ ምን ይላል?**

**አባ ፍቅረ ማርያም፡-** ሰዎች አስቀድመው እግዚአብሔርን ቀሣፊ አድርገው ከሚረዱት ይልቅ መሓሪነቱን መረዳት ቢችሉ ይጠቀማሉ። እግዚአብሔር ዕድሜ ለንስሐ ሰጥቶ አልመለስ ያሉትን ይቀጣል። እግዚአብሔር ከሃይማኖት ወጥተው ለጣዖት ሲሰግዱ፣ ሕጉን ሲተላለፉ፣ ግብረ ሰዶምን ሲፈጽሙ፣ ብዙ ጊዜ ከታገሠ በኋላ የቀጣበት ዘመን ነበር። ዛሬም ቢሆን ከመጠን አልፈን ስንገኝ እግዚአብሔር ዳኝነቱን ይገልጽና ሌላው ትውልድም ይማርበት ዘንድ መቅሠፍት ያመጣል። ይሁን እንጂ ከላይ የተከናወኑ ተግባራት በረከትን የሚያሰጡ እንጂ የሚያስቀስፉ አይደሉም።

ይልቁንም እግዚአብሔር አምላካችን "ሰንበቴን ቢጠብቁ፣ ደስ የሚያሰኘኝንም ነገር ቢመርጡ፣ በቃል ኪዳኔም ጸንተው ቢኖሩ፣ በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ ስም የሚያስጠራ ቦታን እሰጣቸዋለሁ። የማይጠፋ የዘለዓለም ስምንም እሰጣቸዋለሁ።" (ኢሳ. ፶፮፥፬-፭) ብሎ በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ይህን ጽኑ ቃል ኪዳን ተስፋ አድርገው፣ በቅዱሱ ስም ተሰብስበው እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ እግዚአብሔርም ቅዱሳንም ደስ ይላቸዋል። ለተሰበሰቡትም በረከትን ያድላቸዋል።

በቅዱሳኑ ስም ተሰብስበው የማይገባ ሥራ የሚሠሩ ከሆነ ጥያቄው መሆን ያለበትም ሌላ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ለሕዝበ እስራኤል በሚገለጥበት በእግዚአብሔር ድንኳን የማይገባ ሥራ ይሠሩ የነበሩት የዔሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ እግዚአብሔርን አሳዝነው ታቦተ ጽዮንን አስማርከዋል፤ እነርሱም ተቀስፈዋል(፩ኛሳሙ. ፬፥፩፲፩)። እንደዚህ ሁሉ ሰዎች በመደፋፈር እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ተግባር ከፈጸሙ ለመከራ ይዳረጋሉ። እግዚአብሔር ይህን የሚያደርገው ተጸጽተው ንፍሐ ገብተው ለድኅነት እንዲበቁ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች እንዲማሩበት ነው።

ያለምንም ምክንያት ጽዋው ማታ በመውጣቱ ብቻ ያስቀስፋል እየተባለ የሚወራው ትክክል አይደለም። ምክንያቱም ጸዋው ማታ ከቤት በመውጣቱ የሚያስቀስፍ ከሆነ በከተራ ዕለት ታቦተ ሕጉ ማታ ይወጣልና ያን ጊዜ መቅሰፍት መውረድ ነበረበት። ይህ ግን በረከትን የሚያሰጥ እንጂ የሚያስቀስፍ ባለመሆኑ በዚህ ምክንያት የተቀሰፉ ምእመናን መኖራቸው አልተነገረም። ስለዚህ ሰዎች ለሚናገሯቸው ነገሮች ምክንያታዊ ከመሆን በተጨማሪ የሚያደናግር ጉዳይ ሲገጥማቸው መምህራነ ቤተ ክርስቲያንን ብቻ መስማት ይኖርባቸዋል።

**ሐመር መጽሔት፡- የጽዋ ማኅበር መዝከር ከጀመሩ በኋላ ማቋረጥና ጥሎ መውጣትን በተመለከተ የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ምን ይላል?**

**አባ ፍቅረ ማርያም፡-** ጽዋ አንድነት ነው ብለናል። እንዲሁም የሐዋርያትንና የማኅበረ እስጢፋኖስን አንድነት የሚያስረዳ ነው፣ ከዚህም አልፍ ሲል ሰማያዊ አንድነትን የሚያስረዳ ነው ብለናልና እስከ መጨረሻው እንዲዘልቅ ይመከራል። ይሁን እንጂ ከሰዎች አቅም በላይ የሚሆንበት አጋጣሚ እንዳለም ማሰብ ተገቢ ነው። ለምሳሌ፡- የቦታ ለውጥ ሊኖር ይችላል። አዲስ አበባ ይኖር የነበረ ሰው ባሕር ዳር ቢሄድ ከባሕር ዳር እየመጣ በጽዋ ማኅበሩ መሳተፍ አለበት አይባልም። እንዲህ ያለው ይቅርና መንግሥት ቦታውን እፈልገዋለሁ እያለ አንድ አካባቢ የነበሩትን የጽዋ ማኅበርተኞች ወደ ተለያዩ አካባቢዎች ይበታትናቸዋል። በዚህ ጊዜ ከተለያየ ቦታ ተሰብስበው ማከናወን ካልቻሉ አይገደዱም።

በእርግጥ በተቻለ መጠን ከሩቅ ቦታም ቢሆን የቅዱሱ ፍቅር፣ የማኅበሩ አንድነት ስቧቸው ቢሰባሰቡ ራሱን የቻለ ተጋድሎ ነውና የበለጠ በረከትን ያገኙበታል። መከራው በጸና ቊጥር የሚገኘው በረከትም እንዲሁ ይበዛልና ከቻሉ መልካም ነው። ካልቻሉ ግን በዚያው በሚኖሩበት አካባቢ ባሉ የጽዋ ማኅበሮች ገብተው መሳተፍ ይችላሉ። ያንንም ማድረግ ካልቻሉ ደግሞ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ የቅዱሱን መታሰቢያ ማድረግ ከቅዱሱ የሚገኘውን በረከት አያሳንሰውም። በቦታው ያሉት አንድም

ይሁን ሁለትም ይሁኑ የተጀመረውን ማኅበር ቢያስቀጥሉትና እስከ መጨረሻው ቢያዘልቁት ደግሞ ለእነርሱም በረከት ነው:: በፊት ተሰብስበው ለነበሩትም ሳይቀር በረከት ነው::

**ሐመር መጽሔት፡- ከጽዋ ማኅበርተኞች መካከል አንዱ በሞት ቢለይ ሌላ ሰው መተካት ይቻላል ወይ?**

**አባ ፍቅረ ማርያም፡-** ይህም ከላይ ከተገለጸው ጋር በተመሳሳይ ሊታይ የሚችል ጉዳይ ነው:: ልጆች አባት እና እናቶቻቸው ያገኙት የነበረውን በረከት ተረድተው እናስቀጥላለን ካሉ መልካም ነው:: ይሁን እንጂ ልጆች የራሳቸውን ማኅበር መሥርተው ሊኖሩ ይችላሉና እንደ ግዴታ መወሰድ የለበትም:: አንዳንድ ጊዜ ከአባት ወደ ልጅ የሚወረሱ ተግባራት በጊዜው መልካም ቢሆኑም እየዋሉ እያደሩ እንደ ሕግ እየተቈጠሩ እንደ ግዴታ የሚወሰዱበት ሁኔታ ይስተዋላልና ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል:: በአጭሩ በፈቃድ በረከቱን ሽተው ቢያደርጉት መልካም ነው:: ይህ ግን እንደ ግዴታ የሚወሰድ አለመሆኑን መረዳት ይገባል::

**ሐመር መጽሔት፡- በጽዋ ማኅበር የሚባለው ለምሳሌ ማን ነው ባለ ሳምንት የእገሌ ወዳጅ እየተባለ የሚተላለፈው ጽዋና አጠቃላይ ዝግጅቱ ምንን የሚያመለክት ነው ሃይማኖታዊ አንድምታውስ ምንድን ነው?**

**አባ ፍቅረ ማርያም፡-** ሙሴው የሚናገራቸው ነገሮች እጅግ ሃይማኖታዊ መልእክት የሚተላለፍባቸው፣ ጥልቅ ምሥጢር የሚገኝባቸው ናቸው:: ምክንያቱም ከሚናገራቸው ቃላት መካከል ጥቂቶችን ብናነሣ "ሙሴው እጁ ባዳ፣ ዐይኑ በሳሳ ይቅር በሉኝ" የሚል ነውና ሰው በሰውነቱ ፍጹም አይደለም:: ስለዚህ በሚመለከታቸው ነገሮች ዐይኑ ሊሳሳ ይችላል:: ስለዚህ በዚህ ሁሉ ይቅር በሉኝ ማለቱ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ፀሐይ ሳይጠልቅ ቁጣችሁን አብርዱ፤ ለሰይጣንም መንገድን አትስጡ" (ኤፌ.፬፥፳፯) በማለት እንደተናገረው በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የበደለውን በደል ይቅር እንዲሉት መጠየቁ በትክክልም ጉባኤው መንፈሳዊ መሆኑን የሚያስረዳ ነው::

ሌላው ሰጪውና ተቀባዩ የሚለዋወጡት ንግግርም አለ:: እርሱም እንዲሁ ሰጪው እርሱ መስጠቱን በመስጠቱ ሂደትም ችግር ካለ ይቅርታ እንዲያደርጉለት ይጠይቅና ተቀባዩ ማን እንደሆነ ይጠይቃል:: ጸዋ የሞት ምሳሌም ነው:: ስለሆነም በአልናከን የሚቀምሱት የማኅበሩ አባላት የሆኑት ብቻ መሆናቸው የግድ የሚዘክሩ መሆናቸውን ያመለክታል:: ጽዋ ተቀምሶ ሳይዘክሩ እንዲሁ አይሄድም:: ተራቸው እንስኪደርስ ድረስ ተዘጋጅተው በመጠበቅ ተራቸው ሲደርስ መዘከር ይኖርባቸዋል::

ከላይ የተነሣውን "ማነው ባለ ሳምንት፣ ማነው ባለ ወር የቅዱስ እገሌ ወዳጅ" የሚለውን አሳብ ስንመለከትም እግዚአብሔር የውስጣችንን ቢያውቅም ሃይማኖታችን በልባችን የምናምነው፣ በአንደበታችን የምንመሰክረውና በሕይወታችን የምንኖረው ስለሆነ በአንደበታቸው መመስከራቸው እኛም ሃይማኖታችንን መመስከር እንዳለብን የሚያስረዳ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ ተቀባዮች ለሚያደርጉት ዝግጅት ማንቂያና ማስታወሻ ነው::

ሙሴው "ማነው" ብሎ ሲጠይቅ ተቀባዩ "እኔ አለሁ" ብሎ ሲነሣ ማኅበርተኞችም ያውቃሉ:: ተቀባዩም የወደ ፊቱ ጽዋ የእርሱ

> **በእርግጥ በተቻለ መጠን ከሩቅ ቦታም ቢሆን የቅዱሱ ፍቅር፣ የማኅበሩ አንድነት ስቧቸው ቢሰባሰቡ ራሱን የቻለ ተጋድሎ ነውና የበለጠ በረከትን ያገኙበታል:: መከራው በጸና ቍጥር የሚገኘው በረከትም እንዲሁ ይበዛልና ከቻሉ መልካም ነው:: ካልቻሉ ግን በዚያው በሚኖሩበት አካባቢ ባሉ የጽዋ ማኅበሮች ገብተው መሳተፍ ይችላሉ::**

በመሆኑ ሊዘጋጅ እንደሚገባው በማኅበርተኞቹ ፊት ምስክርነት ይሰጣል።

**ሐመር መጽሔት፦ በአንድ ጽዋ ማኅበር ያሉ አባላት መጋባት ይችላሉ አይችሉም የሚል አሳብ በብዙዎች ዘንድ መከራከሪያ ሆኖ ይቀርባልና ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ አንጻር እንዴት ይታያል?**

**አባ ፍቅረ ማርያም፦** ቤተ ክርስቲያን የምትመራበት ፍትሐ ነገሥት አላት። ይህ መጽሐፍ ፍትሕ መንፈሳዊና ፍትሕ ሥጋዊ ተብሎ የተከፈለ ነው። በዚህ መጽሐፍ ጋብቻ የሚከለክለው ለማን እንደ ሆነ ተጽፏል። የሥጋ ዝምድና ሲሆን እስከ ሰባት ቤት ድረስ ቈጥሮ ከሰባት ቤት በኋላ መጋባት እንደሚያስፈልግ ያስረዳል። መንፈሳዊ ዝምድናን ደግሞ የክርስትና አባትና የክርስትና ልጅ መጋባት እንደሌለባቸው በዝርዝር ያስቀምጣል። በዚህ መልኩ የሚከለከለውን ሲዘረዝር በአንድ የጽዋ ማኅበር ያሉ እኅት ወንድሞች አይጋቡም አላለንም።

የሚከለክል ቢሆን ኖሮ የሥጋዊ ዝምድናውንና የመንፈሳዊ ዝምድናውን ዘርዝሮ ሲናገር አብሮ ይህንም ይናገረው ነበር። ስለዚህ ባልተጻፈ ነገር ላይ መጋባት ክልክል ነው ብሎ መናገር ራስ ተተሳስቶ ሌሎችንም ማሳሳት ነው። እንዲያውም ለጋብቻ የሚጠይቁ መሥፈርቶች በሃይማኖት መመሳሰልና የመሳሰሉ ነገሮች በተሻለ መልኩ የተሟላ ይሆናልና ተጠናንተው ትሆነኛለች፣ ይሆነኛል ብለው ቢጋቡ ትዳራቸው የሠመረ ይሆናል።

ቤተ ክርስቲያን ሳታስተምረው፣ በመጽሐፍም ጽፋ ሳታስቀምጠው ሰዎቹ እንደ ልምድ በሚጠቅሱት ኢ መጽሐፋዊ ሕግ የቤተ ክርስቲያን ሕግ እንደሆነ አድርጎ መውሰድ ተገቢ አይደለም።

ይልቅ ቤተ ክርስቲያን በመጽሐፍ የጻፈችውን፣ ሁል ጊዜም በሊቃውንቷ የምታስተምረውን መጠበቅ ያስፈልጋል። አስቀድመን እንደጠቀስነው ቤተ ክርስቲያናችን በመጽሐፍ ባይጻፍም በትውፊታዊ ሕግ የምትጠብቃቸው ነገሮችም አሉ። ይሁን እንጂ ይህንን ጉዳይ አባቶቻችን የተከለከለ ነው ብለው አላስተማሩም። በእርግጥ የተቀደሰውን የጽዋ ማኅበር ለዚህ ዓላማ ብቻ የሚያደርጉት ከሆነ ስሕተት ነው።

ሰው ቤተ ክርስቲያን የሚሄደው ጊዜያዊ ፍላጎት እንዲሟላለት አስቦ ከሆነ ስሕተቱ እዚህ ላይ ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "እናንተስ አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል" ብሏል (ማቴ.፮፥፴፫)። ስለዚህ የጽዋ ማኅበር ለመዝከር ሲያስቡ አስቀድመው ሰማያዊውን በረከት ፈልገው መመሥረት አለባቸው። ከዚያ በኋላ ግን በጽዋ ማኅበሩ ውስጥ ያሉ አባላት ከተፈላለጉና ከተፈቃቀዱ መጋባት ይችላሉ።

**ሐመር መጽሔት፦ አባታችን ከጽዋ ማኅበራት ጋር በተያያዘ ቢጠቀስ የሚሉት ተጨማሪ ነገር ካለ ቢገልጡልን?**

**አባ ፍቅረ ማርያም፦** ጽዋ ማኅበርን በተመለከተ በርከት ያሉ ጉዳዮችን አንሥተናል። ይየሆነው በጽዋ ማኅበራት በርከት ያሉ ክፍተቶች ስለሚስተዋሉ ነው። ምእመናን ልብ ቢሏቸውና ማስተካከል ቢችሉ የምለውን ልጨምር። የጽዋ ማኅበር ሰዎች በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ፣ በቅድስት ድንግል ማርያምና በሌሎች በቅዱሳን ስም ተሰብስበው የተቸገሩትን እንዲረዱ፣ ለተራበ አብልተው በረከት እንዲያገኙ ነው። አሁን አሁን ግን አንዱ ለሌላው የሚከፍለው የዕዳ ክፍያ እየሆነ መጥቷል።

በቅዱሳን ስም ተሰብስበው ቃለ እግዚአብሔር የማይነገርበት፣ የማይዘመርበት፣ ችግረኞች የማይጠየቁበት፣ ከዚህ ይልቅ እገሌ ቤት እንዲያህ ያለ ድግስ ተደገሰ፤ እገሌ ቤት ግን ድግሱ እንደማንኛውም ነበር ብለው የድግስ ውድድር ውስጥ መግባት ትክክል አይደለም። እንዲህ ያለው ድርጊት በረከት የሚገኘው በድግሱ ማማር ብቻ አስመስሎ የሚያሳይና ድሆንችን በማግለል ከበረከት የሚያርቅ በመሆኑ መስተካከል ይኖርበታል። ለሆድ እንጂ ለበረከት አለመሰብሰብንም ያሳያል።

ከላይ ከተጠቀሱት ችግሮች በተጨማሪ የስብስቡ መሠረታዊ ተግባር ዋዛ ፈዛዛ የሚስተዋልበት፣ ተራና ሥጋዊ ነገሮች ብቻ ጎልተው የሚስተዋሉበት እየሆነ መጥቷል። ከዚህ ይልቅ ቃለ እግዚአብሔርን የሚማሩበት፣ ስለ መንፈሳዊ ሕይወታቸው የሚወያዩበት፣ ችግረኞችን የሚጠይቁበት መሆን አለበት። በመካከላቸውም የሚገኙ የንስሓ አባቶችና መምህራንም ይህን ጉዳይ አስመልክተው ማስተማርና ችግሮችን ማስተካከል መቻል አለባቸው። እንደ ሥርዐቱ የማይኳዝ የጽዋ ማኅበር ዓላማውን ይስታል፤ ለመናፍቃንም የተጋለጠ ይሆናል።

መናፍቃን ዛሬ እንዲህ ለይቶላቸው ከቤተ ክርስቲያን ወጥተው የራሳቸውን አዳራሽ እስከመሠረቱበት ጊዜ ድረስ ቤተ ክርስቲያንን ሲያስድዷት የኖሩት ቤተ ክርስቲያን እየመጡም ሆነ ሳይመጡ በየቤቱ በጽዋ ማኅበር ስም በሚያደርጉት ስብስብ ነበር። ስለዚህ ምእመናን በቅዱሳን ስም መሰብሰባቸው መልካም ነው፤ ከተሰበሰቡ በኋላ ግን የተሰበሰቡት እንደ እድር፣ እንደ ዕቁብ ሳይሆን እግዚአብሔር ለቅዱሳኑ የገባላቸውን ቃል ኪዳን አምነው ነውና ከቅዱሳኑ በረከትን ለማግኘት ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው ማድላት ይኖርባቸዋል።

**ሐመር መጽሔት፦ ጥያቄዎቻችንን በሚገባ ስለመሱልን በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን።**

**አባ ፍቅረ ማርያም፦** እኔም አመሰግናለሁ።✠